ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ባሕላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በለሊሳ ገጠር ቀበሌ ማህበረሰብ ተተኳሪነት

በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ

ሙኒራ ጀማል አባ ቡልጉ

ሰኔ፣2011ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ባሕላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በለሊሳ ገጠር ቀበሌ ማህበረሰብ ተተኳሪነት

በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ

ሙኒራ ጀማል አባ ቡልጉ

ዋና አማካሪ

ጌታቸዉ አንተነ (ደ/ር)

ረዳት አማካሪ

ሃብታሙ እንግዳዉ

ሰኔ፣2011ዓ.ም

# ባሕላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ  ትንተና በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በለሊሳ ገጠር ቀበሌ ማህበረሰብ ተተኳሪነት

በ

ሙኒራ ጀማል አባ ቡልጉ

ሰኔ፣2011ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| ______________________ | ______________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________ |
| ረዳት ኣማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________ |
| የዉስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

## ማዉጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


ማዉጫ ........ III
ምስጋና ........ VI
አጠቃሎ ........ VII
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.2 የጥናቱ አላማ ........ 4
1.3 የምርምር ጥያቄዎች ........ 4
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 5
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.6 በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 6
1.6.1 ያጋጠሙ ችግሮች ........ 6
1.6.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 7
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማች ጥናቶች ቅኝት ........ 8
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቶች ........ 8
2.1.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት ........ 9
2.1.2 ቁሳዊ ባህል የመጠናት ፋይዳ ........ 11
2.1.3 የቁሳዊ ባህል ትንታኔ ........ 12
2.1.4 የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ስልቶች ........ 13
2.1.4.1 ትዕምርታዊነቱ ........ 14
2.1.4.2 ባህላዊነቱ ........ 14
2.1.4.3 ታሪካዊ ጥበብ አመልካች ........ 15
2.1.4.4 አካባቢያዊነት ........ 15
2.1.4.5 አገልግሎቱ ........ 15
2.1.4.6 መዋቅራዊነቱ ........ 15
2.1.4.7 ባህርይ ጠቋሚነት ........ 15
2.1.4.8 ማህበራዊነቱ ........ 16
2.1.4.9 የማህበረሰብ ታሪክ ገላጭነት ........ 16
2.1.5 ቁሳዊ ባህል እና ምደባ ........ 16

2.1.6 የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ........ 17
2.1.7 ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ........ 18
2.1.8 የሸክላስራ ታርክ በአለም ........ 18
2.1.9 የሸክላስራ ታርክ በአፍሪካ ........ 19
2.1.10 የሸክላ ስራ ታሪክ በኢትዮጵያ ........ 20
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 24
2.3 ጥናቱ የተካሀደበት አካባቢያዊ ዳራ ........ 27
2.3.1 የወረዳዉ ህዝብ ብዛት ቋንቋና ሓይማኖት ........ 27
2.3.2 የወረዳዉ ህዝብ መተዳደርያና መሰረተ ልማት ........ 27
ምዕራፍ ሶስት ........ 29
የአጠናን ሥነ ዘዴ ........ 29
3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 29
3.2 የጥናቱ አካላይ ........ 29
3.3.1 የቦታ ናሙና አመራረጥ ........ 30
3.3.2 የመረጃ ሰጪዎ ናሙና አመራረጥ ........ 31
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 31
3.5 ቀዳማይ የመረጃዎች መሰብሰብያ ዘዴ ........ 31
3.5.1 ቃለመጠይቅ ........ 32
3.5.2 ምልከታ ........ 33
3.5.3 ተተኳሪ ቡድን ዉይይት ........ 34
3.6 ካላአይ የመረጃዎች መሰብሰብያ ዘዴ ........ 34
3.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 35
3.8 የመስክ ቆይታ ........ 35
ምራፍ አራት ........ 37
የጥናቱ የመረጃ ትንተና ........ 37
4.1 የለሊሳ ቡላ ገጠር ቀበሌ የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ ........ 37
4.2 የሸክላ ሰራተኞች /ባለሙያዎች ጥበቡን የለመዱበት ሁኔታ ........ 41
4.3 የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደት እና ጠቀሜታ መተንተን ........ 45
4.3.1 የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደት ........ 45
የሸክላ ስራ ሂደቶች ወይም ደረጃዎች ........ 45
4.3.1.1 ቁፋሮ ........ 46
4.3.1.2 ቁሱን መስራት ........ 47

4.3.1.3 ቅርጽ ማውጣት ........ 48
4.3.1.4 ማቃጠል/መቶከስ ........ 54
4.3.2 የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ ........ 55
4.3.2.1 ማህበራዊ ጠቀሜታ ........ 55
4.3.2.2 ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ........ 55
4.3.2.3 ምግብ ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ........ 56
4.3.2.4 የሸክላ ቁሶች ባህላዊ አገልግሎት ........ 56
4.3.2.5 ሀብታምነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች ........ 56
4.3.2.6 ድህነትን የሚያመላክቱ የሸክላ ቁሶች ........ 56
4.3.2.7 ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ........ 56
4.4 ጾታዊ ተሳትፎ ........ 57
4.5 የሸክላ ሰራተኞቹ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ ያጋጠሟቸዉ ችግሮች ........ 60
4.6 የማህበረሰቡ አሉታዊ አመለካከት ........ 61
4.7 የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር ........ 66
4.8 የሙያዉ ቀጣይነት ........ 67
ምዕራፍ አምስት ........ 68
ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ ........ 68
5.1 ማጠቃለያ ........ 68
5.2 የይሁንታ ሃሳብ ........ 69
ዋቢዎች ........ 71
አባሪዎች ........ 74

# ምስጋና

በቅድሚያ ለዚህ ላበቃኝ አላህ አለህምዱልላህ በማለት ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ በመቀጠል ጥናቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜዉ አቅጣጫ በመስጠት እና በማረም ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ ከፍተኛ እገዛ ላደረጋችሁልኝ አማካሪዎቼ ዶ/ር ጌታቸዉ አንተነህ እና አቶ ሀብታሙ እንግዳዉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡

የድህረ ምረቃ ትምህርት እድከታተል እና ይህንን ጥናት እንዳካሂድ ፍቃድ ለሰጠኝ የኦሞ ናዳ ወረዳ ትምህርት ቢሮ እና ቀና ትብብራችሁ ላልተለየኝ መረጃ አቃባዮቼ በተለይ ባለ ሙያዎቹ እና ሌሎች ማህበረሰቦች የጉደታ ቡላ ነዋሪ መምህር አወል አባ ዲጋ እና ባለቤቱ ሚስኩ አባ ጊዲ ላደረጋችሁልኝ ትብብር ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነዉ ፡፡

የግልህ የስራ ጫና እና ድካም እንዲሁም የጊዜ እጥረት ሳይገድብህ ይህ ጥናት ስኬታማ እንዲሆን የገንዘብ እና የሃሳብ ድጋፍ ላደረክልኝ ዉዱ ባለቤቴ ዶ/ር ሱልጣን ጀበል ዕድሜህን ያርዝምልኝ እያልኩ የልፋትህ ፍሬ ደርሷል እና እንኳን ደስ አለህ ልልህ እወዳለሁ ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ኦሞናዳ ወረዳ የለሲሳ ቡላ ገጠር ቀበሌ ማህበረሰብ ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና በሚል ርእስ የተካሄደ ነዉ ። ጥናቱ ባለሙያዎቹ ባህላዊ እዉቀታቸዉን ተጠቅመዉ የሚሰሩ የሸክላ ዉጤቶች ጠቀሜታቸዉ እና የቁሶችን አሰራርና አገልግሎት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ ተመርኩዞ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደረጃቸዉን ለማሳየት አልሞ የተነሳ ነው ።

አጥኚዋ የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የቤተ መጻሃፍት ንባብ እንዲሁም ጥናቱ በሚከናወንበት ቦታ ላይ በአካል በመገኘት በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችላለች።መረጃዎቹን እንደ አስፈላጊነቱ በቪዲዩ እና በፍቶ ግራፍ ሰንዳዋለች ። መረጃ አቀባዮች የተመረጡበት መስፈርት አላማ ተኮር ናሙና ሲሆን የአከባቢዉን ባህል ጠንቅቆ የሚያዉቁ ፣በሞያቸዉ የታወቁ እና ለብዙ ጊዜ ሙያ ዉስጥ የቆዩ ፣ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ ከወጣት እስከ ሽማግሌ የእድሜ ክልል ዉስጥ ያሉና በታሪክ አዋቂነታቸዉ በአካባቢዉ ማህበረሰብ የታወቁ ናቸዉ ።

ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ካለዉ አሉታዊ አመለካከት የተነሳ ለሰነልቦናዊ ጥቃት እንደተጋለጡ ታይቷል ። የሸክላ ባለሙያዎች ደረጃ ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ጋር በሰርግ፣በለቅሶ፣በወሊድ እና በህመም መሰል የማህበራዊ ህይወት ላይ እንደሚሳተፉ እና ጋብቻ የሚያከናዉኑት ግን ከራሳቸዉ ሰዎች ጋር እንደሆነ እና አሁን አሁን በጋብቻ የመቀላቀል ሁኔታ አንድ ሁለት እንደታየ በጥናቱ ታዉቋል ።ከላይ የቀረቡትን የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ አጥኚዋ የሚመለከታቸዉን የወረዳ ባለሙያዎች ፣የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ፣በአካባቢዉ የሚገኙ የሀይማኖት አባቶች ፣ወዘተ ማህበረሰቡ በሙያዉ እና በሙያተኞቹ ላይ ያለዉን የተዛባ አመለካከት እንዲቀይር ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ቢሰሩ የሚሉ ይሁንታዎችን ሰንዝሯለች ። በተጨማሪም አጥኚዋ ባለሙያዎቹ የሸክላ መስሪያዉን አፈር ከግለሰብ በገንዘብ እየገዙ በመሆናቸዉ የአከባቢዉ የመንግስት ኃላፊዎች የሸክላ አፈር የሚቆፍሩበትን ቦታ ቢሰጣቸዉ መልካም ነዉ የሚል አስተያየት ለመሰንዘር ትወዳለች ።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ባህል የሰዉ ልጅ የማንነቱ መገለጫ እና ከዓለም ጋር ያለዉን መስተጋብር የሚያመለክቱ መንፈሳዊ ፣ቁሳዊ ፣ አዓምሮአዊ፣ጥበባዊና ገቢራዊ እሴቶች ስብስብ ፣የእርስ በእርስ ግንኙነቶች ፣ዕምነቶች ፣ ልማዶች እና ባህሪዎች ዉስብስብ እንቅስቃሴና ፍች ነዉ ። ባህል የሰዉ ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻሉት ወይም ከሌሎች ፍጡራን ለመለየት ያበቁት ማንኛቸዉም ምሁራዊ ፣ሥነ ምግባራዊ ፣አካላዊ ፣ ቴክኒካዊና ሌሎችም ስራዎች ሁሉ ፣ እንዲሁም የሰዉ ልጅ የመማር ፣በቴክኒክ እና በአዕምሮ ዕዉቀት ራሱን የማሰልጠን ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሃሳብ ነዉ ። እንዲሁም አንድ ህዝብ ከሌላዉ ተለይቶ የሚታወቅባቸዉ ሁኔታዎች ማለትም የአኗኗር ዘይቤዎቹን፣ዕምነቶቹን ፣ ባጠቃላይ ቁሳዊ እና ህሊናዊ ሀብቶቹን የሚያካትት ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነዉ ። ባህል በተመሳሳይ ድንበር ክልል በሚገኙ ህዝቦች መካከል እየተተገበረ የሕዝቦችን ተመሳሳይነትና አንድነት የሚያሳዩና ለመጪዉ ትዉልድ እንዲቆዩለት የሚፈልጋቸዉን ጉዳይዎች የሚወክል ነዉ ይላሉ (Mbakogu,2004 ;Storey<2009 ):: ሌሎች ደግሞ ባህል ረቂቅ የሆነና በተለያየ መልኩ የሚገለጽ የአንድ ማህበረሰብ ዕዉቀት ማስተላለፍያ መንገድ እንደሆነ ይገለጻል ። የሰዉን ልጅ አጠቃላ ልማዳዊ ባህሪን የሚያደራጁ ማህበራዊ ልማዶችና ቁሳዊ ሁነቶች በአመለካከት ፣በንግግር፣ በድርጊት ፣ በዕደ ጥበብ ፣የሚገልጹበት ትምህርት እና ዕዉቀት የሚተላለፍበት ነዉ።

ቁሳዊ ባህል የምንላቸው የሰው ልጅ በስሜት ህዋሳቱ አማካኝነት የሚያያቸው፣ የሚዳስሳቸው፣ የሚያሽታቸው የመሳሰሉትና ተፈጥሮ በለገሠችው ነገር የራሱን የፈጠራ ብቃት አክሎ የሚሠራቸው ነገሮች ሲሆኑ ዘመናዊ ስልጣኔ ከመታየቱ በፊትና ኢንዱስትሪዎች ከመቋቋሚቸዉ ቀድሞ የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ክንዋኔውን ይከውንባቸዉ የነበሩ ቁሳቁሶችን አጣምረው የያዙ ነገሮች ናቸው።

ከላይ ከቀረበው ሀሣብ የምንረዳው የሰው ልጅ ተፈጥሮ በለገሠችውና በአካባቢው በሚያገኛቸው ነገሮች የራሱን የፈጠራ ክህሎት ጨምሮ የሚሠራቸውን እና እንደየ ባህሉ፣ እንደ አስተሳሰቡ፣

እንደ እምነቱ፣ እንደ ፍልስፍናው የሚሠራቸውን አልባሳት፣ለመኖሪያነት የሚሠራቸውን ቤቶች የመሳሰሉትን እንደሚያጠቃልል ልብ ይሏል፡፡ ቁሳዊ ባህል የአንድን ዘመን ምንነት /አሻራ የሚያመለክት ሲሆን የዘመኑን ማኅበረሠብ ፖለቲካዊ አቋሙ፣ ንቃተ ህሊናው፣ የፈጠራ ብቃቱ፣ ወጉ፣ እምነቱና ፍልስፍናው ምን ይመስል እንደ ነበር የምናውቅበት ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

በሀገራችን በስፋት ከሚታወቁት የእጅ ስራዎች መካከል የሽመና፣ የሸክላ ስራ፣ የስፌት ስራ፣ የብረት ስራ፣ የቀርቀሃ ስራ፣ የቆዳ ስራ፣ የቀንድ ስራ የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሀገረሰባዊ እጅ ስራዎች በየአከባቢው በሚገኙ የጥበብ ባለሙያዎች አመካኝነት ተዘጋጅተው ለማህበረሰቡ የእለት ተእለት ህይወት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ለማከናወንና መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት በተመለከተ Prown እና Mayo እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ Prown [1982፣3] «Inherent and Attached value,The most obvious culture belief associated with material objects has to do with value.» ይላል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ ቁሶች ከእለት እለት ግልጋሎት ባሻገር የተለየ እሴት የሚገለፅባቸው መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እሴቶቹም ተፈጥሯዊ ወይም ሰዎች የሚያበጁቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሀብታሙ (2001፡13-14 ) Glassie እና prown ጠቅሶ እንደ ጠቀመዉ ጽንሰ ሀሳቡ ተጨባጭ ለሆኑና የሰዉ ልጅ ባህሉን መሰረት አድርጎ የሚያበጃቸዉን ቁሶች የሚመለከት ሲሆን ቁሶቹ የጽንሰ ሀሳቡ መሰረታዊ ጉዳይ ይሁኑ እንጂ በራሳቸዉ ግን ግብ አለመሆናቸዉን ነዉ ፡፡ ይህም ጥናቱ ቁሶቹን መሰረት አድርጎ ከቁሶቹ ባሻገር የሚገኘዉን የሰዉ ልጅ አስተሳሰብ እና ግብ ይመረምራል ማለት ነዉ፡፡ እርግጥ ነዉ የቁሳዊ ባህል ጥናት መሰረታዊ ጉዳይ ቁስ ነዉ ፡፡ ይሁን እንጂ ቁሱን ብቻ ተመልክቶ ቁሱ የተሰራበትን ንጥረ ቁስ እና አገልግሎት መግለጽ ብቻዉን በቂ አይሆንም ፤ የጥናት መስኩ አላማም አይደለም ፡፡ ዋና ጉዳዩ ቁሱን ስለ ሰሩት የሰዉ ልጆች ማህበራዊ ፣ ባህላዊ ፣ ሀይማኖታዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ጉዳዮች እያነሱ መፈከር (interpret )ማድረግ ነዉ ፡፡

Prown (1982) ቁሳዊ ባህል በተወሰነ ጊዜ የነበረን ማህበረሰብ በቁሶቹ አመካኝነት ስለ ቁሶቹ ባለቤት እምነት ፣ እሴት ፣ሀሳብና አመለካከት ትንታኔ ወይም መላምት የሚቀርብ የጥናት

ዘርፍ እንደሆነ ነዉ ። ጽንሰ ሀሳቡ ብዙ ጊዜ ቁሶቹን የሚያመለክት ሆኖ የጥናት ዘርፉ መጠሪያ በመሆን እንደ ሚያገለግልም ልብ ይለዋል ።

Schlereth, Thomas. ኢንተርኔት ዉስጥ (2017,7-8) ለቁሳዊ ባህል ጥናት ይበጃል ያላቸውን ዘጠኝ የመተንተኛ ሞዴሎችን ዘርዝሯል፡፡የቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት አቅጣጫዎችን በመጠቆም ስለ ቁሳዊ ባህል ምንነት ምሁራን የሰጡትን ሀሳቦች በመጠቆም የቁሳዊ ባህል ትኩረት መሆን ያለበት ነገሮች ለምን ተሰሩ? እስካሁን ድረስ ያነሳዉን ሀሳቦች እንዲሁም ቁሶቹ ምን ማህበራዊ፣ጥበባዊ ወይም ትምህርታዊ አላማን በማመልከት ተወከሉ? የሚሉትን ጉዳዮች ማብራራቱ ላይ መሆኑን ገልጸዋል::

ቁሳዊ ባህል ማለት አንድ ማህበረሰብ ባህላዊ እዉቀቱን እና ጥበቡን ተጠቅሞ በእጁ የሚሰራቸዉን የተለያዩ ባህላዊ ቁሳቁሶችን የሚያመለክቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በመሆኑም የተለያዩ የፎክሎር ውጤቶች የፈጣሪያቸው ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ላይ ትኩረቱን አድርጎ የተሰራ ሲሆን የኦሞ ናዳን ወረዳ በማሳያነት የሚያቀርብ ነው፡፡ስለ ባህላዊ የሸክላ ስራ ምንነት ፣ ታሪካዊ ዳራ ስለ ሚሰጡት ጥቅሞች እና የሸክላ ስራ ባለሙያዎች የሚሰሩት ቁሶች ስላላቸዉ ጥብቅ ቁርኝት ብዙ ተብሏዋል::

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ይህን ጥናት እንድታጠና ያነሳሳት ምክንያት ጥናቱ በተሰራበት አካባቢ በመምህርነት ተቀጥራ ለሶስት አመት ስታገለግል የተመለከተችዉ ለየት ያለ ክስተት ነዉ፡፡ በቆይታ ጊዜዋ ከተለያየ ክፍል ሶስት ተማሪዎች ለመማር ትምህርት ቤት ከደረሱ በኋላ ወደ ተማሪዎች ለመቀላቀል ፍላጎት በማጣት በፍራቻ ይሁን በጥላቻ ባይገባትም ለብዙ ወራቶች በር ስር እየቆሙ ተማሪ ሲለቀቅ አብረዉ ወደ ቤታቸዉ ሲገቡ ትመለከታለች ። ስለተማሪዎቹ ስታጠያይቅ የተመለሰላት መልስ "የሸክላ ሰሪ ልጆች ናቸዉ" የሚል ነበር:: ከዚህ በመነሳት ስለ እነሱ ስታሰላስል ቆይታለች እነዚህ የሸክላ ስራ ባለሞያዎች እያበረከቱት ያለዉ አስተዋጽኦ የጎላ ሆኖ እያለ የማህበረሰቡ አስተያየት ግን ከዚህ የተለየ ነዉ ። ማህበረሰቡ የሚሰጣቸዉን አላስፈላጊ ስሞች እና የሚወራባቸዉን አንዳንድ ጉዳዮች ለማስቀረት በጉዳዩ ላይ ጥናት ብታደርግ እና ዉጤቱን ለማሳወቅ ብትሞክር ለእነሱም ሆነ ለአከባቢዉ ህዝብ የምታበረክታት ትንሽ ነገር ዉጤት ልታስገኝ ትችላለች ከሚል አስተሳሰብ የተነሳ ነዉ ።

ሁለተኛዉ ምክንያት በለሊሳ ቡላ ቀበሌ ማህበረሰብ ላይ በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና የሚያሳይ ጥናት ባለመኖሩና በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ የታዩ ክፍተቶችን በተወሰነ መልኩ ሊሞላ ይችላል በሚል እሳቤም ጭምር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞናዳ ወረዳ የለሊሳ ቡላ ቀበሌ ማህበረሰብ ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና ላይ ያተኮረዉ ይህ ጥናት የሚከተሉት አላማዎች አሉት ፡፡

- ❖ ባለ ሙያዎቹ ለዘመናት በቆየ ሙያቸዉ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደ ሆኑ በመመርመር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደረጃዎቹን ማሳየት፤
- ❖ ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉትን ቅርፅ መግለፅ እና ቁሶችን በምን አይነት ዘዴ እንደሚያበጁ ማሳየት፤
- ❖ የሸክላ ባለ ሙያዎቹን ህይወት እና ልምድ መመርመር፤የባለ ሙያዎቹን የወደፊት እጣ ፋንታ ከሙያዉ መቀጠል አንጻር እና ቁሶች የሚሰጡት አገልግሎት ምን እንደ ሚመስል ማሳየት፤
- ❖ የሸክላ ባለሙያዎች በመገለላቸዉ ምክንያት የሚደርስባቸዉን ስነልቦናዊ ተጽዕኖ መፈተሽ የሚሉት ይገኙበታል፡

## 1.3 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎችን መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ይመልሳል ተብሎ ይታሰባል ፡፡

- ➢ በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን እኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደረጃዎችን በምን መልኩ ያሳያሉ?
- ➢ ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድነዉ ? ቁሶችን በምን አይነት ዘዴ ያበጃሉ?
- ➢ የሸክላ ባለ ሙያዎች ህይወት የወደፊት እጣ ፋንታ ከሙያዉ መቀጠል አንጻር እና ቁሶች የሚሰጡት አገልግሎት ምን ይመስላል?
- ➢ የሸክላ ባለ ሙያዎች በመገለላቸዉ ምክንያት የሚደርስባቸዉ ስነልቦናዊ ተጽዕኖ አለ?

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት  የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡ለአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሁፍ እና ፍክሎር  ትምህርት  ክፍል የሚያስገኘው  ጠቀሜታ  በቁሳዊ  ባህል  ጥናት ውስጥ ጎልተው የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በተወሰነ መልኩ ይሞላል፡፡ ባለ ሙያዎቹ ባህላዊ እዉቀታቸዉን ተጠቅመዉ የሚሰሯቸዉን ባህላዊ የሸክላ ዉጤቶች በምን አይነት የአሰራር ሂደት እንደ ሚያልፉና እንዲሁም ባህላዊ የሸክላ ዉጤቶች የአሰራር ሂደት እና ጠቀሜታ በዝርዝር ያሳያል ፡፡

ይህ ጥናት የባለ ሙያዎቹን ባህላዊ እዉቀት እና የሚሰሩትን የተለያዩ የሸክላ ዉጤቶች አሁን ባለበት ሁኔታ በፎቶ ግራፍ እና በቪዲዮ ቀርሶ ለመጪዉ ትዉልድ ለማስተላለፍ ይጠቅማል ፡፡

ለተጠኚዉ የማህበረሰብ ክፍሎች በቁሶቹ አመካኝነት ባህላቸዉን የበለጠ እንዲ ያስተዋዉቁ እድል ይሰጣል ፡፡ለወረዳዉ በህልና ቱሪዚም ጽህፈት ቤት የሚሰጠዉ ጠቀሜታ ደግሞ በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች መስብ የሚሆንበትን መንገድ ይጠቁማል ፡፡

ወደፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያለዉ ጥናት በስፋት እና በጥልቀት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች መንደርደሪያ በመሆን ያገለግላል ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታ አንጻር  በኦሮሚያ ክልል  በጅማ ዞን ኦሞናዳ ወረዳ በለሊሳ ቡላ ገጠር ቀበሌ ብቻ  የተወሰነ ነው፡፡

ከሚጠናዉ ርዕሰ ጉዳይ አንጻርም በቁሳዊ ባህል ላይ መሰረት አድርጎ  የተቃኘ ሲሆን  ቁሳዊ ባህል በስሩ በርካታ ዘርፎች ቢኖሩትም፣ ጥናቱ ሀገረሰባዊ እጅ ስራን በማንሳት በተለይም ደግሞ ሀገረሰባዊ የሸክላ ስራ እና የማህበረሳቡን የኑሮ ዘይቤ ለመመልከት የተወሰነ ነዉ ፡፡

## 1.6 በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በዚህ ርእስ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና ችግሮቹን ለመቅረፍ የተወሰዱ መፍትሔዎች ቀርበዋል፡፡

### 1.6.1 ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት የመስክ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም፡፡ መስክ ላይ አጥኚዋን ካጋጠሟት ችግሮች በመጀመሪያ ዙር በጥር 16 / 2011 መረጃ ለማሰባሰብ ወደ ቦታዉ ሄደች፡፡ በወረዳዉ ባህል እና ቱሪዝም ጥቆማ መሰረት ያገር ሽማግሌ ጋሊ አባ/ዲጋ ቤት በመሄድ የሄደችበትን አላማ ስታስረዳዉ “ችግር የለዉም እወስድሻለሁ ፤በቅድሚያ እነሱን ማነጋገር ሰላለብኝ የዛሬ ሳምንት ነይ” ብሎ ቀጠሮ አሲዞ ያለምንም መረጃ ተመልሳ ገባች ፡፡

ሁለተኛዉ ችግር በሳምንቱ በ 22/06/2011 በቀጠሮ ቀን ተመልሳ ሄደች ፡፡ ልክ ከመኪና ወርዳ የእግር መንገድ ስትጀምር ከየት እንደመጣ የማይታወቅ ዝናብ ወረደባት ፡፡ በአቅራቢያዉ የሰዉ ቤት የለም ፤ ብትቆምም ዝናቡ ያዉ ስለ ሆነ መንገዱን ተያያዘችዉ፤በዝናብ ከአስፓልት የአንድ ሰአት መንገድ ተጉዛ የጋሊ ቤት ደረሰች፡፡ ቡና ተፈልቶላት ጠጥታ ያቀረቡላትን ነገር ቀማምሳ እየተጫወቱ ዝናቡ አባራ፡፡ “በቃ አንሂድ” ብላ ብትጠይቀዉ “ሰዎቹን አስፈቅጃለሁ ነገርግን ጭቃዉ አያስኬድሽም፤ ሌላ ጊዜ ደዉዬልሽ ብትመጪ ይሻላል” አላት፡፡ “እችላለሁ” ብላ ብትለምነዉ “እንደማትችይ ስለማወቅ ዛሬ አንሄድም” በማለት ተስፋ ሲያስቆርጣት ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡

በጥናቱ ያጋጠማት ሶስተኛው ችግር አንዳንድ መረጃ አቀባዮች መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ ድምጻቸው በቴፕም ሆነ በቪዲዮ ካሜራ እንዳይቀረጽ መከልከላቸዉና ፎቶ ግራፍ አንነሳም ማለታቸው ነው፡፡

አራተኛዉ ችግር ጥናቷን እሷ የምታካሂድበት ቦታ ገጠር እንደመሆኑ የተወሰነ መንገድ በመኪና መጓዝ አለባት፡፡ ነገር ግን እዛ ቦታ ላይ ትራንስፖርት ከሀሙስ እና ከቅዳሜ ዉጪ እንደልብ አይገኝም፡፡ በነዚህ ቀናት እንዳትመላለስ ሀሙስ የደነባ ገብያ ቅዳሜ የአሰንዳቦ የገብያ ቀን እንደ መሆኑ መረጃ አቀባዮችም ሆኑ የሸክላ ባለሙያዎች ቤት አይገኙም፡፡

### 1.6.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

አጥኚዋ መስክ ላይ ያጋጠሟትን ችግሮች የፈታችዉ በሚከተለው መልኩ ነው፡፡

አንደኛዉ ችግር የተቃለለዉ በስልክ ጥሪ ጥቆማ መሰረት ወደ ባለሞያዎቹ ቤት በመሄድ የመጣቹ ለጥናት እንደሆነ ስታስረዳቸዉ እነሱም ያለ ምንም ማመንታት እኛ "ከህግም ሆነ ካሀገር ሽማግሌ የሚያስወጣን ምንም ችግር የለብንም" በማለት ፍቃዳቸዉን ስለሰገሱ በዚህ መሰረት ጥናቷን ለማካሄድ ችላለች፡፡

ሁለተኛዉን ችግር የፈታችበት መንገድ ይህችግር በድጋሚ እንዳይደገም ካገር ሽማግሌ ከጋሊ አባ/ዲጋ ጋር በስልክ በመነጋገር ባለሞያዎች ከቤት በማይወጡበት እና ዝናብ በማይዘንብበት ቀን እየተደዋወለች እሱ በሚሰጣት መረጃ መሰረት እየተመላለሰች ጥናቷን ለመከታተል ችላለች፡፡

ሶስተኛዉን ችግር የፈታችበት መንገድ ደግሞ ድምጻቸዉን በቴፕ እና በቪዲዮ ካሜራ ለማስቀረጽ ያልፈለጉትን እንዲሁም ምስላቸዉን በፎቶ ግራፍ ለመስጠት "በአይማኖታችን የተከለከለ ነዉ" በማለት ፍቃደኛ ያልሆኑትን መረጃ አቃባዮች መረጃዉ ጠቃሚ እንደመሆኑ በማስታወሻ ላይ ለማስቀመጥ ሞክራለች፡፡

አራተኛዉን ችግር ያቃለለችበት ሁኔታ በቀጠሮ ቀኗ ባጃጅ ወይም ሞተር ኮንትራት በመያዝ ከጥናቷ ሳትሰናከል በዚህ መልኩ ችግሮቿን ለመፍታት ችላለች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማች ጥናቶች ቅኝት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቶች

ይህ ክፍል ከሚጠናዉ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ማለትም ሰለ ቁሳዊ ባህል ፣ በቁሳዊ ባህል ስር ስለ ሚጠናዉ ሀገረሰባዊ እጅስራ ፣ ስለ ሸክላ ስራ ምንነት እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የመስኩ ምሁራን ምን ምን ሀሳቦችን እንዳቀረቡ የቀረበበት ነዉ ፡፡

> ፈቃደ (1991፣15) "ቁሳዊ .ባህል በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንድስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣የቅመም አቀማመም ብላሃትን፣የልብስ፣የቤት፣የአጥር ወዘተ አሰራርን ፣ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሳሪያዎችን እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው፡፡ እቃውን እራሱን ማጥናት አንድ ዋና ተግባር ሲሆን አሰራሩን ማጥናት ደግሞ ሌላው ነው ማለት ነው" ይላል፡፡

ከላይ ካቀረበው ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ መሆናቸውን ነው፡፡ቁሶቹ ከምንና እንደምን ካለ ብልሃት ይሰራሉ? ቁሶቹ የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ ፈለቀ? የሚሉትን ጥያቄዎችን ለመመርመር የሚያስችል ነው፡፡በቁሶቹ አሰራር እና አገልግሎት መነሻነት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚመረምር መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

Dorson (1972፣ 2) "ቁሳዊ ባህል የዘመን አሻራን የሚጠቁሙ ራሳቸዉ ሰዎች አበጅተዋቸዉ ፣ለኑሮሯቸዉ ፣ ለጌጣጌጣቸዉ ፣ለመዝናኛቸዉ የሚገለገሉባቸዉ እና ህይወታቸዉን ለመጠበቅ የሚዉሉ መሳሪያቸዉን የሚያካትት ፣ መሆኑንገልጸዋል ፡፡ከዚህ የምንረዳዉ ሀሳብ ቁሶች በተለያየ ዘመናት ዉስጥ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች ምን እንደሚመስል የሚገልጽ መሆኑን ነዉ ፡፡ የተለያዩ ቁሶችን ሰርተዉ የእለት ተዕለት ተግባራቸዉን መከወኛነት ፣ለማስዋቢያ እና ለማደሻነት እንደሚያዉሏቸዉ የሚያስ ገነዘብ ነዉ ፡፡ በሌላ በኩል ሕይወታቸዉን ከሚጎዱ እንስሳትም ይሁኑ ሰዎች ራሳቸዉን የሚከላከሉበትን ቁሳቁስ አቅፎ የያዘ መሆኑን የሚያመለክትነዉ ፡፡

ሰለሞን (2007 Glassie 1968፤10)ን ጠቅሶ እንደገለጸው ቁሳዊ ባህል የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ ታሪክ፣እምነት፣ሀይማኖት፣ባህል ወዘተ መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የዘመን ተሞክሮ አሻራዎች የሚያሳዩ ጥበባዊ ውጤቶች ናቸው። Brooner(1986፤100)ቁሳዊ ባህሎችን ስናጠና ትኩረታችን የቁስ ቅርጽ ላይ ማድረግ እንደሚኖርብንና ቅርጹም የቁሱን ቋሚና የሚታዩ ገጽታዎችን በዋናነት የሚያሳይ መሆን እንዳለበት ይገልጻል።

Prown (1982፤1 )በበኩሉ የቁሳዊ ባህልን ምንነት ሲገልጽ «Material culture is study of through artifacts of the beliefs, values, ideas, attitudes and assumption of a particular community or society at a given time.» ይላል። ቁሳዊ ባህል የትኩረት አቅጣጫው በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶቹ ስለበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍል እምነት፣አስተሳሰብ፣እሴት፣አመለካከትእና መላምታቸውን የሚመረመርበት መሆኑን የሚጠቁም ነው።

ፈቃደ (1991፤15) ፤ Dorson (1972፤ 2)፤ ሰለሞን 2007 ( Glassie 1968፤10) እና Prown (1982፤1 ) እነዚህ ምሁራኖች ካቀረቡት ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ መሆናቸውን ነው። ቁሶቹ ከምንና እንደምን ባለ ብልሃት ይሰራሉ? ቁሶቹ የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ ፈለቀ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመርመር የሚያስችል ነው። በቁሶቹ አሰራርና አገልግልት መነሻነት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚመረመርበት መሆኑን የሚጠቁም ነው።ከቁሶቹ አሰራር እና አገልግሎት ውስጥ ተፈልቅቀው የሚወጡ አስተሳሰቦችን በመመርመር ቁሶቹ የበቀሉበትን የማህበረሰብ ክፍሎች ያላቸውን አስተሳሰብ፣እምነት፣ማህበራዊ ደረጃ እና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም የህይወት ፍልስፍናቸው ምን እንደሚመስል እንድንገነዘብ የሚያስችሉን መሆኑን የሚያመለክት ነው።

## 2.1.1 የቁሳዊ ባህል ምንነት

ስለ ቁሳዊ ባህል ምንነት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸዉን ብያኔ ሰጥተዋል ። ሀብታሙ (2001,13) Glassie ጠቅሶ እንዳመለከተዉ ጽንሰ ሀሳቡን እንዲህ አቅርቧል material culture is the conventional name fore the tangible yield of human conduct … material culture is culture made material , it is the inner wit at work in the

world. Beginning necessarilyl with things but not ending with them the study of material culture uses objects to approach human thought and action ( 1999:41).

ከሀብታሙ ጥቁም ስራ መረዳት እንደሚቻለዉ ጽንሰ ሀሳቡ ተጨባጭ ለሆኑና የሰዉ ልጅ ባህሉን መሰረት አድርጎ የሚያበጃቸዉን ቁሶች የሚመለከት ሲሆን ቁሶቹ የጽንሰ ሀሳቡ መሰረታዊ ጉዳይ ይሁኑ እንጂ በራሳቸዉ ግብ አለመሆናቸዉን ነዉ ። ይህም ጥናቱ ቁሶቹን መሰረት አድርጎ ከቁሶቹ ባሻገር የሚገኘዉን የሰዉ ልጅ አስተሳሰብ እና ግብር ይመረምራል ማለት ነዉ ።

Cleary (2004) የተባለ ምሁር በበኩሉ ጽንሰ ሀሳቡን ሰፊ እና በተለያዩ ምሁራን በተለያየ መልኩ እንደ ተበየነ በመጠቆም ዋናና ቀላሉ መንገድ ጽንሰ ሀሳቡን የሚመለከተዉ ነገሮች ወይም የነገሮች ስብስብ ሆኖ ነገሮቹን እኛ ፈጥረን የሰራናቸዉ እና በእለት ተእለት ኑሯችን የምንገለገልባቸዉ ሆነዉ ፣ቁሶቹም የባህሉ ዉጤት መሆን እንደ ሚገባቸዉ ገልቷዋል፡

> Wood (2007፣14) "Material culture have as their primary concern the mutual relations between people and objects.In particular,studies of material culture are concerned with what uses people put objects to and what objcets do for,and to,people" ይላል።

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው ቁሳዊ ባህል ተቀዳሚው ትኩረቱ በማህበረሰቡና በቁሱ መካከል ያለውን የጋራ ግንኙነት መመርመር ነው። ማህበረሰቦቹ ቁሶቹን ለምን አገልግሎት ያስቀምጡታል? ቁሱ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድነው? የሚሉትን መጠይቆች የሚመረምር መሆኑ ነው።ቁሳዊ ባህል በቁሶቹና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው።

ይህ ደግሞ ቁሶቹ የማህበረሰቡን ምን የህይወት ዘይቤ ያሳያሉ? ቁሶቹ የበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍሎች ለቁሱ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ቁሶቹን የሚጠቀምባቸው ከምን አስተሳሰብ የመነጨ ነው? ቁሶቹ ከሚሰጡት ግልጋሎት ባሻገር ምን የሚያመለክቱት ነገር አለ? ቁሶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ምን ትዕምርትን ይወክላሉ? ቁሶቹ የያዙትን ቅርፅ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? የሚለትን መጠይቆች እንድናነሳ ያስችለናል።

የመጠይቆቹን ምላሽ ስንመረምር ደግሞ ቁሶቹ የበቀለበትን የማህበረሰብ ክፍል አመጋገብን፣መልካምድራዊ ገፅታውን፣እምነታቸውን፣አስተሳሰባቸውን እና መሰል ጉዳዮችን እንድን ገነዘብ መንገድ ያመቻችልናል ፡፡

የቁሳዊ ባህል ምንነትን አስመልክቶ የፎክሎርና የስነሰብእ ሊቃውንት የተለያየ አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ የፎክሎር ሊቃውንት ቁሳዊ ባህል የሚባለው የቁሶቹን ጥርቅም ብቻ ሳይሆን በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን አስተሳሰብና ማንነት የሚጠናበት ነው ይላሉ፡፡ የዚህ ሃሳብ አቀንቃኝ ሊቃውንት ያቀረቡት ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

Prown (1982፣1 ) «Material culture is study of through artifacts of the beliefs, values,ideas,attitudes and assumption of a particular community or society at a given time.» ይላል፡፡ ቁሳዊ ባህል የትኩረት አቅጣጫው በቁሶቹ አማካኝነት ቁሶቹ ስለበቀሉበት የማህበረሰብ ክፍል እምነት፣አስተሳሰብ፣እሴት፣አመለካከትና መላምታቸውን የሚመረመርበት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

## 2.1.2 ቁሳዊ ባህል የመጠናት ፋይዳ

የሰው ልጅ የህይወት ውጣ ውረደን ለመግፋት የሚያስችል ቁሶችን ሲሰሩ ብዙ ዘመናትን አስቆጥረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የለሊሳ ቡላ ማህበረሰብ ዘመናዊ ቁሶች ቢበዙም ባለሙያዎቹ ግን ቁሶቹን መስራት አላቋረጡም፡፡ በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ለመከወኛነት ከማገልገላቸውም በላይ የዘመን ጥበብ አሻራ ያደረባቸው ናቸው፡፡ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶች የማህበረሰብ ባህል፣ፍልስፍና እና እሴትን በመግለጽ በኩል አበርክቶ ስላላቸው ቢጠኑ ጥሩ ነው፡፡የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነት በተመለከተ Prown እና Mayo እንደ ሚከተለው ገልፀውታል፡፡

Prown [1982፣3] «Inherent and Attached value. The most obvious cultural belief associated with material objects has to do with value.»ይላል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ ቁሶች ከእለት ተዕለት ግልጋሎታቸዉ ባሻገር የተለያየ እሴት የሚገለጽባቸዉ መሆናቸዉን የሚስገነዝብ ሲሆን ቁሶቹ ከታለመለት አገልግሎት ባሻገር የተለየ እሴት የሚገለፅባቸው መሆናቸዉን ነዉ ፡፡ እሴቶቹም ተፈጥሯዊ ወይም ሰዎች የሚያበጁቸዉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በማስከተልም Prown ‹‹Surviving Historical events. Objects created in

the past are the only Historical occurrences that continue to exist in the present.›› የሚለውን ሃሳብ አቅርቧል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ሃሳብ ቁሶች ስላልኖርንበት ዘመን የተከናወነን ድርጊት ታሪክን እየነቀሱ በውል እንድንገነዘብ የሚያስችሉ እና የሚጠቁሙ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

‹‹More Representative. They offer the possibility of a way to understand the mind of the greatmajority of non literate people,past and present,Who remain otherwise in accessible exceptthrough impersonal records and the distorting vieብw of a contemporary literary elite.›› Prown [1982 3]ቁሳዊ ባህል የተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ይሁኑ ያልተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በቁሶቹ አማካኝነት አስተሳሰባቸውን ፣ባህላቸውን፣ እምነታቸውን እንዲሁም ማህበራዊ ደረጃቸውን የሚገልፁበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

## 2.1.3 የቁሳዊ ባህል ትንታኔ

Fleming /ውስተ ኢንተርኔት 156–161/ እንደሚለዉ ቁሳዊ ባህል በሚከተሉት መንገዶች ከፋፍሎ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁሟል፡፡ እነሱም፡-የቁሱን ታሪክ /history/፣ ቁሱ /material/ የአሰራር ስልቱ /construction/፣ ጌጥ/ design / እና አገልግሎት/ function/ ናቸው፡፡ Fleming ከላይ የጠቀሳቸውን በማሻሻል በሚከተለዉ መልኩ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ Cultural analysis can carry artifact study beyond description toward explanation by ‹‹the explication of those critical links that exist between human behavior and its material products.›› ይላል፡፡ ይህ የቁሳዊ ባህል ሂደት ከመለየት እና ግምገማ ቀጥሎ የሚመጣ ነው፡፡የቁሱ ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል ቁሶቹን ከየትኞቹ የባህል ዘውግ ጋር አጣጥሞ ጥቅም ላይ እንደ ሚያውላቸው የሚተነተንበት ነው፡፡ የቁሱ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን የሚጠቀሙት ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ነው? ቁሶቹ የማህበረሰቡን ባህል በምን መልኩ ይገልፁታል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስለል ? ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ባህል አንፃር ምን ፋይዳ አላቸው? ቁሶቹ ለየትኞቹ የማህበረሰብ ክፍሎች ተምሳሌት ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመርመር ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መገንዘብ ያስችላል፡፡

> “One important form of cultural analysis deals with the functions performed by the artifact in its culture.unlike the other artifact properties

of material, construction, and design, function involves both the concrete and the abstract aspects of the artifact, the reasons for its initial manufacture, its various intended uses, and its unintended roles.”ይላል። Fleming /ውስተ ኢንተርኔት 156–161/

ከላይ የቀረበው ሃሳብ የሚያስረዳው ባህላዊ ትንታኔ ሁለት አይነት መሆናቸውን ነው።እነሱም፡- አንደኛው የቁሱ ተግባራዊነት በራሱ ውስጥ መሆኑን የሚቃኝ ነው። ቁሶቹ ከተቀዳሚው ተግባራቸው ባሻገር ምን ትዕምርት አላቸው? ከቁሶቹ አገልግሎት ውስጥ ተሸልቅቆ የሚወጣው እሳቤ ምንድነው? ቁሶቹ አሁን የሚሰጡትን አገልግሎት እንዴት ሊሰጡ ቻሉ? የሚሉት መጠይቆች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ነው።ሌላኛው ደግሞ የቁሶቹን አሰራርና ጌጣጌጥ የሚቃኝ ነው።

የቁሱን አገልግሎት ስንቃኝ የሚታየውና የማይታየው ክፍል በጥምረታ መመርመር እንደሚገባ የሚገልፅ ነው። የቁሶቹ አሰራር ከምን አስተሳሰብ የመነጩ ናቸው? በቁሶቹ ላይ ያለው ጌጥ የማህበረሰቡን የህይወት ዘይቤ በምን መልኩ ያሳያል? ባለሙያዎቹ ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድነው? ቁሶቹ በተጠቃሚዎች እይታ አስደሳች ከመሆናቸው ባሻገር ከጀርባቸው ምን እሳቤ አለ? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመርመር የቁሱን ተቀዳሚ ተግባር እና ከታለመለት አገልግሎት ባሻገር ያለውን ሚና እንድንገነዘብ ያስችለናል።

### 2.1.4 የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ስልቶች

Schlereth ውስተ ኢንተርኔት (,2017 7-8) ስለቁሳዊ ባህል ጥናት ይጠቅማል ያላቸውን የተለያዩ የመተንተኛ ስልቶችን ዘርዝሯል። ስልቶቹን በተናጠል ከማስቀመጥ ይልቅ በቡድን መቀመጡ ተመራጭ መሆኑን ጠቁመዋል ። አጥኝዋ ስልቶቹን እንደ አስፈላጊነታቸዉ አስቀምጣለች።

### 2.1.4.1 ትዕምርታዊነቱ

“The role held by an object in society”. ቁሶች ከዘዉትራዊ ጥቅማቸዉ ባሻገር የማንነት መገለጫ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንዴ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ሀብታምነትን እና ባለሞያነትን የሚገልፁበት ሁኔታ አለ፡፡ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ከቁሶቹ ግልጋሎት ጀርባ ያለውን ጥበብ ለይቶ መመርመር እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ቁሶቹ የያዙት ቅርፅ ትዕምርቱ ምንድነው? ቁሶቹ ምን የህይወት ፍልስፍና ያሳያሉ? የሚለትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ነው፡፡

### 2.1.4.2 ባህላዊነቱ

“The development of characteristics of an object which can be related to particular cultures”. በቁሶቹና በማህበረሰቡ ባህል መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚመረምር ሲሆን የሚከተለትን ጥያቄዎች ያነሳል፡፡ ቁሶቹ የየትኛውን የማህበረሰብ ክፍል ባህል ይገልጻሉ? ቁሶቹ የአንድን ማህበረሰብ የትኛውን የባህል አይነት ይወክላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመርመር የሚያስችል የስልት አይነት ነው፡፡

አንድ ሰዉ የሌላን ባህል ቁሳችን ሲፈክር ሙሉ በሙሉ የራሱን የቀድሞ ባህል ለመርሳት ቢቸገርም በተቻለ መጠን ግን ተጨባጭ የሆነ ትንታኔ ለመስጠት መጣር እንደ ሚገባዉ Prown ይመክራል ፡፡ በተለይ ቁሱን ለመፈከር ስንነሳ ቁሱን የሰራዉ ማህበረሰብ ምን እምነት ፣አመለካከት፣ ባህል ፣አቋም ወይም አተያይ ነበረዉ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ቁሱ ስለተሸከመዉ ባህላዊ እሴት እና ታሪካዊ እዉነታዎች ሁሉ መመርመር እንደ ሚገባ Prown፡፡( 1982፣5) አጽንኦት ሰቶ ይመክራል ፡፡

እንደ Prown አባባል ባህላዊ ጥናቶች (cultural studies) ዉስጥ አስቸጋሪዉ ነገር ባህላዊ አቋም (cultural stance ) ወይም ባህላዊ አተያይን (cultural perspective ን) ማወቅ ወይም መለየት ነዉ ፡፡ (1982 ፣ 4 )፡፡ ይህ ማለት ቁሶቹን መሰረት አድርገን ቁሶችን ስለሰሯቸዉ ማህበረሰቦች ለመፈከር ስንሞክር በራሳችን ባህል ፣እምነት ፣አመለከት ፣ማህበራዊ ቡድን ፣መደብ ፣ፖለቲካ ፣ የስራ ዘርፍ ፣ እድሜ ፣ብሄር፣ወዘተ. ማሰባችን ስለ ማይቀር ወደ ራስ ባህል ማድላት (cultural bias ) ይፈጠራል ፣ በዚህም መረጃዉ ይዛባል (distorted ይሆናል) በማለት ይገልጻል ፡፡

### 2.1.4.3 ታሪካዊ ጥበብ አመልካች

“Evaluation of art by material cultural means”. እነዚህ የስልት አይነቶች ባህላዊ ቁሶችን ስናጠና የእለት ከእለት ግልጋሎታቸዉ ላይ ማተኮር ሳይሆን በቁሶቹ ላይ ያለዉን ጥበባዊ ውበት የምናመለክትበት ነው ። ውበታዊ ዋጋቸው ጎልቶ እንዲወጣ የቁሶቹን ቀለም፣ ቅርፅ፣ጥንካሬና ስስነት በአግባቡ በመግለፅ ታሪካዊ ጥበብ አመልካችነታቸውን በግልጽ ማስቀመጥ ይገባል።

### 2.1.4.4 አካባቢያዊነት

“The role of the physical environment on object”. የአንድ አካባቢ ምልክአ ምድራዊ ገፅታና ማህበረሰቡ በቁሱ ላይ በጎና መጥፎ ነገር የሚፈጥርበት ሁኔታ አለ ? ቁሱ የተሰራበትን አካባቢ የሚያመለክትበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚቃኝበት ስልት ነው።

### 2.1.4.5 አገልግሎቱ

“The way an object is used”.ቁሶቹ ምን ምን ተግባራትን ለመከወኛነት ይውላሉ? ቁሶቹ በምን መልኩ አገልግሎት ይሰጣሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ይገለገሉባቸዋል? የቁሶቹ አገልግሎት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና በምን መልኩ ያሳያሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን እያነሳን እንድን መረምር የሚያስችል ስልት ነው።

### 2.1.4.6 መዋቅራዊነቱ

“How an object was physically made”. ቁሶቹ የቁስነት ደረጃ የሚይዙበትን ውቅር የሚያሳይ ነው። ቁሶቹ ከምን ከምን ጥሬ እቃዎች ተሰሩ? ቁሶቹን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉ ንጥረ ቁሶች ምን ምን ናቸው? የአሰራር ሂደቱ እንዴት ነው? የሚለትን ጥያቄዎች በማንሳት ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የስልት አይነት ነው።

### 2.1.4.7 ባህርይ ጠቋሚነት

“The interaction of object and behavior patterns of society”.ማህበረሰቡ ቁሱን በምን መልኩ ይረዳዋል? በቁሱና በማህበረሰቡ መካከል ምን አይነት ግንኙነት አለ? የቁሱ አገልግሎት

በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ተፅኖ አሳደረ? ቁሶቹ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ የለወጡበት ሁኔታ አለ ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የሚያስችል የተወሳሰበ ስልት ነው፡፡

### 2.1.4.8 ማህበራዊነቱ

"The interaction of object and society which form /reflects common view point/ character".ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ትስስርና ቁርኝት የሚቃኝ ነው፡፡ ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ገፅታ በምን መልኩ ያሳያሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ቁሶቹን ከምን አስተሳሰብ በመነሳት ይገለገሉባቸዋል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያላቸው እይታ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመረመርበት ነው፡፡

### 2.1.4.9 የማህበረሰብ ታሪክ ገላጭነት

"The story of the object or its provenance".ቁሶቹ የማህበረሰቡን ታሪክ በምን መልኩ ይገልፁታል? ቁሶቹን ማን አበጃቸው? ከየትኛው የማህበረሰብ ክፍል ተገኙ? በየትኛው ዘመን ፈለቁ? ለሚለት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የስልት አይነት ነው፡፡

## 2.1.5 ቁሳዊ ባህል እና ምደባ

ምደባ በቁሳዊ ባህል ጥናት ዉስጥ የሚጠናዉን ቁስ በቀላሉ ለመለየት እና ትንተናችንን ቀና ለማድረግ እንደሚጠቅም Marchese ያብራራል ፡፡ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ቁሶችን በየፈርጃቸው ማደራጀት ጠቀሜታ አለው፡፡ የቁሶቹ ምደባ አስፈላጊነት ስለቁሶቹ በጥልቀትና ባልተወሳሰበ መልኩ ለመመርመር የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በቁሳዊ ባህል ጥናት ስር ሊጠኑ የምችሉ ቁሶች በርካታ በመሆናቸዉ የተነሳ ስርአት ያለዉ ምደባ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል Prown (1982፣15)ይሁን እንጂ ምደባዉን በቀላሉ ማበጀት አስቸጋሪ መሆኑን አያይዞ ገልጿል፡፡

ምደባውን ለመከወን መሰናክል እንዲኖር ያደረጉት የሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጿል፡፡ እነሱም፡-ቁሶቹ በአይነትም ሆነ በቁጥር በርካታ መሆናቸው ፣ ቁሳዊ ባህልን ለመመደብ የሚያስችል ምልዑነትን የተጎናፀፈ እና አንድ ወጥ መስፈርት አለመኖሩን ጠቅሷል፡፡ ለቁሳዊ ባህል ምደባ እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶችን ያንሳ እንጂ ይበጃል ያላቸውን የቁሳዊ ባህል መመደቢያ መስፈርቶች ሳይገልጽ አላለፈም፡፡ መስፈርቶቹም፡-ቁሱ ከሚሰራበት ንጥረ ቁስ ፣ከአሰራር ጥበብና አገልግሎት አንፃር በመመደብ ማጥናት እንደሚቻል ጠቁሟል ፡፡ የገለፃቸው

መስፈርቶች ግን ምልዑነትን የተካኑ አለመሆናቸውን ገልፆ ቁሳዊ ባህልን ለመመደብ አገልግሎት የተሻለ መሆኑን አመልክቷል፡፡

አገልግሎትን የተሻለ መስፈርት በማለት መግለጹ ቁሶቹ ከተሰሩበት ንጥረ ቁስና የአሰራር ጥበባቸውን መስፈርት አድርጎ ከመጠቀም ይሻላል ማለቱ መሆኑን ከገለጸው መረዳት ይቻላል፡፡

Marchese(1984፣16)፡፡ የተባለ ምሁር በርካታ ነገሮች (things) የእጅስራ ዉጤቶች (artifacts) ተብለዉ ስለሚጠሩ ትንተና ለመስጠት ፣ ለመሰብሰብ እና ለህትመት ለማብቀት ሲባል ምደባ አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም ቁሶች በአይነት (type)መመደብ ይገባቸዋል ይላል ፡፡

አይነት ደግሞ “አገልግሎታዊ አይነት” functinonal type (1984፣23 )፡፡ እና “ትንተናዊ አይነት” (analytical type)በማለት በሁለት ጎራ በመመደብ ስለ ምድቦቹ ምንነት ለማብራራት ሞክሯል አያይዞም ምደባችን ለአጠናናችን እና ለትንታኔያችን አጋዠ እስከ ሆነ ድረስ በምድባችን በቀላሉ ረክተን መቆም እንደ ማይገባን እና በተቻለ መጠን እስከ መጨረሻዉ ቅንጣት ምደባ ድረስ መሄድ እንደሚገባ ይመክራል ፡፡

Beals and Harry (1958፣238) አንድ ቁስ ዘርፈ ብዙ ግልጋሎት “multi functional objects”እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሃሳብ አንድ ቁስ በአንድ ተግባር ላይ ብቻ አለመወሰኑን የሚያሳይ ነው፡፡ አንድ ቁስ በአንድ ተግባር ላይ ብቻ ከመወሰን ይልቅ የተለያዩ ተግባራትን ለመከወኛነት የሚያስችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ለምሳሌ የሸክላ ቁስ የሆነው ወጪት/ጣባት ተቀዳሚው ተግባር ለክትፎ ፣ ለአይብ ፣ለጎመን ፣ ለተለያዩ ወጣ ወጥ ማዉጫነት ነው ፡፡ ይህ ወጪት ከወጣወጥ ማቅረብያነት ውጪ ቤት ውስጥ በመስቀል /በማንጠልጠል/ ለጌጥ የሚዉልበት አጋጣሚ ስላለዉ ነው፡፡

የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ያስቀመጡትን መስፈርቶችን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በዚህ ጥናት ዉስጥ ቁሶችን ለመመደብ እና ለመተንተን ተገልግላበታለች፡፡

## 2.1.6 የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

ፈቃደ dorsonን ጠቅሶ ቁሳዊ ባህል ከአራቱ የፎክሎር ዘዉጎች አንዱ እንደ ሆነ እና በስሩ የሚካተቱ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ/ folk craft/ ሀገረሰባዊ ስንክን/folk art/ ሀገረሰባዊ ምህንድስና /folk architecture/ ሀገረሰባዊ ልብስ /folk costume/ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር /folk cookery/ እንደሚያቅፍ አስቀምጠዋል ፡፡በቁሳዊ ባህል ስር ሊጠኑ የሚችሉ እነዚህ ዘርፎች

ቢኖሩም  የዚህ ጥናት ትኩረት በቁሳዊ ባህል ስር ከሚጠኑት መካከል ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ርዕስ ጉዳዩ እንደሚከተለዉ  ተብራርቷል፡፡

## 2.1.7 ሀገረሰባዊ እጅ ስራ

ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ሰዎች በእለት ተእለት ተግባራቸዉ የሚገለገሉባቸዉን ቁሶች አካባቢያዊ እና ባህላዊ የሆነን እዉቀታቸዉን ተጠቅመዉ በእጃቸዉ የሚያበጇቸዉን ቁሶች የሚመለከት የቁሳዊ ባህል አንድ ዘርፍ ነዉ ፡፡ ሀገረሰባዊ እጅስራ በአጭሩ ባህላዊ የሚለው ሀገር በቀልነትን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ  በአጭሩ ባህላዊ  እጅ ስራ (traditional craft) ሲሆን ሙያዉም ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ ሆኖ በተለይም በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ በልጅነት ጊዜ በምልከታ፣ በመኮረጅ እና ደጋግሞ በመስራት የሚካኑት ጥበብ መሆኑን (Roberts  ወስተ dorson 1972 ፣233 እና bornner ዉስተ Oring 1986 ፣ 199)ገል ጿል፡፡ አጥኚዋ ያገኘችዉን መረጃ መሰረት በማድረግ ሸክላ ስራ እንዴት እና መቼ እንደተጀመረ እንዲሁም እንደተስፋፋ በኢትዮጵያ የሚሉ አጫጭር ንኡስ ርእሶችን በመስጠት ለመዳሰስ ትሞክራለች ፡፡

## 2.1.8 የሸክላስራ ታርክ በአለም

“አንድ ነገር መቼ ተጀመረ ?እንዴት ተጀመረ ? እነማን ጀመሩት ? ወዘተ.“ የማሳሰሉ ጥያቄዎችን አንስቶ እንቅጩን ምላሽ ማቅረብ በብዙ የጥናት መስኮች አስቸጋሪ ጉዳይ ነዉ፡፡ በተለይ በጥንት ጊዜ የተፈጸሙ ወይም የተከናወኑ ጉዳዮችን ምንጭ ለመጠቆም በሚደረግ እንቅስቃሴ አንድ ወጥ እና ተመሳሳይ ምለሻ ማግኘት አይቻልም ፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ነገር መነሻዉ ወይም ምንጩ መቶ በመቶ እርግጠኛ ባይሆንም እንኳ ተቀባይነት ያላቸዉ መላምቶች መሰንዘራቸዉ ግድ ነዉ ፡፡

በመሆኑም የሸክላ ስራ  አጀማመር ጋር ተያይዞ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ሀሳቦችን አቅርበዋል ፡፡ የቀረቡት ሀሳቦች የተለያዩ ቢሆኑም አንድ የሚያደርጋቸዉ ጉዳይ ሙያዉ ወይም ጥበቡ እጅግ በጣም ረጅም ዘመን ያስቆጠረ መሆኑን መግለጻቸዉ ነዉ ፡፡

Copper የተባለ ምሁር  የሸክላ ስራ  የተጀመረዉ ከእሳት መገኘት ጋር ተያይዞ እጅግ በጣም ሩቅ በሆነ የቅድመ ታሪክ ዘመን (pre-historic  times) በአዲሱ የድንጋይ ዘመን አካባቢ (New stone Age ) በኢንድስ ሸለቆ እና በሜሶፓታሚያ ግዛት መሆኑን በመግለጽ የመጀመርያዎቹ የሸክላ ዉጤቶች ለአምልኮ ማስፈጸምያ (ማምለኪያ )ማገለላቸዉን ጠቁሟል (1981፣ 13)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Noble የተባለ ምሁር በበኩሉ የሸክላ ስራ ጥበብ የተጀመረዉ በ7000 B.C.አከባቢ በድንጋይ ዘመን (Neolithic period) የሰዉ ልጅ በእሳት መጠቀም በጀመረበት ጊዜ መሆኑ በመጠቆም ግኝቱም ድንገተኛ እንደ ነበረ ገልጿል ፡፡(1966 ፣10) ፡፡Fagg እና picton በበኩላቸዉ የሸክላ ስራ ጥበብ የተጀመረዉ በመካከለኛዉ ምስራቅ ጀሪቾ በተባለ የፍልስጤም ግዛት በ6000 B.C አካባቢ ሆኖ ወድያዉ ወደ ሰሜን አፍሪካ እንደተሰራጨ ገልጿል (1970፣7)፡፡በሌላ በኩል የሸክላ ስራ እንቅስቃሴ የተጀመረበትን ጊዜ እንቅጩን ከመንገር ይልቅ ጥንታዊነቱን ብቻ በማስቀደም ስራቸዉን ያቀረቡ ምሁራን በርካታ ናቸዉ ፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ Chattopadhyay አንዱ ሲሆን ጥበቡ ጥንት እንደተጀመረ ፣ የሰዉ የመጀመርያ የእጅስራ ዉጤት እና የስልጣኔ መገለጫ ትምርት መሆኑን እንዲሁም የሸክላ መስርያ ማሽን (machine) ሳይሆን አይቀርም በማለት ገልጿል (1975፣3)፡፡

Trevor የተባለ ምሁር በበኩሉ የሸክላ ስራ ከእጅስራ ዉጤቶች ሁሉ ቀዳሚ እንደሆነና ከብዙ ሺህ አመታት በፊት በናይል ወንዝ ዳርቻ በሚኖሩ ግብጻዉያን ሲተገበር እንደነበረ በመጠቆም ሙያ ረጅም እድሜ ያስቆጠረዉ ቀላልና አገልግሎት የሚሰጥ እጅስራ (simple and uncional craft) በመሆኑ ነዉ፡፡ በማለት ገልጿል (1966፣4)፡፡

Bricks በበኩሉ "Since clay is an an abundant natural material, it is not surprising that its history as acreative medium shouid be as long as the history of art itself "(1967፣9 ).በማለት የሸክላ አፈር በቀላሉ በብዛት የሚገኝ የተፈጥሮ ቁስ በመሆኑ ሙያዉ ከጥበቦች ሁሉ የቀደመ ታሪክ ያለዉ ፣ በሁሉም የአለም ክፍሎች የሚገኝ ፣ የአሰራር ቴክኒክኩ ቀላል እና አለማቀፋዊ ይዘት ያለዉ መሆኑን ጠቁሟል ፡፡

ብዙዎቹ የመስኩ ሙሁራን እንደጠቆሙት የሸክላ አፈር ጥሩ የሸክላ ዉጤቶችን ለመስራት እንደ ሚያስችል ፣ባለሙያዎ ጥራት ያለዉ የሸክላ ለማግኘት እረጅም መንገድ እንደሚጓዙ እንዲሁም በሸክላ ስራ ሂደት ቅርጽ ማዉጣት (forming) ፣ማስጌጥ (decorating)እና ማቃጠል (firing) የሚሉ ዋና ዋና ሂደቶች እንደሚከወኑ Noble (1996፣15 )፣Bricks (1967,12) Copper (1981,25) ገልጿል

### 2.1.9 የሸክላስራ ታርክ በአፍሪካ

በአፍሪካ የሸክላስራ አጀማመር በተመለከተ ያለዉ እዉነታ ከአለም የሸክላ ስራ አጀማመር ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ልዩነቱ ስለ አለም የሸክላ ስራ አጀማመር ያለዉ መረጃ በርካታ ሲሆን ስለ

አፍሪካ ያለዉ መረጃ ግን ዉስን ነዉ ፡፡ ስለ አፍሪካ የሸክላ ስራ አጀማመር እና በአጠቃላይ እንቅስቃሴ የገኘኒቻ መረጃዎች ዉስን ቢሆኑም ስለ አጠቃላዩ የአፍሪካ ሸክላ ስራ ሁኔታ የመግለጽ ወይም የማሳየት ብቃትታቸዉ ግን ከፍ ያለ ነዉ ፡፡ በማለት ከባለሙያዎቹ ዉጭ ያለዉ ማህበረሰብ እንደሚፈራራቸዉ እና እንደ ሚያገላቸዉ Frank (2004፣59) ገልጿል፡

## 2.1.10 የሸክላ ስራ ታሪክ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የሸክላ ስራ ታሪክ ረጅም እድሜ ያለዉ ሲሆን እንደሌሎቹ የእጅስራ ዉጤቶች ለህብረተሰቡ የእለት ተእለት ፍላጎት ከፍተኛ ሚና የነበረዉ መሆኑን Pankhurst (1964፣221-222 እና 1992፣251 ) ገልጸዋል ፡፡ በኢትዮጵያ የእጅስራ (handicrafts ) ዉጤቶች ረጅም ታሪክ እና ጉልህ ስፍራ አላቸዉ ፡፡ በሀገራችን ከጥንት  እስከ ዛሬ አብዛኛዉ የህብረተሰብ ክፍል የሚገለገልባቸዉ በርካታ ቁጥር ያላቸዉ የእጅ ስራ ዉጤቶች ያሉ ሲሆን መሰሪያ ንጥረ ቁሶችም በአከባቢዉ በቀላሉ የሚገኙ ፣የእጅ ስራ ዉጤቶቹ በባህላዊ መንገድ የሚሰሩና ከባለቤት ማህበረሰቦቹ  (ከፈጣሪዎቻቸዉ ) ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

Ethiopian Tourist Organization (1971፣1) በኢትዮጵያ የእጅስራ ዉጤቶች ከምን ከምን ንጥረ ቁሶች እንደሚሰሩ የሚከተለዉን ሀሳብ አቅርበዋል ፡፡

“ከሸክላ እና ከቀንድ ለመጠጫነት ፣ከትላልቅ ግንድ የተለያዩ የእንጨት ዉጤቶች ፣ከእንስሳት ቆዳዎች ልብሶች እና ብራናዎች ፣ከተለያዩ  የሳር ዘሮችና ቀርቅሀዎች ቅርጫቶች እንዲሁም ከቆዳ ፣ ከቀንድና ከብረታብረት የጦር መሳሪያዎችና የእርሻ መገልገያዎች ይሰራሉ” ፡፡

ይሁን እንጂ ከአከባቢያችን በተፈጥሮ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የሚሰራዉ ፣ረዥም ዘመን ያስቆጠረዉ እና ከማህበረሰቡ የእለት ትእለት ህይወት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለዉ የእጅስራ በበርካታ ምሁራን ጽሁፎች ዉስጥ ቦታ ተሰጥቶት አለመጠናቱን (silverman) እንዲህ ይገልጸዋል ፡፡”Yet, most books that have been written about Ethoipian material culture deal only with the painting associated with the Ethoipian orthodox church ‘’ (1999;3 )

በመሆኑም ስለ ኢትዮጵያ የእጅስራ ዉጤቶች እንቅስቃሴ በተለይም ስለ ሸክላ ስራ ታሪካዊ አጀማመር ያለን መረጃ አነስተኛ ነዉ ፡፡ የመረጃ እጥረት እንዲ ገጥመን አስተዋጽኦ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ለሙያዉ እና ለሙያተኞቹ የነበረዉ ዝቅተኛና የተሳሳተ አመለካከት ትልቁን ድርሻ ይወስዳል ፡፡ በተለይም ቀደም ባሉት ዘመናት በነበሩ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት የተነሳ የእጅስራ ሙያተኞችን በይፋ የሚያንቋሽሹ እና የሚአዋርዱ አባባሎች ይንጸባረቁ ነበር ፡፡በዚህ

የተነሳ  በሀገራችን ረጅም እደሜ ያለዉ መሆኑ የሚነገርለት የሽክላ ስራም ሆነ አጠቃላይ የእጅስራ ጥበብ መሻሻል ሳይታይበት ለዘመናት ዘልቋል ። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ "ባህል እና ህብረተሰብ " በሚለዉ አምዱ በፌዉዳሉ ስራተ ማህበር ወቅት በእጅ ስራ ሰራተኞቹ ይደርስ የነበረዉን ተጽእኖ እና የዘርፉን አለመሻሻል በሚከተለዉ መልኩ ገልጿል ።

> የእደጥበብ ሙያተኛን ለመጣል ሸክላ ሰራተኛዉን "ቡዳ"፣አንጥረኛዉን "ጠይብ"፣ቆዳ ሰራተኛዉን "ፋቂ"፣ሠማ ሰሪዉን "ቁጢት በጣሽ" በማለት ተገቢ ያልሆኑ አነጋገሮች እና ኢ- ሳይንሳዊ አባባሎች ተለምደዉ ነበር። በታሪክ ቅርስ ምርምር እንደሚታወቀዉ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሸክላ ስራ የሶስት ሺህ አመት እድሜ እንዳለዉ ይነገራል። አሰራሩም ከትዉልድ ትዉልድ ሲወርድ የቆየ ከመሆኑም በላይ በሙያዉ የተሰማሩት ጠቢቦች የተሻሻለ ምርት ለማዉጣት እንዳይችሉ ትምህርቱም ሆነ እርዳታዉ ተነፍጓቸዉ ቆይቷል(1971፣ነሀሴ 19፣8)።

በተመሳሳይ መልኩ Hecht (1968፣8) Cassiers (1971 ፣46 ) እንደ ገለጹት ከሆነ የሸክላ ስራ በኢትዮያ ዉስጥ ረጂም እድሜ ያስቆጠረ ፣ ከሌሎች የእጅስራ ሙያዎች የበለጠ ጠቃሚ የሆነ ፣በአብዛኛዉ በሴቶች የሚተገበር ፣የሸክላ የሸክላ ዉጤቶቹ ለቤት ዉስጥ መገልገያነት (utilitarian) የሚዉሉ እንጂ እንደሌሎች ሀገሮች ወደ ጥበብነት (an art ) ያላደጉ መሆናቸዉን እንዲሁም ባለሙያዎቹ ለዘመናት ዝቅተኛ ቦታ /ደረጃ (lower classes ) የተሰጣቸዉ መሆናቸዉን ጠቁመዋል

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በኢትዮጵያ ዉስጥ ከጥንት ጀምሮ የእጅስራ ባለሙያዎችን በተለይ የብረታብረት እና ሸክላ ሰራተኞችን ማግለል እና ዝቅ አድርጎ መመልከት የተለመደ ነዉ ።ባለሙያዎቹ ለብዙ ዘመናት የራሳቸዉ የሆነ የእርሻ መሬት ያልነበራቸዉ እና ጋብቻ የሚፈጽሙትም  የራሳቸዉን ሰዉ ፈልገዉ ነበር ።የእጅስራ ባለሙያ ካልሆነ ማህበረሰብ ጋር ጋብቻ አይፈጽሙም ። በዚህም የተነሳ ባለሙያዎቹ በገጠርም ሆነ በከተማ ዳር በሆነ ቦታ ላይ ተሰብስበዉ ይኖራሉ። የእጅስራ ዉጤታቸዉን ለመሸጥ ወደገብያ ሲወጡ እንኳ ምርቶቻቸዉን ይዘዉ የሚቀመጡት በገብያ ጠርዝ ወይም ዳር ቦታ ላይ ሲሆን (ይህንን እኔም በጥናቴ አስተዉያለሁ)። ብዙ ጊዜ የተለየ አደገኛ ሀይል ወይም መንፈስ ባለቤት ተደርገዉ በመቆጠራቸዉ የተነሳ የእጅስራ ባለሙያ ባልሆነዉ ማህበረሰብ ዘንድ "ቡዳ" ፣ "ካላይ"፣"ጠይብ" ወዘተ በመባል የታወቃሉ። የሚሉ  ስሜት የሚጎዱ ስሞች እየተሰጣቸዉ ለከፍተኛ የስነ ልቦና ችግር ይጋልጣሉ።

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Pankhurst (1992)፣ Combes እና Tamisier (1838) የተባሉ የዉጭ አገር ሰዎች ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት አንድ የብረታብረት ሰራተኛ ከሰይጣን መንፈስ (devil spirit ) ጋር ግንኙነትአለዉ በመባሉ መኖርያቀዬዉን በመልቀቅ ለስደት በመዳረጹ ተነሳ የተለያዩ ችግሮችን ተሂዙሮመኖርያ በማጣቱ በመጨረሻ ዋሻ ዉስጥ በመኖር ለልመና መጋለጡን ዋቢ በማድረግ የባለሙያዎቹን ገጠመኝ በሚከተለዉ መልኩ አስፍረዋል ፡፡

”oh, if instead of being ablackmith I had worked the land or adopted the occupation of solider, I would not have had to exile myself. I would still be in my native country,in the midst of a family which loved me: and here I live alone in a cave which wild animals will perhaps one day dispute with me .oh why was Iborn a blcksmith? My skill in that art made my entire life miserable “ (1992 ;263).

ከላይ ከቀረበዉ ሀሳብ የምንረዳዉ ጉዳይ ባለሙያዎቹ ጋር ተያይዞ የሚደርስባቸዉን ኢኮኖሚየ፣ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ችግር ነዉ ፡፡ በኢትዮጵያ የእጅስራ ባለሙያዎች በሙያቸዉ የተነሳ እንደሚገለሉ Silverman እንዲ ገልጸዋል ፡፡ “ Caste groupare are found throughout Ethopia and are associated with the production of certain types ofcertai types of objectes” (1999;14).

እንደ Silverman አባባል ብዙ ጊዜ የእጅስራ ባለሙያዎች የሚገለሉት በተለየ መለኮታዊ ሀይል (special supernatural power ) የተሞሉ እና የተለየ እዉቀት ባለቤት የሆኑት የሆኑት ያላንዳች ነገር አይደለም የሚል እምነት የእጅ ባለሙያ ባልሆኑት ማህበረሰቦች ዘንድ በመታሰቡ ነዉ፡፡ በተለይ አፈርን ወደ ሸክላ እና የተለያዩ ብረቶችን መቀየር በሰዉ ዘንድ የማቻል ጉዳይ ነዉ፡፡ ተብሎ በመታመኑ የተነሳ ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ነገር ቢያበረክቱም ባለሙያዎቹ አደገኞች ፣የበሽታና የሞት መንሴኤዎች ፣ የተፈሩና የማይጠቅሙ ወይም የተናቁ (despised) ተደርገዉ ይቆጠራሉ ፤ለብቻቸዉ ተገልለዉ ይኖራሉ ፤ ከሌሎች ማህበረሰቦች (በአብዛኛዉ ከአርሶአደሩ ) ጋር ጋብቻ አይፈጽ (1999፣14)፡፡

በእትዮጵያ በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከብረታብረትና ሸክላ ሸራተኞች ጋር ተያያዞ የሚነሳዉ ሌላዉ ጉዳይ “ቡዳ” የሚለዉ ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን ጽንሰ ሀሳቡ በማህበረሰቡ ዉስጥ ስር የሰደደ እና ለዘመናት የዘለቀ ነዉ ፡፡ በተለይ ከሁለቱ የሙያ መስኮች ጋር ተያይዞ ቤተእስራኤላ

ዉያን (“ፈላሾች”) አብሮዉ የሚነሱ ሲሆን “ካይላ “ ቡዳ (evil eye ) ወይም “ጠይብ “ እየተባሉ እንደ ሚጠሩ Qurin (1992,13 ) ጠቁሟል፡፡  Qurin አያይዞም “ካይላ “ የሚለዉ ቃል በ17 ኛዉ ክፍለ ዘመን አካባቢ በጽሁፍ ዉስጥ ለመጀመርያ ጊዜ የተገኘ ሲሆን የ “ፈላሻዎችቹ “ መጠርያ ሆኖ እንደ ሚያገለግል እና በታላቋ ጎንደር ቤተእስራኤልላዉያን የሚኖሩበት ቦታ “ካይላ ሜዳ  “ በመባል እንደሚጠራ ገልጿል ፡፡ (1992፣13 )፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Salamon (2004) ቤተእስራኤላዉያኑ ብረታብረትና ሸክላ ሰራተኞች በኢትዮጽያዊዉ ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ መለኮታዊ ሃይል ያለቸዉ ፣ቡዳ ተብሎ እንደ ሚጠሩና ወደ ጅብነት የመቀየር ሃይል ወይም ችሎታ ያላቸዉ መሆኑን የጠቀመዉ በሚከተለዉ መልኩ ነዉ ፡፡

Bete Israel specialization in blacksmithing and pottery making was treated with ambivalence by neighboring groups,who attributed supernatural powers to the Jewish artisans. They were perceived as buda, the my thical Ethiopian Hyena, who possesses the power of transforman in to human during daytime and thus crosses the boundary between human and non human (2004;195).

Stevens (2004) በበኩሉ Evil eye የሚለዉ ጽንሰ ሀሳብ በአፍሪካ ዉስጥ በተለይም በሰሜን አፍሪካ ማህበረሰብ እና ከሳሃራ በስተደቡብ በሚገኙ እንደ ኢትዮጵያ እና ሱዳን ባሉ ሀገሮች በማህበረሰቡ ወስጥ ጎልቶ የሚታይ ክስተት መሆኑን እና ጉዳዩን ትክክል ነዉ ብሎ ማጠቃለል አስቸጋሪ እንደሆነ ጠቁሟል (2004፣121) ፡፡በተጨማሪም በተለይ በአማራ ባህል “ቡዳ” የሚል መጠሪያ መኖሩን በመጠቆም “ቡዳ” የሆነ ሰዉ ወደ ግብነት መቀየር እንደሚችል እንዲሁም ሰዎችን በእይታ እንደሚጎዳ ገልጿል፡፡(2004፣122)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Honea (1957 ) ”ቡዳ“ የሚለዉ ቃል Evil eye የሚለዉን የእንግሊዘኛቃል የሚተካ ሲሆን በዘር የሚወረስበ፣አንድ ሰዉ ”ቡዳ“ መሆን የሚታወቅበት ምልክት አለመኖሩን ገልጿል (1957፣20-21 )፡፡በኢትዮጵያ ዉስጥ የሸክላ ስራ በጠአቃላይም የሀገረሰባዊ እጅስራ ረጅም እድሜ ያስቆጠረና የጎላ ጠቀሜታ ያለዉ ቢሆንም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሰር በሰደዱ የተለያዩ አመለካከቶች የተነሳ ባለሙያዎቹን ተገቢሁን ቦታ ለማግኘት ሳይችሉ ቀርተዋል ፡፡ በእርግጥ ከቅርብ አመታት ወዲህ ባለሙያዎቹን በተመለከተ ይፋዊ በሆነ

መልኩ የማንቋሸሹ ጉዳይ የቀነሰ ቢሆንም ተጨባጭ ለዉጥ መጥቷል ለማለት ግን አያስደፍርም ።

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በቁሳዊ ባህል ስር ሊዳሰስ የሚችለዉን ሀገረ ሰባዊ እጅስራ በተለይ ደግሞ የሸክላ ስራን ሙሉ በሙሉም ይሁን በጨረፍታ ትኩረት ያደረጉ ቀደምት ጥናቶችን ለመፈለግ አጥኚዋ ባደረገችዉ ጥረት መሰረት የተወሰኑ ጥናቶችን ለማየት ችላለች ። ከተጠኝዉ አካባቢ እና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ካላቸዉ ቀረቤታ አንጻር በሚከተለዉ መልኩ ቃኝታቸዋለች።

በዚህ ክፍል ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቅርበት ያላቸዉ እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል እና ከትምህርት ክፍሉ ዉጭ ለአርትስት ማስተርስ ድግሪ ሟሟያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ተካተዋል ።በተጨማሪም ይህ ጥናት ከፎክሎር ዘርፎች አንዱ በሆነዉ በቁሳዊ ባህል ( material culture ) ላይ የሚያጠናን ስለ ቁሳዊ ባህል ፤በቁሳዊ ባህል ስር ስለ ሚካተተዉ ሀገረ ሰባዊ እጅ ስራ (folk craft) እንዲሁም በአገረሰባዊ እጅ ስራ ዉስጥ ስለ ሚካተተዉ ሸክላ ስራ ምንነት እና ተዛማች ጉዳዮች በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን መጻህፍት ከቁሳዊ ባህል ዘርፍ ውስጥ በምን ላይ የተከናወኑ ነበሩ? ምን ፍሬ ሀሳቦችን አነሱ? መቼ ? ፣ የትና በማን ተከናወነ ? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ከዚህ ጥናት ጋር በምን ይዛመደል ? እንዲሁም በምን ይለያል? የሚለው ሌለኛው የቅኝት ክፍሌ ነው።

ሀገረ ሰባዊ እጅስራ በተለይ ደግሞ የሸክላ ስራን ሙሉ በሙሉም ይሁን በጨረፍታ ትኩረት ያደረጉ ቀደምት ጥናቶችን ለመፈለግ አጥኚዋ ባደረገችዉ ጥረት መሰረት የተወሰኑ ጥናቶችን ለማየት ችላለች ። ከተጠኝዉ አካባቢ እና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ካላቸዉ ቀረቤታ አንጻር በሚከተለዉ መልኩ ቃኝታቸዋለች።

ከዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተሻለ ዝምድና ያላቸዉ ጥናታዊ ጽሁፎች በቁጥር ሁለት ናቸዉ።እነዚህ ጥናታዊ ጽሁፎች የ (ሀብታሙ እንግዳዉ 2001 እና ደምስ መሸሻ 2009 ) የሸክላ ስራን ሙሉ በሙሉ የተመለከቱ ሲሆን አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ስር በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ኤም. ኤ

ዲግሪ መራሀ ግብር የቀረቡ እና በቁሳዊ ባህል ስር ሊጠኑ በሚችሉ ዘርፎች ላይ በማትኮር ሸክላ ስራን የተመለከቱ ናቸዉ፡፡

ሀብታሙ እንግዳዉ ( 2001 ዓ.ም ) "በደቡብ ጎንደር አስተዳደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ሻሞ ጉድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሸሞ መድሃኒአለም ሸክላ ስራ ዉጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ "በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበዉ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳዉ የሸክላ ስራ ዉጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ መሰብሰብ ፣መሰነድ ከዚያም ባለፈ ቁሶች ያላቸዉን ባህላዊ እና ማህበራዊ ፋይዳ መርምሮ ማሳየት የሚል እና ከባለሞያዎቹ ህይወት ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ቃል ግጥሞችን ፣ ትረካዎችን እና ምሳሌያዊ ንግግሮችን አካቶ አይቷል፡፡

ስለ ሸክላ ስራ የአሰራር ሂደት እና አገልግሎት በማን ይተገበራል የሚሉ ጉዳይዮችን አንስቶ የሚከተለዉ ማጠቃለያ ላይ ደርሷል፡፡የሸክላ ስራ አሰራር ተመሳሳይነት ያለዉ መሆኑን ቁሶቹ ባህላዊ ‹ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ያላቸዉ መሆናቸዉን እንዲሁም የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከወን ተግባር መሆኑን አብራርቷል፡፡

የኔ ጥናት ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና መመርመር በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋራ የሚመሳሰልበት በርካታ ቁምነገሮች ቢኖሩም ፣ የተጠኚዎች ማህበረሰብ መገኛ አከባቢ እና ከባለሙያዎቹ ህይወት ጋር ተያይዞ የሚነገሩ ቃለ ግጥሞችን ፣ ተረቶችን ፣ እና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ማካተቱ የልዩነት አንኳር ነጥቦች ናቸዉ፡፡

ደምስ መሸሻ (2009 ዓ.ም) "ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የአንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ "በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ባቀረበዉ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳዉ በክስታኔ ማህበረሰብ በሸክላ እና አንጥረኛ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶችን አሰራር እና አገልግለት መተንተን እንዲሁም በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍእና መመርመር ነው፡፡የሸክላ ስራ እና የአጥረኛ ስራ የአሰራር ሂደትና ጥቅም እንዲሁም የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ ምን እንደሚመስል ተመልክቶ ማጠቃለያ ላይ ደርሷል፡፡ ጥናቱ ባተኮረበት ቦታ ላይ ቁሶቹ ተመሳሳይ የአሰራር ሂደትን የሚከተሉ መሆናቸው እንዲሁም ቁሶቹ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ገልዋል፡፡

የሸክላ አሰራርና አገልግሎት እንዲሁም የባለሙያዎቹን ህይወት ፍልስፍና መመርመሩ ያመሳስለናል፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ የአንጥረኛ ስራ አለማካተቱ እንዲሁም በተጠኝዎች መገኛ ቦታ ልዩነት አለን፡፡

አስቴር ሙሉ (2000ዓ.ም)‹‹ባህላዊ ቤቶች እና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት ዋና አላማ አድርጋ የተነሳችው በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ መግለፅ ፣መቅረስ፣መሰነድና የነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ህልውና ፈፅሞ ከመጥፋት ተቆጥቦ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚሰጥበትን መንገድ መጠቆም መሆኑን ገልፃለች፡፡

የጥናቷን ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅማ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ባህላዊ ቤቶቹ ማህበረሰቡ ቅርፁን ተከትሎ በሰጣቸው ስያሜ፣የሸክላ ቁሶቹን ደግሞ በአገልግሎታቸው መድባ በገላጭ ዘዴ ሰፋ ያለ ትንታኔ አቅርባለች፡፡ በጥናቷ የቁሶቹን አገልግሎት እና የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ህይወት መመርመሯ እና የሸክላን ስራ በዋናነት ማንሳቷ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል ፡፡ ይህ ጥናት ባህላዊ የሸክላ ስራፅና የኑሮ ዘይቤ ትንተና ነዉ ፡፡በርእሰ ጉዳይ እና በተጠኚ መገኛ ቦታ እንዲሁም ይህ ጥናት በቁሶቹ አማካኝነት የማህበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ መመርመሩ ሌላው ልዩነታችን ነው፡፡

ደግሰው ጥላሁን (2003ዓ.ም) ‹‹ባህላዊ የሸክላ እና የቆዳ ስራ በቡሬና ወንበርማ ወረዳ›› በሚል ርዕስ ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ባቀረበችው ጥናት ዋና አላማ አድርጋ የተነሳችው 26 ባህላዊ የሸክላና ቆዳ የአሰራር ሂደትና ጥቅም ማሳየትና መቅረስ፣የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ መዳሰስ ነው፡፡ ባለሙያዎቹ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና በሙያቸው ያገኙት እና ያጡትን ጉዳይ መቃኘት ሌላኛው ዓላማ መሆኑን ገልፃለች፡፡የሸክላ እና ቆዳ የአሰራር ሂደት እና ጥቅም እንዲሁም የባለሙያዎቹን የህይወት ልምድ ምን እንደ ሚመስል ተመልክታ የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ደርሳለች፡፡ ጥናቷ ባተኮረበት ቦታ ላይ ቁሶቹ ተመሳሳይ የአሰራር ሂደትን የሚከተሉ መሆናቸውን እንዲሁም ቁሶቹ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን ገልፃለች፡፡

ስለሸክላ አሰራርና አገልግሎት መመርመሯ ያመሳስለናል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የቆዳ ስራ አለመመልከቴ እንዱሁም በተጠኝዎች መገኛ ቦታ ልዩነት አለን፡፡

## 2.3 ጥናቱ የተካሀደበት አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ክፍል የተጠኚዉ ማህበረሰብ መገኛ ቦታ እና ነዋሪ ህዝቡን የሚመለከቱ ጉዳዮች ተዳሰዋል

### 2.3.1 የወረዳዉ ህዝብ ብዛት ቋንቋና ሓይማኖት

እንደ ወረዳዉ ባህልና ቱርዝም ቢሮ ዘገባ የኦሞናዳ ወረዳ ህዝብ  ብዛት 314311 ሲሆን ከዚህ ዉስጥ በለሊሳ ቡላ ቀበሌ የሚገኙ ህዝብ ብዛት 11225 ነዉ፡፡ በዚህ ገጠር ቀበሌ ከሚኖሩ ህዝቦች ዉስጥ 5190 ሚሆኑት ወንዶች ሲሆኑ 6035 የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸዉ፡፡ የወረዳዉ ዋና ከተማ የሆነችዉ ናዳ ከተማ የሚኖሩ ህዝብ ብዛት 16764 ያህል ሲሆን ከዚህ አሃዝ ዉስጥ 8035 ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ 8729 ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸዉ፡፡

የኦሞ ናዳ ወረዳ በአብዛኛዉ የኦሮሞ ህዝብ የሚኖርበት ቢሆንም አልፎ አልፎ የአማራ፣የየም ፤ የስልጤ፣ ጉራጌ እና በትንሹ ትግሬ ፣ኩሎና ከፋ ይገኙበታል ፡፡የወረዳዉ ህዝብ የኦሮሚኛን ቋንቋ በዋናነት የሚናገር ቢሆንም አማሪኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ይጠቀሙታል ፡፡ ህዝቡ በብዛት የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ቢሆንም የኦርቶዶክስ እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮችም ይገኛሉ፡፡

### 2.3.2 የወረዳዉ ህዝብ መተዳደርያና መሰረተ ልማት

የኦሞ ናዳ ወረዳ ህዝብ እንደማንኛዉም የኢትዮጵያ ገጠር ወረዳዎች ሁሉ ዋነኛ መተዳደርያዉ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ  ሲሆን በወረዳዉ የተለያዩ የብር ፣የአገዳ ፣ የሰብል ፣የፍራፍሬና የአታክልት ዘሮች (አይነቶች )ይመረታሉ፡፡ ይሁን እንጂ ወረዳዉ በዋናነት የሚታወቀዉ በቦቆሎ፣ ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ ገብስ  እና ስንዴ ምርቱ ነዉ፡፡ (ከኦሞ ናዳ ግብርና ቢሮ)

በወረዳ ዉስጥ ከአምስት በላይ ለመስኖ ልማት የሚዉሉ አነስተኛና ከፍተኛ አቅም ያላቸዉ ወንዞች አሉ፡፡ የወረዳዉ የተወሰኑ የገጠር ቀቤሌዎች የመስኖ እርሻ ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡ ወረዳዉ በስሩ ያሉትን ወንዞች በመጠቀም በበጋ ወቅት የቦቆሎ ፣የቲማቲም እና ሌላም አትክልቶችን በማምረት ወደተለያዩ የጎረቤት ክፍሎች በተለይም ወደ ጅማ ፣አሰንዳቦ ፣ሰኮሩ ፣ደነባ በማጓጓዝ ለነጋዴዎችም ሆነ ለአምራቹ ገበሬ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር አስችሏል፡፡

የኦሞ ናዳ ወረዳ  ለግንባታ አገልግሎት ዘርፍም የሚዉሉ የአሸዋ ምርት ከመኖሩም በተጨማሪ ለጡብ መስሪያ ሊያገለግል የሚችል የኖራ ድንጋይ ያለበት መሆኑም ይታወቃል፡፡

መሰረተ ልማትን በተመለከተ በወረዳዉ ያሉ ሁሉም ቀበሌዎች ከወረዳዉ ከተማና እርስ በእረስ የሚያገናኝ የገጠር መንገድ ተጠቃሚ ናቸዉ፡፡ በሶስቱ ከተማዎች አካባቢ ያሉ የገጠር ቀበሌዎችም የኤሌክትሪክ መብራት ተጠቃሚዎች ናቸዉ፡፡

ወረዳዉ የተማሪን ዜጋ ለማፍራት እና ትምህርት ለሁሉም ማህበረሰብ ለማድረስ ተልኳቸዉን በመወጣት ላይ ያሉ አንድ የመሰናዶ ትምርት ቤት ፣ የሙያና ቴክኒክ ተቋም ፣ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣በአጠቃላይ በገጠር እና በከተማ ከአንድ እስከ ስምንት ያሉ ትምህርት ቤቶች ብዛት ሰማኒያ አንድ(81) ሲሆን ሰባሁለቱ በገጠር የሚገኙ ሲሆኑ  ዘጠኙ በከተማ የሚገኙ ናቸዉ፡፡ (ኦሞናዳ ወረዳ ትምህርት ቢሮ)

በጤና ዘርፍ ደግሞ በወረዳዉ ዉስጥ አንድ አንደኛ ደረጃ ሆስፒታል ፣ 7(ሰባት) ታዳጊ ጤና ጣቢያዎችና 24(ሃያ አራት) ጤና ኬላዎች ይገኙበታል፡፡ (የኦሞናዳ ጤና ቢሮ)

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ሥነ ዘዴ

በዚህ ክፍል ጥናቱ ሲደረግ ምን ምን ተግባራት እንደተከናወኑ፣ ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች አይነት፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችና አስፈላጊነታቸው ተገልጿል።

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ገላጭ ተንታኝ የአጠናን ስልትን የሚከተል ነው። የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በመጠቀም ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን መሰረት አድርጎ የተሰራ ነው።

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት የተካሄደዉ በጅማ ዞን ኦሞ ናዳ ወረዳ ነዉ። ወረዳዉ ሰላሳ ዘጠኝ ቀበሌዎች የሚገኙበት ሲሆን ከእነዚህ ቀበሌዎች የሸክላ ሰሪ ባለሞያዎች በብዛት የሚኖሩበት አንድ ቀበሌ ተመርጠዋል። ይህ የሆነበት ምክኛት በሌሎቹ ቀበሌዎች የሸክላ ሰሪ ባለሞያዎች በብዛት ባለመኖራቸዉ ትክክለኛ መረጃ ላይገኝ ይችላል በሚል ስጋት እና አጥኚዋ በነዚህ ቀበሌዎች መረጃ አቀባዮችን በብዛት አገኛለሁ ብላ በማሰቧ ነው። ምክንያቱም የጥናቱ አካላይ ማለት የተመራማሪው ትኩረት ያረፈበት ቦታ ያመለክታል። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ያለው እንዳወቀ (1998፡119) ላይ “የጥናቱ አካላይ ሲባል ጥናቱ የሚካሄድበት የተመራማሪው ትኩረት ያረፈበት ችግሩ የተከሰተበት አጠቃላይ የተጠኚዎችን ቁጥር ያቀፈ ነው” በማለት ገልጿል።በመሆኑም ይህን ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ይህ ጥናት የተካሄድበት ቦታ በወረዳው ከሚገኙት ቀበሌዎች አንዱን በማካለል ነዉ ። የጥናቱ ትኩረትም ባህላዊ የሸክላ ስራና የኑሮ ዜይቤ በመሆኑ የጥናቱም አካላይ እነዚህ ሁለት ነጥቦችን መሰረት ያደረገ ነው።

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለጥናት ያመቻል ተብሎ የተመረጠው የንሞና ዘዴ አላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው ።ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት የመረጃ አቀባዩች ናሙና አመራረጥ የባህል መረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ዕድል የማይሰጥ የንሞና ዘዴ አካል የሆነው ታላሚ ናሙና ተመራጭ ነው።ይህ ጥናት ሲጠና 45 መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል ።አርባ አምስት የተመረጡበት ምክንያት ለጥናቱ ከተመረጠዉ ቀበሌ አጥኚዋ ስለ ባህላዊ ሽክላ ስራ ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው የሚታመንባቸውን ከወጣት እስከ ሽማግሌ ድረስ ያሉትን በማካተት 30 ሴቶች እና 15 ወንዶች በማካተት መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጋለች ። በእነዚ መረጃ አቀባዮች በመታገዝ ጠቃሚ መረጃ ሰብስባለች። በተለይ እዚያው ተወልደው እዚያው ያደጉ የባህሉ ባለቤቶች ላይ የተለየ ትኩረት አድርጋለች።

### 3.3.1 የቦታ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ ካሉት ሰላሳ ዘኝ ጠቀበሌዎች መካከል አንዱን በመምረጥ ነዉ። አጥኝዋ የመረጃ መሰብሰቢያ ቦታዎችን በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የመረጠች ይሆናል። ይህ ዘዴ በጥናቱ ብቻ የሚካተቱ መረጃዎችን ለመምረጥ አመቺ ከመሆኑ የተነሳ ነው። ምክንያቱም በሌሎቹ ቀበሌዎች የሸክላ ሰሪ ባለሞያዎች በብዛት ባለመኖራቸዉ ትክክለኛ መረጃ ላይገኝ ይችላል በሚል ስጋት ነው። ይህ ቀበሌ የተመረጠዉ በአመቺ የናሙና ዘዴ ነው። ጥናቱ ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ ትንተና ማሳየት ስለሆነ ከዚህም ባለፈ አጥኚዋ አከባቢውን ከሌሎች ቀበሌዎች በተሻለ ሁኔታ ስለምታዉቅና ለስራ የቆየችበት አካባቢ በመሆኑ ልትመርጥ ችላለች።

### 3.3.2 የመረጃ ሰጪዎ ናሙና አመራረጥ

አጥኚዋ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በመረጃዉ ላይ በቂ እዉቀት ያላቸውን ግለሰቦች ከባለሙያዎች ጋር አብራ በመሆን መርጣለች፡፡ ይህ ጥናት በሚደረግበት ጊዜ አስተማማኝ እና ትክክለኛ መረጃ ይገኝ ዘንድ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ስለ ባህላዊ ሸክላ ስራ ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው የሚታመንባቸውን ከወጣት እስከ ሽማግሌ ድረስ ያሉትን በማካተት መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጋለች፡፡ ይህን የእድሜ ክልል ለማካተት የወሰነችበት ምክንያት የእድሜ ባለፀጋዎቹ ድሮ ይገለገሉባቸው ስለነበሩ የቁሶችን ስያሜ፣ አገልግሎታቸውና ተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ስለ ሆኑ ለቁሶቹ የነበራቸውን አመለካከት እንዲነግሯት ስለምትፈልግ ነው፡፡ ወጣቶቹ ደግሞ የሀገር በቀል ቁሶችን ስም፣አገልግሎትና ለቁሶቹ ያላቸውን አመለካከት እንዲገልፁላት በመፈለግ 30 ሴቶችና 15 ወንዶችን በድምር 45 መረጃ አቀባዮችን በመምረጥ ቁልፍ መረጃ ሰብስባለች፡፡ በተለይ እዚያው ተወልደው እዚያው ያደጉ የባህሉ ባለቤቶች ላይ የተለየ ትኩረት አድርጋለች፡፡

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ጥናቱ ቀዳማይ እና ካልአይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የተካሄደ ሲሆን በተለይም ከመስክ በተገኙ መረጃዎች የተዋቀረ ነዉ ፡፡በመሆኑም መረጃዎቹን ለማግኘት እንዲሁም የተገኙትን መረጃዎች ለመተንተን የተከተለቻቸዉን ዘዴዎች በሚከተለዉ መልኩ አስፍራቸዋለች፡፡

### 3.5 ቀዳማይ የመረጃዎች መሰብሰብያ ዘዴ

የቁሳዊ ባህል ጥናት ባጠቃለይ የፎክሎር ጥናት የመስክ ምርምር የሚጠይቅ እንደመሆኑ ይህ ጥናትም በቀዳማይ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ማለትም ቃለ መጠይቅ ፣ምልከታ እና በተተኳሪ በድን መስክ ላይ በተገኙ መረጃዎች በመታገዝ የተካሄደ ነዉ ፡፡ የመስክ ምርምር ዋና የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ሲሆን በሶስት መንገዶች ሊካሄድ ይችላል ፡፡ እነሱም ምልከታ ፣ኢንተርቭዉ እና መጠይቅ ናቸዉ ፡፡ በማለት ፈቃደ አስፍረዋል (1991፣90)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Goldstine (1974፣77) እና Jackson(1987,66) ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ መስክ ላይ መረጃ ለመሰብሰብ ጠቃሚ ዘዴዎች መሆናቸዉን ጠቁመዋል ፡፡

### 3.5.1 ቃለመጠይቅ

ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዩች ስለተጠየቁት ጉዳይ ፣ሁኔታ፣ ድርጊት ፣ አመለካከት ገለጻ በማድረግ መረጃ እንደሚሰጡ (Goldstine 1964:77) ይገልጻል፡፡ቃለመጠይቅ ስለአንዳን የሚያውቋቸው የተለያዩ ጉዳዮች ጥያቄዎች በመጠየቅ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡በዚህ መሰረት አጥኚዋ ተገቢሁን መረጃ ይሰጡኛል ብላ ያመነችባቸዉን መረጃ አቃባዮች ለይታለች፡፡

ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች ብዛት 45 ናቸዉ ፡፡እነሱም የጥበቡ ባለሞያዎች ፣ የባለሙያዎች ቤተሰቦች ፣ከባለሙያዎቹ ዉጪ የሆኑ ማህበረሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የመንግስት ሰራተኛዎች ፣ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች ተሳትፈዉበታል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ 20ዎቹ የሸክላ ባለሙያዎች ሲሆኑ 10 የሸክላ ባለ ሙያ ቤተሰቦች እና 6 ታሪክ አዋቂ ሽማግለዎች የተለያዩ አርሶ አደሮች በድምሩ 36 ወሳኝ መረጃ አቃባዮች ተካተዋል ፡፡እነዚህ የመረጃ አቃባዮች በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡ የቀሩት 9 መረጃ አቃባዮች ደግሞ ከባለሙያዎች ዉጭ የሆኑ ማህበረሰቦች ሲሆኑ ከእነዚ ዉስጥ በባለሙያዎቹ አከባቢ የሚገኙ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች በተገኙበት አጋጣሚ ተሳትፈዋል ፡፡

የመረጃ አቀባዮች የእድሜ ክልል ከ18-80 ዓመት ድረስ ያሉትን ያካተተ ነው፡፡አጥኚዋ ከወጣት እስከ ሽማግሌ ድረስ ያካተተችበት ምክንያት የእድሜ ባለፀጋዎቹ ከድሮ ይገለገሉባቸው ስለነበር የቁሶችን ስያሜ፣ አገልግሎታቸውና ተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ለቁሶቹ የነበራቸውን አመለካከት እንዲ ነግሯት ስለፈለገች ነው፡፡ ወጣቶቹ ደግሞ የሀገርበቀል ቁሶችን ስም፣አገልግሎትና ለቁሶቹ ያላቸውን አመለካከት እንዲያብራሩላት በመፈለግ ነው፡፡ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች የተመረጡ በሚከተሉት መስፈርት ነው፡፡ እነሱም፡- የአካባቢውን ባህልና ታሪክ በአግባቡ የሚያውቁ፣ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸው እና ቁሶቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲሰጡት የነበረውን እና እየሰጡት ያለውን አገልግሎት የሚያውቁ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አጥኚዋ ቃለ መጠይቅ የተጠቀመቹ በምልከታ ወቅት ማግኘት ያልቻለቹን መረጃ ለማግኘት ሲሆን የተገኙትን መረጃዎች በምስል እና በድምፅ ሪከርድ አዘጋጂታለች ፡፡

በቃለ መጠይቅ በመታገዝ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ የሸክላ ሂደቶችን ዝርዝር የባለሙያዎቹን ማህበራዊ እና እኮኖሚያዊ ደረጃ ሙያዉን የለመዱበት ሁኔታ የገጠሚቸዉን ችግሮች

እንዲሁም ለወደፊት በሙያዉ ለመቀጠል ምን ያህል ፍላጎት እንዳላቸዉ ተገቢዉን መረጃ ለመሰብሰብ ችላለች ።

ቃለመጠይቁ የተካሄደዉ ቀድሞ በተዘጋጀዉ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች (structured interview) ሲሆን ቀድሞ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች ከባለሙያዎቹ ፣ ከባለ ሙያዎቹ ቤተሰቦች እንዲሁም ከአጉራባች ነዋሪሆች ጋራ ባካሄደቹ ቃለ መጠይቅ ተገልግላበታለች። ቀድሞ ያልተዘጋጀዉን ቃለ መጠይቅ ከመረጃ አቃባዮች ምላሽ የጠየቀቻቸዉ ናቸዉ። ቃለመይቁን በማካሂድበት ወቅት መቅረጸድምፅ ወይንም ቴፕ በመጠቀም ባጠቃላይ 16GB ፍላሽ የተገለገልኩ ስሆን ሁሉም ካሰቶች /Transcribed/ ሆነዋል።

ቃለመጠይቁ የተካሄደዉ ባለሙያዎቹ የዋልካ አፈር በሚቆፍሩበት ቦታ እንድሁም ቤታቸዉ አካባቢ የሸክላ ስራ ሀደቱን በሚያከናዊኑብተ ወቅት ማለትም የተለመደ ስራቸዉን እያከናዉኑ ባሉበት ሁኔታ በተፈጥሯዊ መቼት በድምፅና በካሜራ የተቀረፀ ነዉ።

በቃለመጠይቁ በመታገዝ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ የሸክላ ዉጤቶችን ዝርዝር ፣የባለሙያዎቹን ማህበራዊ እና እኮኖሚያዊ ደረጃ ፣ሙያዉን የለመዱበት ሁኔታ ፣ያጋጠማቸዉን ችግሮች ለመሰብሰብ ችላለች።

### 3.5.2 ምልከታ

ምልከታ በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ በመገኘት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።ይህ ዘዴ በመስክ ላይ ሁኔታዎችን በተፈጥሯዊ ግኝታቸው በማየት፣ በመስማት፣ ወይም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው ። መልከታ አንድ መስከኛ ከዉጭ ሆኖ ሌሎች ሰዎች የሚያከናዉንትን ድርጊት ቀጥታ በተመለከተበት ሁኔታ የሚገልጽበት ሲሆን ምልከታዉ ከእይታ ገጽታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የስሜት ህዋሳትን በመጠቀም መስማት ፣ መዳሰስ ፣ ማሽተት እና መቅመስን በማካተት መረጃ የሚገኝበት ዘዴ መሆኑን Jackson( 1987,63)እና Goldstein (1974፣77)ገልጸዋል ።

በዚህ ጥናት በዚህ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ በመታገዝ የሸክላ ባለሙያዎች ባህላዊ እዉቀታቸዉን ተጠቅመዉ ባህላዊ የሸክላ ቁሶቹን ሲሰሩ ስምምነት በመፍጠር ምልከታ

በማድረግ የቁሶቹን አሰራር እና የሚያልፉትን ደረጃዎች በመመልከት እና መረጃዎችን በማሰባሰብ የሰበሰችዉን መረጃዎች በቪዲዮ ካሜራ እና በመቅረፅ ድምጽ ሰንዳለች፡፡

### 3.5.3 ተተኳሪ ቡድን ዉይይት

ያለው (2009 ዓ.ም) በተተኳሪ ቡድን ውይይት እስከ 12 ሰዎች ማሳተፍ እንደሚቻል ሲገልጽ አባላቱ ከ8-10 ቢሆኑ የተሻለ እንደሚሆን ያስረዳል ፡፡ አጥኚዋ በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ እርስበርስ የሚፋለሱ ሃሳቦችን በአግባቡ ለመለየት ትክክለኛውን መረጃ ለማጣራት የተተኳሪ የቡድን ውይይት ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ ይህን ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ መረጃ አቀባዮችን በሚከተለዉ መልኩ በመምረጥ ነዉ ፡፡በለቃለ መጠይቅ እዲሳተፉ የተመረጡት የአካባቢውን ባህል ጠንቅቆ ማወቅ፣ ድሮ ይሰሩ የነበሩ ቁሶችን ስያሜና አገልግሎት የሚያውቅ እና ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቅርበት ያላቸውን በግምት ዉስጥ በማስገባት ነዉ፡፡ ተተኳሪ ቡድን ዉይይት በቃለ መጠይቅ የተገኙትን ሀሳቦች በቡድን ስለመደገፋቸዉ ለማረጋገጥ የሚያስችል አይነተኛ ዘዴ ነዉ፡፡

## 3.6 ካላአይ የመረጃዎች መሰብሰብያ ዘዴ

አንድመስከኛ ወደ መስክ ምርምር ከመዉጣቱ በፊት በሚያጠናዉ ጉዳይ ላይ ቅድመ መስክ ዝግጅት /pre field preparation / ለያከናዉን ይገባል ፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ MacDonald (1972 ፣ 4070) የሚከተለዉን አስፍሯል ፡፡ "እንደ ሚታወቀዉ ማንም ሰዉ በባህል ወደ ዳበረ አከባቢ በመሄድ ጠቃሚ ነገር ማግኘት ይችላል ፤ነገር ግን አብዛኛዉ ስራት ያለዉ የመስክ ምርምር የሚጀምረዉ በቤተመጻህፍት እና በቤተ መዛግብት ባለ ጠጴዛ ላይ ነዉ"፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ወደ መስክ ከመዉጣትዋ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያ የተለያዩ ቀደምት ተዛማች ስራዎችን መጻህፍትን ፣የእንተርኔት ምጮችን በመመልከት ጠቃሚ ሀሳቦችን በማስታወሻዋ ለመያዝ ችላለች፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ካልአይ የመረጃ ምንጮችን ከመስክ መልስም እንደገና በጥልቀት ለመመልከት ችላለች ፡፡ MacDonald (1972፣413-414) ,Goldstein (1974፣36-37)እንዲሁም ፍቃደ (1991፣118 )እንደጠቆሙት ፣የራስን ባህል ሲያጠኑ የሚታጣ ነገር መኖሩ ሳይዘነጋ፣የሚያዉቁትን አካባቢ መጥናት የሚያስገኘዉ ጠቀሜታ

በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። አጥኚዋም ያደገችበት አካባቢ በማጥናት ቢያንስ የቋንቋ እና የባህል ልይነት ያል ገጠማት መሆኑ በመልካም ጎኑ የሚጠቀስ ነዉ።

## 3.7 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በቀዳማይ እና በካልኣይ የመረጃ ማሰባሰብያ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ጥናቱን ከግብ በሚያደርስ መልኩ በማደራጀት ለመተንተን ተችሏል ።ባህላዊ የሸክላ ስራ የቁሶቹ ባለቤት በመደቡበት መስፈርት እና በሌላ በኩል ደግሞ በሚሰጡት አገልግሎት አንጻር በመመደብ ለመተንተን ተሞክሯል ። ትንተናዉም Schlereth ውስተ ኢንተርኔት (,2017 7-8) የቁሳዊ ባህል የመተንተኛ ዘዴዎች በማለት ካስቀመጣቸዉ ደረጃዎች ዉስጥ መሰረት በማድረግ ለማሳከት አጥኚዋ ጥረት አድርጋለች።

## 3.8 የመስክ ቆይታ

የዚህ ጥናት ርዕስ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ጅማ ዩኒቨርስቲ ከአማርኛ ቋንቋና ስነ ፅሁፍና አማርኛ ትምህርት ክፍል አጥኚዋ የተጻፈላትን የትብብር ደብዳቤ ይዛ ወደ ኦሞናዳ ወረዳ በመሄድ ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸዉን የኦሞ ናዳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ አቶ ማሀመድአሚን አባ/መጫን በማነጋገር የሄደችበትን ዓላማ በመግለፅ ስታስረዳዉ በስራ ጉዳይ እዛ ቀበሌ ላይ ተመድቤ ስሰራ ስለ ነበር የአከባቢዉን ማህበረሰብ አዉቃለሁ በማለት የሸክላ ባለሙያዎች በታቀደበት ቀበሌ በየትኞቹ አከባቢ በብዛት እንደሚኖሩ እና የማህበረሰቡን ባህልና ታሪክ እነማን በአግባቡ ያውቃሉ? በሚሉ ነጥቦች ላይ ውይይት በማድረግ መንገድ መርቷታል ። ካስተዋወቋት የመረጃ አቀባዮች መካከል የተወሰኑትን እሷም ታውቃቸው ስለነበር በእነሱ አማካኝነት ሌሎች የመረጃ ሰጪዎቼን በመተዋወቅ የለሊሳ ቡላን ማህበረሰብ ባህልና ወግ ማወቅ እንደምትፈልግ ገለጻችላቸው።

በዚህ መንገድ የተጀመረው ውይይት ወደ ባህልና ታሪክ፣ሃይማኖት፣ቋንቋ፣ባህላዊ አስተዳደር፣የሰርግና ሃዘን ስነስርዓትን ምን እንደሚመስል መረጃ እንዲሰጧት አስተባበረች።በማስከተልም የሸክላ ባለሙያዎች በየትኞቹ አከባቢ ውስጥ እንደሚገኙ እንዲለዩላት አደረገች። የመምረጫው መስፈርት ብዙ ባለሙያዎች የሚገኙበት ቦታ፣ የተለያዩ ቁሶችን የሚሰሩበት ተጠቃሽ ናቸው። የተመረጡትም ሰዎች ተወያይተው የሸክላ ባለሙያዎች

ካራ፣ለሊሳ እና ወሌ  እንደሚገኙ ገለፁላት ። ለጥናቱ የተመረጡላትን ሰፈሮች የተወሰኑትን ታውቃቸው ስለነበረ በየሰፈሮቹ በመዘዋወር የማታውቃቸውን ደግሞ በመንገድ መሪ አማካኝነት በመንቀሳቀስ ከባለሙያወቹ ጋር የጥናት ውይይት አካሄደች። በዚህ መልኩ ከመረጃ አቃባዮች ጋር በመግባባት ጥናቷን ለማካሄድ ችላለች ።

# ምራፍ አራት

# የጥናቱ የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል የለሊሳ ቡላ ማህበረሰብ የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ ፣የሸክላ ስራ ሕይወት እና ልምድ ምን እንደ ሚመስል ከባለሙያዎቹ በተገኘዉ መረጃ በመታገዝ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ጥናቱ በዋናነት ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ መተንተን አላማዉ ያደረገ ቢሆንም Glassie ዉስጥ Dorson (1983፣380 እና 1999፣42) እንደ ጠቆሙት የአንድ ማህበረሰብ ቁሶችን ለማጥናት ለመፈከር ስንነሳ ቁሶቹን የፈጠሩትን ባለሙያዎች (craftsman or performers) አብረዉ መጠናት እደሚገባቸዉ እና በተለይም ቃላዊዉም ሆነ ቁሳዊ የፈጠራ ችሎታ በፈጣሪዎቹ አምሮ (performer's mind) ዉስጥ ተደብቆ ስለ ሚገኝ እሱን መመርመሩ አንጻች ጠቀሜታ እንዳለዉ በመታመኑ የባለሙያዎቹን ሕይወት እና ልምድ አጥኚዋ በስፋት እንድትመለከተዉ አስችሏታል፡፡

## 4.1 የለሊሳ ቡላ ገጠር ቀበሌ የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ

የለሊሳ ቡላ ነዋሪዎች የሸክላን ስራ መች ጀመሩ? ሙያዉን እንዴት እና ከማን አገኙት? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ በአካባቢዉ ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ እና አዋቂ ከተባሉት አባቶች በተገኘ መረጃ በመታገዝ እንደሚከተለዉ ቀርቧል ፡፡ በለሊሳ ቡላ የሚገኙ የሸክላ ሰራተኞች የሸክላ ስራ  የጀመረበትን ጊዜ በትክክል ለመናገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም መረጃ አቃባዮቹ ሙያዉ በጥንት ጊዜ መጀመሩና  ሙያዉን የለመዱት ከአያት ቅድመ አያቶቻቸዉ መሆኑን ነዉ ደጋግመዉ የሚናገሩት ፡፡ ሁሉም መረጃ አቃባዮች በዚህ ዙሪያ ያላቸዉ መልስ  ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ የተለያዩ የባለሙያዎችንም ሆነ ከሙያዉ ዉጪ ያሉትን ማህበረሰብ ሀሳብ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

አ/ራያ አ/ዱራ በግምት የስልሳ አመት የእድሜ ክልል ዉስጥ ልኖር እችላለዉ በማለት ንግግራቸዉን በፍቃደኝነት ጀመረዉልኛል፡፡ እድሜያቸዉን አስመልክቶ በኔ እይታ ከሰባ አምስት እስከ ሰማኒያ የእድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ የእድሜ ባለ ጸጋ ሲሆኑ ስለ ለሊሳቡላ የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ በሚከተለዉ መልኩ ተናግረዋል፡፡



**ምስል 1** አ/ራያ አ/ዱራ ቃለመጠይቅ ስደረግላቸዉ

“Naannoo Lalisaa Bulaatti hojiin Suphee kan eegalame dur bara A/Qoroo A/Zaban A/ Jirgaa Bolchaa Naannoo Turanitti. Isaantu Namoota oogummaa akkasii qaban fidee lafa mataa isaanii irra qubachiise. Akka wasiilli koo A/ Waajii natti himanitti Abbaaan Qoroo keenya jara Fugaa fidanii erga qubachiisanii booda suphee lafuma isaanii irraa fayyadamanii hojii suphee eegalchiisan jechuun dhagahe. Bakka kamittuu jara abbaa qabeenyaatu lafa isaanii irra qubachiisaa hojii hojjechiisa yoo hin qubachiisne ni gaafatamu.”

“በለሊሳ ቡላ አከባቢ የሸክላ ስራ የተጀመረዉ በጥንት ጊዜ አ/ቆሮ አ/ዘበን አ/ጅርጋ በሚባሉ የአገር ሊቀመንበር ነበሩ። እና እሳቸዉ ናቸዉ አምጥተዉ የራሳቸዉ መሬት ላይ ያስቀመጧቸዉ ማለት ነዉ። የሰማሁት አባ ዋጂ የሚባሉ አጎት ነበሩኝ እና አባ ቆሮአችን ፉጋዎችን አምጥተዉ መሬታቸዉ ላይ አስቀምጠዉ ከራሳቸዉ መሬት ላይ እቃ እየሰጡ ነዉ ያስጀመሩት ሲባል ነዉ የሰማዉት። የትህም ቦታ ላይ ሀብታም ሀብታሙ ነዉ የራሱ መሬት ላይ እያስቀመጣቸዉ ስራ የሚያሰራቸዉ ባያስቀምጧቸዉም ይጠየቃሉ” ።

እስኪ ለእነዚህ ባለሙያዎች ምን አይነት አስታየት አላችሁ ብዬ ስጠይቃቸዉ የሰጡኝ መልስ የሚከተለዉን ይመስላል።

“Lakkii nutti akka oromootti ilaalcha adda tahe tokkoyyuu hin qabnuu. Tumtuu dha; Fugaa dha; sheekiidha; Hanquudha sababni nuti jenneef yoo kaanee taayitaa walfakkaataa kennineef lamuu nuuf ajajamanii hojiioogummaa isaanii hin hojjetani soda jedhuun. Malee jarri nurra hanqina hin qaban. Bu.aa OOgummaa Isaanii Sirriitti Barbaanna.Miini Isaanii jireenya keenyaaf nu barbaachisu. Dhimma qoonqooti egaa meeshaa nyaata itti bilcheessan malee jiraachuun hin danda’amu. Amma malee dur meeshaan biraa hin argamu.jiruu waan ta’eef yoo jaraa taayitaa kenninee ofiin of qixxeessine nuuf hin ajajamne soda jedhuuf maleekan biraatiif miti.Oromoonni kallattii mataa isaanii haala jiru ittiin ilaalan qabu. Waan fuulduratti itti dhufu dursanii argu; kun immoo kennaa Uumamaati.”

"ኧረ እኛ እንደ ኦሮሞ ምንም የተለየ አስተያየት የለንም፡፡ ቀጥቃጭ ነዉ ፣ ፉጋ ነዉ ፣ ሼኪ ነዉ ፣ ጎዶሎ ነዉ ያልንበት ምክንያት ተነስተን ከኛ እኩል ወንበር ብንሰጣቸዉ ሁለተኛ ታዘዉልን ይህን ስራ አይተገብሩልን በሚል ፍራቻ ነዉ፡፡ እንጂ እነሱን ከኛ ያጎደሉት ሌላ ችግር የለም፡፡ ቁሳቸዉን በደንብ እንፈልጋለን፡፡ ቁሳቁሶቹ ለኑሮዋችን የሚያስፈልጉን ናቸዉ፡፡ የጎሮሮ ጉዳይ ነዉ እና ያለማብሰያ መኖርም አይቻልም፣ አሁን አሁን ነዉ እንጂ ከዚህ በፊት ሌላ መስርያ የለንም፡፡ መኖርያችን ሰለሆነ ለነሱ ደግሞ ስልጣን ብንሰጠቸዉ እና ከራሳችን እኩል ብናስቀምጣቸዉ ሁለተኛ አይታዘዙልንም በሚል ፍራቻ ነዉ እንጂ ሌላ ፍራቻ የለንም፡፡ ኦሮሞዎች ደግሞ ነገሮችን የሚያዩበት የራሳቸዉ የሆነ መሳርያ አላቸዉ፡፡ ከዋላ የሚመጣባቸዉን ቀድመዉ ያያሉ ይህ የተፈጥሮ ጸጋ ነዉ፡፡"

በመቀጠል ትዳርን አስመልክቶ ያላችሁ ቀረቤታ ምን ያህል ነዉ? ትጋባለችሁ? ብየ ስጠይቃቸዉ "በትዳር አንቀላቀልም ምክንያቱም መጀመርያ እንደነገርኩሽ ወንበራችን ልዩነት አለዉ ፡፡ እነሱም የራሳቸዉን ነዉ የሚያገቡት እንጅ መቀላቀል የለም፡፡" የሚምላሽ አቅርበዋል፡፡

"እንዴት ነዉ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ይቻላል?" ብዬ ብጠይቃቸዉ "ማዳቸዉ ላይ እኛ አንቀመጥም፡፡ እነሱም ማዳችን ላይ አይቀመጡም ፣ የሀብታም ማድ ላይ እነሱ አይቀመጡም፡፡ እኛም የነሱ ማድ ላይ አንቀመጥም፡፡ የተለየ አመለካከት አለ፡፡" በማለት አቅርበዋል፡፡

ሌላዉ እነኚህ ሰዎች ሰዉ ይበላሉ የሚባል አመለካከት አለ ፤ ሁነታዉ እንዴት ነዉ የሚታየዉ? ለሚለዉ ጥያቄ "በወሬ ደረጃ እንጂ እነሱን እድሜዬ አልደረሰም። ብዙ ዘመን አሳልፈዋል። አይደለም ከኔ ከቤተሰቦቼም በላይ ነዉ ይርቃል። አዉን እኔ ስልሳ አመት ቢሆነኝ አባቴም ከሞቱ ስልሳ አመት ይሆናቸዋል ማለት ነዉ። ጉዳዩ ደግሞ ከአባቴም በፊት ነዉ ማለት ነዉ።" ግልጽ እንዲያደርጉልኝ ደጋጋሜ ብጠይቃቸዉም "ይህን ቤተሰቦቼም ስላልደረሱበት ተጨባጭ የሆነ የምነግርሽ ነገር የለኝም። ባይሆን ያገኙትን ነገር እንደሚበሉ አዉቃለዉ። ስለነሱ የማዉቀዉ ታሪክ ይህንኑ ነዉ።" በማለት መልሰዉልኛል።

እንግዲህ ከአ/ራያ አ/ዱራ ለመረዳት እንደተሞከረዉ በለሊሳ ቡላ አካባቢ የሸክላ ስራ የተጀመረዉ በጥንት ጊዜ አ/ቶሮ አ/ዘበን አ/ጅርጋ የሚባሉ የአገር ሊቀመንበር እነኝህን ሞያተኞች አምጥተዉ የራሳቸዉ መሬት ላይ በማስቀመጥ ለራሳቸዉ እና ለመሰሎቻቸዉ እቃዉን እያሰሩ እንደሚጠቀሙ ነዉ በተደጋጋሚ የተገለጸዉ ።

ሀ/ቢያ አባመጋል የ75 አመት የእድሜ ገደማ ዉስጥ የሚገኙ ሲሆን በለሊሳ ቡላ አካባቢ ተወልደዉ እስከ እርጅና ጊዜያቸዉ የቆዩ ሲሆኑ በአካባቢዉ ሰዉ 'አዶ' በመባል በክብር ስም ይጠራሉ። የለሊሳን የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ እንደሚከተለዉ ገልጸዋል።

“Nan yaadadha yeroo sana daa’iman ture qe’ee keenya keessa maatii baayyeetu ture. Gabaabumaan haalli jireenya keenyaa walitti dhufeenyi maatiwwan keenya namatti tola ture. Bunni kan dhugamu mana isaaniitii fidanii mana abbaa kootiitti dha. Ganama gaaf tokkoo walitti qabamanii bakka turanitti namni tokko dhufee nu waame jennaan galaa jennaan ol hin galu “dhaamsa mootii kootinan isiniin gahuuf dhufe dhaamsi isin naaf keessan gaheeraa nama ergadhaa fudhaa” jedhee dubbatee deebi”ee deeme. Akaakayyuun koo “maal inni” jedhanii gaafatan. “dhaamsichi kan dhufe A/Zaman biraayyi jara Fugaa akka naaf dabalu itti himadheetani” jedhanii deebisan…”

“አስታዉሳለዉ እኔ የዛኔ ልጅ ነበርኩ በቀያያችን ብዙ ቤተሳቦች ነበሩ። የኑሮአችን ሁኔታ በአጭሩ የቤተሰብ ስብስብ በመንደራችን ዉስጥ ደስ ይል ነበር እና ቡና የምንጠጣው ከየቤታቸዉ ይዘዉ መተዉ የአባቴ ቤት ዉስጥ ነዉ። ጠዋት ሁሉም ተሰብስበዉ ባሉበት አንድ ሰዉ መጣ ና ተጣራ "ግባ" ቢሉት አይ አልገባም "የአለቃዬን መልእክት ለማድረስ ነዉ

የመጣዉት እና ያስቀመጡት መልክት  ደርሰዋል አንድ ሰዉ ልከዉ ይዉሰዱ" በማለት ተናግሮ ተመልሶ ሄደ፡፡ አያቴ "ምንድ ነዉ" በማለት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ "መልክቱ የመጣዉ ከአባ ዘበን ነዉ ፉጋዎችን እዲጨምርልኝ ነግሬዉ ነዉ" በማለት መለሱላቸዉ፡፡ አንድ ያጎቴ ልጅ በዛን ሰአት ልጅ ነበር እና ፉጋ ምንድነዉ? ብሎ ቢጠይቃቸዉ አያቴ "ፉጋ ማለት ሰዉ ሁኖ ሰዉን ለማገልገል የተፈጠሩ የኛ አገልጋዮች ናቸዉ፡፡" እነሱ ባይኖሩ ለመመገብያ የሚያገለግሉ የቤት ዉሥጥ ቁሳቁሶች አይኖረንም ነበር እና ለዚ ነዉ መሬታችን ላይ በማስቀመጥ ከአፈራችን ቁሶችን እዲሰሩ ያዘዝናቸዉ፡፡ ልክ አያቴ አዉርተዉ ሲጨርሱ አብረን ቤታቸዉ እንሀድ ቁሳቸዉን እናምጣ ብሎ ቢጠይቃቸዉ አይሆንም ክብራችን ይነካል ቤታቸዉ አንሄድም ቤታችን አይመጡም፣የኛ መቀመጫ ላይ አይቀመጡም ነዉር ነዉ፡፡ ከፈለክ እቃዉ ይመጣልሀል በማለት መለሱለት፡፡ እና ወደጥያቄሽ ስመለስ በዚህ አገር የሸክላ ስራ የተጀመዉ በጥንት ጊዜ በ/ቆሮ አ/ዘበን  አ/ጅርጋ የአገር  አስተዳዳሪ በነበሩበት ጊዜ ነዉ፡፡

"እንዴት ነዉ ሰዉ ይበላሉ የሚባለዉ ነገር?" "በዓይኔ ያየዉት ነገር የለም ከቤተሰቦቼ የሰማዉትም ይህኑ ቃል ነዉ፡፡ እነሱም ይላሉ፡፡ ነገር ግን በተግባር የታየ ነገር የለም የሆነ የሰማዉት ጭጭምታ እነዚህ ሳይሆኑ ሌላ ዘሮች እንዳሉ ነዉ ወይንም የመጀመርያዎቹ ናቸዉ፡፡ እንጂ እነዚ ላይ የታየ ምንም ነገር የለም ብቻ ይታማሉ፡፡ ጋብቻን አስመልክቶ መቼም ቢሆን ከኛ ጋር ሊቀላቀሉ አይችሉም፡፡ እነሱ አናሳዎች ናቸዉ ነገር ግን አዉን አዉን አብሮ መስገድ ፣ አብሮ መብላት ፣ አብሮ መጣት ተጀምሮዋል፡፡ ይህ ነገር ልክ አይደለም ባይ ነኝ፡፡ ለልጅ ልጆቻችን አደጋ አለዉ ባይ ነኝ፡፡ በፊት ያመጣናቸዉ ለቁሳቸዉ ነበር፡፡ እየቀረ መተዋል እና መቀላቀላቸዉ ቀርተዉ የታወቀ ቦታ ቢሰጣቸዉ ባይ ነኝ፡፡ መጥፎ መቼም መጥፎ ነዉ በማለት ያላቸዉን አመለካከት ገልጸዉልኛል፡፡(14/7/2011) ፡፡

የሸክላ ስራ አጀማመር ታሪክ ይህን ያህል ካልን ከዚህ በመቀጠል  የሸክላ ሰራተኞች ጥበቡን እንዴት እንደለመዱ ባለሙያዎች ከሙያዉ ጋር በተያያዘ ያጋጠማቸዉ ችግሮች ፣ የባለሙያዎቹ እኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ደረጃ እና የሙያዉ ቀጣይነት በሚሉት ላይ ትንተና ተካሂደዋል ፡፡

## 4.2 የሸክላ ሰራተኞች /ባለሙያዎች ጥበቡን የለመዱበት ሁኔታ

Roberts ዉስተ Dorson (1972፣233) እና Bronner ወስተ Oring (1986፣199) ሀገረሰባዊ እጅ ስራ በልጅነት ጊዜ በምልከታ ፣በመኮረጅ እና ደጋግመዉ በመስራት የሚካኑት ጥበብ

መሆኑን እንደጠቆሙት ሁሉ የለሊሳ ቡላ የሸክላ ሰራተኞች /ባለሙዎች የለመዱት በመመልከት እና ደጋግሞ በመስራት ሲሆን ከበርካታ ባለሞያዎች የተገኘዉ የህይወት ተሞክሮ ይህንኑ የሙሁራንን ሀሳብ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል ። ብዙዎች መረጃ አቃባዮች እንደሚገልጹት ከሆነ ባለሙያዎቹ ሙያዉን የለመዱት በልጅነት ጊዜያቸዉ እናታቸዉ ሲሰሩ ፣እህቶቻቸዉ ሲሰሩ ፣በማየት ፣የቅርብ ዘመዶቻቸዉ ሲሰሩ በመመልከት እና በእናታቸዉ ቤት በአግባቡ ያለመዱትን በአማቾቻቸዉ ቤት ሲሰሩ በመመልከት እና ለማገዝ በሚያደርጉት አጋጣሚ ትንንሽ እቃዎችን ደጋግሞ በመሞከር እና በመስራት ከሙያዉ ጋር እዲተዋወቁ እድል ከፍቶላቸዋል ።በልጅነት ጊዜ ከሙያዉ ጋር መተዋወቃቸዉ እድሜያቸዉን ሙሉ ታዋቂ ባለሙያ እንዲሆኑና የተወሰነ መሰረታዊ ፍላጎታቸዉን ለሟሟላት የገቢ ምንጫቸዉ እንደሆነ ገልጸዋል ።

ሀ/ሙሂዲን አባ ጊዲ 40 አመት የሞላቸዉ ሲሆኑ የአምስት ሴቶች እና የሶስት ወንዶች እናት ናቸዉ። እራሳቸዉን ካወቁበት ጊዜ አንስተዉ ሸክላ በመስራት እድሜያቸዉን እንዳሳለፉ ልጆቻቸዉንም ሸክላ ሰርተዉ በመሸጥ እንዳሳደጉ እና እንዲሁም እናታቸዉን በማየት ሙያዉን እንደለመዱ እንደ ሚከተለዉ አጫዉተዉኛል ።

የሸክላ ስራ ካመን ለመዱ? የሚል ጥያቄ ስጠይቃቸዉ የመለሱልኝን መልስ እንደሚከተለዉ አስቀምጣዋለች ።

> ‘’… akkuma maatiin hundi godhu oogummaa kana kan na barsiise haadha kooti. Yeroon mana jiru haadha kiyyaa waanin hojjetaa tureef ergan heerumees ittin fufe. Hojichii waan nama gammachiisu baayyee yoo hin qabnes toles bades ittiinan bula. Ijoollees ta,e abbaa manaa koo kanan bulchu bu,aa oogummaa kanaatiini. Lafa bal’aa hin qabnu. Oomishni qonna irraa argannu hamma kana miti kanaafuu daa’imman kootiin wal qarqaarree hojjechuun qoonqoo maatii kooti akka naa danda’uuf meeshaalee garagaraa hojjedha. Eelee, ixan macesha, waciitii, jabanaa fi maandajaa hojjechuun torbanitti guyyaa lama gabaa geessa. Duraan gaanii warra barbaadaniif ajajaanin hojjedhan ture. Amma garuu meeshaalee ammayyaa waan fayyadamaniif dhiiisaniiru malee bu’aa gaarii qaba ture.”

…ያዉ ማንኛዉም ወላጅ እንደሚያደርገዉ ሙያዉን ያስለመደችኝ እናቴ ናት:: ቤት እያለዉ ለእናቴ እሰራ ስለነበር ትዳር ከያዝኩም ቀጠልኩበት፡፡ ስራዉ ብዙ የሚያስደስት ነገር ባይኖረዉም ከፋም በጀም መተዳደርያ ሆኖኛል፡፡ ልጆቼንም ሆነ ባለቤቴን የማስተዳድረዉ ከዚዉ በማገኘዉ ጥቅም ነዉ፡፡ ሰፊ መሬት የለንም፡፡ በእረሻ የምናገኘዉ እህል ብዙም አይደለም ስለዚህ ከልጆቼ ጋር ተጋግዘን በመስራት የእለት ጉሮሮዬን እንድሸፍንልኝ የተለያዩ እቃዎችን ሰራለዉ፡፡ ምጣድ ፣እጣን ማጨሻ፣ ወጪት ቡና ማፊያ እና እሳት ማንደጃ በመስራት በሳምንት ሁለት ገበያዎች በመዉሰድ እጠቀማለዉ፡፡ ከዚህ በፊት ጋን የሚፈልጉ ሰዎች በትዛዝ ያሰሩኝ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ዘመናዊ  እቃዎችን በመጠቀም ጋኑን ትተዉታል እንጂ ከሌሎቹ የተሻለ ገቢ ያስገኝልኝ ነበር፡፡" (2/7/2011 ለሊሳ ቡላ)

በተመሳሳይ መልኩ ሀ/ሱልጣን አባ ራያ የአርባ አምስት አመት የእድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ወይዘሮ ሲሆኑ  ሙያዉን ከማን እንደ ተማሩ ስጠይቃቸዉ  የሰጡኝ ምላሽ "ሙያዉን እናቴ ስትሰራ አግዛት ነበር ነገር ግን በሰፊዉ እጄ  የተፍታታዉ አማቾቼ ቤት መጥቼ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ወደዚ ቤተሰብ ስቀላቀል በጣም ልጅ ነበርኩ ፡፡ ቤት እያለዉ የምሞክርዉ ምጣድ ብቻ ነበር፡፡ እናቴም  የምትሰራዉ እሱን ብቻ ስለ ነበረ እዚህ መጥቼ የተለያዩ እቃዎችን በመስራት ታዋቂ ባለ ሙያም ሁኛለዉ አሁን  የምተዳደረዉም በሱ ነዉ" የሚል ነዉ፡፡ (2/7/2011 ለሊሳ ቡላ)

ወ/ሮ ካንዚ ማመሳኒ 36 አመት ወይዘሮ ነች፡፡ የሸክላ ስራን መቼና እንዴት እንደጀመረች ለቀረበላት ጥያቄ የሚከተለዉን ምላሽ ሰታለች፡፡

"Kan na guddise akkoo koo waan ta'eef jalqabbii isaa kanan baradhe manatti. Haa ta'u malee isheen waan dulloomteef waan garaa garaa hojjeechuu hin dandeessu. Bakki amma ani itti heerumee jiru mana maatii kootii irraa adeemsa sa'aatii sadiiti. Ergan bakka kana dhufee waa hedduu hojjechuu eegaleera. Oogumma isaa ijoollummaatti akkoon koo fi amaatileen koo yeroo hojjetanun arge bare malee mootummaas ta'ee qaamni biraa harka qabee na barsiise hin jiru."

“ያሳደገችኝ አያቴ ስለሆነች መነሸዉን የተማርኩት ቤት ነዉ። ነገር ግን እሷ ስላረጀች የተለያዩ ነገሮችን መስራት አትችልም ነበር እና ትዳር የያዝኩበት ይህ ቦታ ቤተሰቦቼ ከሚኖሩበት የሶስት ሰአት ርቀት ላይ ነዉ የሚገኘዉ እኔም እዚህ ቦታ ላይ መኖር ከጀመርኩ ብዙ ነገሮችን፣ የተለያዩ እቃዎችን ለመስራት ችያለዉ። ሙያዉን በልጅነቴ እያቴ ስትሰራ እያየዉ ነዉ ልምድ ያገኘዉት ፣ከቤተሰቦቼ እና ከአማቾቼ ነዉ አይቼ የለመድኩት እንጂ መንግስትም ሆነ ሌላ አካል እጄን ይዞ አላስተማረኝም።"(2/7/2011 ለሊሳ ቡላ)

ወይዘሬት አሊማ መሀመድሳኒ የ20 አመት ወይዘሪት ሲትሆን የአስረኛን ክፍል ቤሐራዊ ፈተና ተፈትና በዉጤት ያለመሳካት ምክንያት ወደ ቤተሰቦቻዋ ተመልሳ ሁለተኛዉ ዙር ፈተና እስኪመጣ በመጠባበቅ ላይ ያለች ስትሆን ሙያዉን ከማን እንደ ተማረች ስጠይቃት የሰጠችን ምላሽ “ሙያዉን የተማርኩት ከእናቴ እና ከታላላቅ እህቶቼ በሚሰሩበተ ግዜ በትኩረት በመመልከት ነዉ ። በሙከራ የማይሰራ ነገር የለም እኔም የተማርኩት ቤተሰቦቼን እየረዳዉ ከዚህ በማገኘዉ ገንዘብ ነዉ ። እገዛ ቢደረግልን ማሰልጠን ሁሉ እንችላለን” የሚለዉን ነዉ።

ብዙዎቹ መረጃ አቃባዮቼ እንደገለጹልኝ ከሆነ ባለሙያዎቹ ሙያዉን የለመዱበት በልጅነት ጊዜአቸዉ እናቶቻቸዉ ሲሰሩ በማየት ነዉ። እናቶቻቸዉም ሆኑ የቅረብ ዘመዶቻቸዉ ሲሰሩ በመመልከት ለማገዝ በሚያደርጉት አጋጣሚ ትንንሽ እቃዎችን ደጋግሞ በመሞከር እና በመስራት ከሙያዉ ጋር ለመተዋወቅ እድል ፈጥሮላቸዋል። በልጅነት ጊዜ በአጋጣሚ ከሙያዉ ጋር መተዋወቅ በወጣትነትም ሆነ ከወጣትነት በኋላ የእድሜ ዘመናቸዉ ዋና ባለሙያ እንዲሆኑ የገቢ ምንጭ ማግኛ እንደሆናቸዉ ተናግረዋል።

ባጠቃላይ ከሸክላ ሰራተኞች ወይም ከባለሙያዎቹ የቀረበዉን ሀሳብ የምንረዳዉ የሸክላን ስራ የለመዱት በልጅነት ጊዜ ከቤተሰቦቻቸዉ አብረዉ በሚኖሩ ጊዜ እና ከፍ ካሉ ቡሃላ ደግሞ ትዳር በያዙበት አከባቢ ኢኮኖሚያዊ ችግርን ለመቋቋም ከአማቾቻቸዉ ሙያዉን የለመዱ መሆኑን ነዉ ።ባለሙያዎቹ ሙያዉን በልጅነት ጊዜያቸዉ ወይም ካደጉ ቡሃላ የገጠማቸዉን ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማስወገድ በመመልከት እና ደጋግሞ በመሞከር የሚለምዱበት ዋናዉ ምክንያት Trevor (1966፣4 )ሙያዉ ቀላል እና አገልግሎት የሚሰጥ እጅ ስራ በመሆኑ ማንም ሰዉ ብዙ ወጪ ሳያወጣ በቀላሉ ሰርቶ የእለት ችግሩን ለማስወገድ የሚያስችለዉ የገቢ ምንጭ ማግኛ እና ጠቃሚ ሙያ በመሆኑ ጭምር እንደ ሆነ ይገልጻል።

## 4.3 የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደት እና ጠቀሜታ መተንተን

ይህ ክፍል የጥናቱ አብይ ጉዳይ ሲሆን ከመስክ በተገኙ መረጃዎችና በክፍል ሁለት ቅኝት ስር በቀረቡ የምሁራን ሀሳቦች (ድርሳን) በመታገዝ የተተነተነበት ነው፡፡ በመሆኑም ትንተናውን በተገቢው መንገድ ለማስኬድ የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደት እና የሸክላ ውጤቶቹ ጠቀሜታ የሚሉ ንዑሳን ርዕሶችን በመስጠት የተተነተነ ሲሆን prown(1982) ያቀረባቸውን የመተንተኛ ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል ፡፡

### 4.3.1 የሸክላ ውጤቶች የአሰራር ሂደት

የሸክላ አፈር በማንኛውም የአለም ክፍል የሚገኝ በመሆኑ የሸክላ ስራ አለማቀፋዊ ክስተት ለመሆን በቅቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሸክላ ስራ በርካታ ሂደቶች ወይም ደረጃዎች ቅርጽ ማውጣት (Forming) ፣ መስጌጥ(decorating) ፣ እናማቃጠል (Firing) የሚባሉ መሆናቸውን Noble(1966,15) Copper (1981፣25) ፣ እና Bricks (1967፣12) ጠቁመዋል፡፡ ምሁራኖቹ የሸክላ ስራ ሂደቶችን በሶስት ክፍሎች ከፋፍለው ማቅረባቸው ይታወቃል፡፡ እንዲሁም አቶ ሀብታሙ እንግዳው (2001-67) የሸክላ ስራ ሂደቶች ወደ አምስት አሳድጎ እንደተነተነው በመጀመሪያ ደረጃ ባለሙያዎች ጥሬ እቃውን ሲያቀርቡ፤ ጥሬ እቃውን ለስራ ሲያዘጋጁ ፤ የተዘጋጀውን ጥሬ እቃ በመያዝ ስራ ሲጀምሩ፤ የማስጌጥ ስራ ሲያከናውኑ ፤ ያጌጠውን የደረቀውን ሸክላ በመተኮስ/ በማቃጠል የስራውን ሂደት ሲያጠናቅቁ በማለት ምደባ አካሂደኋል፡፡

ምሁራኖች የሸክላ ስራን በሶስት ከፍለው ያስቀመጡትን እና ሀብታሙ በአምስት ከፍሎ ያስቀመጣቸውን የአሰራር ሂደቶች በመከተል በዚህ ጥናት በሚከተለሁ መልኩ ለማየት ችያለሁ፡፡

**የሸክላ ስራ ሂደቶች ወይም ደረጃዎች**

1. ቁፋሮ ማካሄያድ
2. ቁሱን መስራት
3. ቅርጽ ማውጣት እና
4. ማቃጠል ናቸው፡፡

ባለሙያዎቹ የመጀመሪያውን ደረጃ ወደ ቁፋሮ መሄድ ለሸክላ ስራ የሚያገለግል አፈር በተለያየ ጊዜ ወደ ቤታቸው ያመጣሉ፡፡



**ምስል** 2 የሸክላ አፈር ቁፋሮ ላይ እያሉ

### 4.3.1.1 ቁፋሮ

ባለሙያዎቹ ነጩን አፈር ካመጡ ቡኋላ የተወሰነ እረፍት በመውሰድ ወይም በነጋታው ኮረት/ጥቁር አፈር በማምጣት ጉራ በሚባለው ቦታ በመሄድ አፈሩን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ወደ ቁፋሮ ቦታ በሚሄዱበት ጊዜ የሆድ የሆዳቸውን እያወጉ ለመንዝ ከሁለት እስከ አምስት ሰው በመሆን ተጠራርተው ይሄዳሉ፡፡ የሚጠራሩትም በተለያዩ ምክንያቶች ተሳንፈው እንዳይቀሩ ነው እንጂ የባለ ሙያዎቹ ቤትም ከወንዝ ዳርቻ ላይ ስለሚገኝ ከቤታቸው እስከ ወንዝ ከ30፡00 ደቂቃ እስከ 40፡00 ደቂቃ የእግር ጎዞ በመንዝ ይዘው ይመጣሉ፡፡

ጥሩዉን የሸክላ አፈር እንዴት መለየት ትችላላችሁ?

ሚስኩ አባዲጋ እንግዲህ ይህ አፈር ከድሮ ጀምሮ ከመሬት ነው የሚወጣው እራሳችንን ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን የምንሰራው በሱ ስለሆነ በትክክል እንለየዋለን፡፡

አይደለም እዚህ ሌላ ቦታ ሄደን እንዲህ አይነት አፈር ብናይ የሸክላ መስሪያ ነው ብለን መለየት እንችላለን፡፡ ለማድቀቅም የምንጠቀመው ለሸክላ ስራ የሚያስፈልገን ይህ የተለያየ ሶስት አይነት ከለር ያለው አፈር ነው፡፡ ነጭ አፈር፣ ጥቁር አፈር እና ዋልካ አፈር በመቀላቀል ነው የሚሰራው ካልሆነ አይጠነክርም፡፡ በመጨረሻ ለማስዋቢያ ቀዩን አፈር እንጠቀማለን፡፡

ደወል አፈር የሚባለው ቀይ መልክ ያለው አፈር ሲሆን ሸክላዎቹ ተሰርተው ከደረቁ በኋላ ከመተኮሳቸው/ ከመቃጠላቸው በፊት ውበት እንዲኖረው ይቀባል፡፡ (18/ 2011 ለሊሳ ቡላ)



**ምስል 3** የሸክላ አፈርን ይዘው ሲመለሱ

### 4.3.1.2 ቁሱን መስራት

ባለሙያዎቹ ጥሬ እቃዎቹን ከተለያዩ ቦታዎች ካመጡ በኋላ ቀጣይ ስራቸው የሚሆነው ጥሬ እቃዎቹን ለስራ ማዘጋጀት ሲሆን ይህም የሸክላ ስራው ሁለተኛ ደረጃ ሂደት ነው፡፡ ነጬን አፈር ከየዲ ወንዝ ዳር ቆፍረው ወደ ቤታቸው ከደረሱ በኋላ በኬሻ ተደርጎ በደንብ ይቀጠቀጣል፡፡ ምክንያቱም ይህ አፈር ከአሸዋው ጋር እንዲለይይ ነው፡፡ የተቀጠቀጠው አፈር መድቀቁ ከታወቀ በኋላ በወንፊት ይነፋል፡፡ ጥቁሩ የዋልካ አፈር ጉራ ከተባለው ቦታ ከመጣ በኋላ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ለቅመው ለመለየት እሱ ልክ እንደ ነጬ አፈር ተመቶ ይነፋል፡፡ ቆሻሻ ነገሮች በጥንቃቄ ይለቀሙና ንፁህ ከሆነ በኋላ Cardew9(1970፣9) እንደጠቆመው እኩል በእኩል ተቀላቅሎ በውሃ እየተቦካ አንድ ላይ ታሽቶ ለስራ ይዘጋጃል፡፡ ወ/ሮ አሊማ ጥሬ እቃዎች በምን ሁኔታ ለስራ እንደሚዘጋጅ የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ከቅዳሜ እና ከሰኞ ውጭ ያሉ ቀናቶች ከየዲ ወንዝ ዳር ያመጣነውን ነጬን አፈር ጉራ በመሄድ ጥቁሩን የዋልካ

አፈር እናመጣዋለን፡፡ ከቤት አምጥተን እንጠቀጥቀዋለን ከዚያም በወንፊት እንነፋዋለን፡፡ ከዚያ አፈሮቹን አብኩተን ስራ እንጀምራለን፡፡(18/2011 ለሊሳ ቡላ)



**ምስል** 4 ወ/ሮ አሊማ በወንፊት አሸዋዉን ከ አፈሩ ስትለይ

ደወል አፈር እንደ ነጩና ጥቁሩ ዋልካ አፈር ቀድሞ የሚዘጋጅ ሳይሆን ሸክላዎቹ ተሰርተው ከደረቁ በኋላ ከመተኮሳቸው /ከመቃጠላቸው በፊት መልካቸው ቀይ እንዲሆን በቀጭኑ በትናንሽ ድስት ወይም በሸክላ ስባሪ ካልሆነም በተገኘው እቃ ተበጥብጦ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በመሆኑም ደወል አፈሩን ለስራ ማዘጋጀት አድካሚ ያልሆነው የሸክላ ሰራ ሂደት ነው፡፡

## 4.3.1.3 ቅርጽ ማውጣት

ነጭ የየዲ አፈር እና ጥቁር ዋልካ አፈር በሚገባ ተቦክቶ ከተዘጋጀ በኋላ የሸክላ ስራው ይጀመራል፡፡ ጥሬ እቃው ከያለበት ተፈልጎ መጥቶ ለስራ ዝግጁ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እንደ ባለ ሙያዋ የቀድሞ ልምዷን መሰረት በማድረግ የምትችለውን የሸክላ ስራ አይነት

መስራት ትጀምራለች፡፡ ይህም የሸክላ ስራ ሁለተኛው ሂደት ነው፡፡ ለሁሉም የሸክላ ውጤቶች በባለሙያዎቹ የሚዘጋጀው ጭቃ አንድ አይነት ነው፡፡

ይህ ጭቃ ለምጣድ፣ ይሄኛው ደግሞ ለጋን ወይም ለድስት ተብሎ አይደለም የሚዘጋጀው፡፡ አንዲት የሸክላ ስራ ባለሙያ አንዴ ባዘጋጀችው ጥሬ እቃ ሁሉንም የሸክላ አይነቶች መስራት ትችላለች፡፡ ነገር ግን በመስክ ቆይታዋ እንዳስተዋለቹ ባለሙያዎቹ በልጅነታቸው የለመዱትን አንድ ወይም ሁለት አይነት የሸክላ ውጤቶችን በመስራት ብቻ የተወሰኑ ናቸው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በልጅነታቸው ባገኙት ልምድ ስለሚወሰኑና ሁሉንም እቃዎች ለመስራት አቅም ማጣታቸው ነው፡፡

ሀ/ቢያ አባ መጋል ሌሎች የሸክላ አይነቶችን ለምን አትሰሩም ? በማለት ጠየቀቻቸው ያማ ከልምድ ነው፡፡ እናቴ የምትሰራው ምጣድ፣እሳት ማንደጃና እጣን ማጨሻዎችን ነው፡፡ እኔም ይህንኑ ለምጄ ቀረሁ፡፡ ያው ከልምድ ነው ጥናት ብናደርግ መስራት እንችል ነበር አሏት፡፡

ሁሉም የሸክላ አይነቶች በቀላል እና በተመሳሳይ የአሰራር ሂደት የሚያልፉ ናቸው፡፡ ሁሉም የሸክላ አይነቶች የሚሰሩት በእጅ ሲሆን ጣቶች ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ባለሙያዎቹ ሸክላዎቹን በእጃቸው እና በአከባቢያቸው በቀላሉ ከሚያገኟቸው መስሪያ ቁሳቁሶች (ስንጥር፣ አሎሎ፣ ቢላዋ፣ የሸክላ ስባሪ፣ ቆረቆንዳ፣ ላስቲክ፣ እንጨት ወዘተ.) በመታገዝ ይሰሯቸዋል፡፡

የሁሉም የሸክላ ውጤቶች ስራ የሚጀምረው ከታችኛው ክፍላቸው ነው፡፡ በባለሙያዎቹ አባባል ሁሉም ስራ ከቂጥ ይጀምራል፡፡ የሸክላዎቹ አካል/ቅርጽ ከሰው አካል መጠሪያ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ቂጥ፣ ሆድ፣ አንገት እና ጆሮ የሚሉ መጠሪያዎች አሏቸው፡፡

ከምጣድ ውጭ ሁሉም ሸክላዎች የሚጀመሩበት ከጣውላ የተሰራ መቀመጫ ያላቸው ሲሆን በዚህ ማስቀመጫ ላይ ሊሰራ የታሰበው የሸክላ አይነት ጭቃውን ጣውላው ላይ በማስቀመጥ እያሽከረከሩ ይሰራል፡፡ ለስራ የተዘጋጀው ጭቃ በስብርባሪ ጣውላ ላይ ወይም ኬሻ ላይ በማስቀመጥ ወደ ጥላ ቦታ በመውሰድ ያስቀምጡታል፡፡

አንድ የሸክላ ቁስ ስራው ከቂጡ ከተጀመረ በኋላ የተወሰነ አካሉ ከፍ እንዳለ ለጸሃይ ይሰጣል፡፡ በመጠኑ ደረቅ ሲል የቀረው ክፍል ጭቃው እየተደበለበለ ይቀጠላል፡፡ ከዚያም በውሃላ እየተራሰ ከቀድሞ አካሉ ጋር እኩል እስኪሆን ድረስ ይለሰለሳል፡፡ ከዛም ለጸሃይ ይሰጣል፡፡ የተጀመረው እስኪደርቅ ሌላ አዲስ ይጀመራል፡፡ ሲደርቅ ይቃጠልል፡፡ አሁንም ሌላ ይጀመራል፡፡ በዚህ

አይነት ሁኔታ ባለሙያዎቹ በአንድ ጊዜ እስከ አራት የሚደርሱ እቃዎችን እያፈራረቁ መስራት ይችላል፡፡



**ምስል 5** እሳት ማንደጃ ስሰራ



**ምስል 6** እጣን ማጨሻ ስሰራ

Prown (1982፣2) እንደጠቆመው ቁሶች በተሰሩበት ዘዴ ወይም ባገልግሎታቸው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ Georges እና Jones በበኩላቸው የተለያዩ የመመደቢያ መስፈርቶች መኖራቸውን ጠቁመው የቁሶቹን ባለቤት ቁሶቹን በመደቡበት መስፈርት መመደብ እንደሚቻልም ገልጸዋል፡፡ በመሆኑ የለሊሳ ቡላ የሸክላ ስራ ባለሙያዎቹ የሸክላ ውጤቶችን prown (1982፣2) ከጠቆማቸው መመደቢያ መስፈርቶች በአንዱ ቁሶቹ በተሰሩበት ዘዴ (methods of fabrication ) መሰረት በማድረግ የቁስ ፣ የቁም እቃና የቁጭታ እቃ በማለት ይመድቧቸዋል፡፡

ይህም ከምሁሩ የመመደብያ መስፈርቶች ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ የቁም እቃ ማለት ባለሙያዎቹ ቁመዉ ሊሰሯቸዉ የሚችሉ ገንቦ፣ እንስራ፣የእንጀራ መጋገርያ ምጣድ ፣ጋን ሲሆኑ ፤የቁጭታ እቃ ቁጭ ተብሎ የሚሰሩ ፣ድስት ፣እጣን ማጨሻ፣ እሳት ማንደጃ ወዘተ ናቸዉ ፡፡ ይህንን የባለሙያ መመደብያ መስፈርት መሰረት በማድረግ ከቁም እቃ የምጣድን (Eelee)፣ ከቁጭታ እቃ ደግሞ እሳት ማንደጃ (Eelee Ibiddaa) አሰራርን ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ የእነዚህ ሁለት የሸክላ ዉጤቶች አሰራር ሂደት ባለሙያዎቹ ሁሉንም የሸክላ ዉጤቶች ሲሰሩ ተመሳሳይ በመሆኑ ነዉ ፡፡



**ምስል** 7 በቁም ምጣድ ሲሰራ

የጥሬ እቃዉን ሂደት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ  ለምጣድ መስርያ የተዘጋጀዉን ጭቃ ወደ ጥላ ስር በመዉሰድ አመድ የተበተነበት መሬት ላይ በማድረግ ባለሙያዋ እየተዟዟረች ትሰራዋለች ፡፡

ወ/ሮ አሊማ እኔ “ከምሰራቸዉ ስራዎች የእንጀራ መጋገርያ ምጣድ አድካሚዉ ነዉ ፡፡ እየሰፋ ሲሄድ እጅሽ አይደርስም እና ትክክለኛዉን ቅርጽ ለማስያዝ ወደሚስተካከልበት አብረን መዞር አለብን ካልሆነ ይጣመማል እና በተከታታይ ከሁለት በላይ ምጣድ ስንሰራ ወገብ ያሳምማል”፡፡(8/8/2011 ለሊሳ ቡላ )

ምጣድ(Eelee) ለመስራት በመጀመርያ ኑጹህ እና የተስተካከለለ ቦታ ይመረጣል ፡፡ በዚህ በተመረጠዉ ንጹህ መሬት ላይ አመድ ይነሰነሳል ፡፡ ከዛላይ የምጣድ ስራዉ ይጀመራል ፡፡ ከዝያም ባለሙያዋ ጭቃዉን እያነሳች በመዳፏ እያስተካከለች ስራዉን ትቀጥላለች ምጣዱ

ተሰርቶ ካለቀ ቡኃላ በጸሃይ እንዲደርቅ ይደረጋል ። ከደረቀ ቡኃላ ቂጡ በቢላዋ (senxi) ይፋቀፍቁታል።

ካንዚ ማመሳኒ በምጣድ ስራ የታወቀች ባለሙያ ነች ። የስዋ ምጣድ ከአካባቢዉ የተመረጠና ጥሩ እየተባለ ይነገርለታል ። “ያዉ የስራ ትንሽ የለዉም ከምንሰራዉ ስራ የምጣድ ስራ ያደክማል። ለመቶከስም ብዙ እንጨት ይፈልጋል ከስሩ የተለያዩ እንስራዎችን(uuroo) አስቀምጠን በነሱ ላይ አዙረን ስለምንተኩስ በብዛት ረዥም ጊዜ ወስደን በደንብ ለማድረቅ እንዳይ ጠፋ ማንደድ አለብን ። ከእሳት ሲወጣ የተተኮሰዉ ምጣድ ቀይ መልክ ይዞ ይወጣል። ካላይ የቀረበዉ ከቁም እቃ የተመደበዉን የምጣድ የአሰራር ሂደትን የሚያሳይ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ከቁጭታ እቃ የተመደበዉን የእጣን ማጨሻ የአሰራር ሂደትን ለማሳየት ሞክራለዉ ።

ቀደም ስል ለመጠቆም እንደተሞከረዉ የሸክላ ስራ በተጀመረበት ለሸክላ መስርያነት የጭቃ ማስቀመጫ ላይ የማንደጃዉ ስራ ይጀመራል። ለማንደጃ እና መሰሎቹ መስርያነት የተዘጋጀዉን ጭቃ ባለሙያዎቹ ለመስርያነት ያዘጋጁት ጣዉላ ላይ ጠጠሮችን ጨምሮ ለማዟዟር እንዲመቻቸዉ ሰፋ ያለ የሸክላ ስባሪ በማድረግ ጭቃዉን ያደርጉበታል ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ስራዉን ሲጀምሩ በቁጭታ እያዞሩ ለመስራት እንዲያመቻቸዉ በመፈለግ ነዉ። ምድጃዉን ሲሰሩ ማሀሉን በአጃቸዉ እያጎረገዱት ያሰፉታል። ሆዱን እና እጅታዉን ሰርተዉ በመጨረሻም እንዲያሟልጭላቸዉ ዉሃ እያራሱ እንዳይደርቅ እያደርጉ ሰርተዉ ስያበቁ ጸሀይ ላይ ሆኖ ለአንድቀን እንዲደርቅ ይደረጋል ከደረቀ ቡኂላ በቃጣዩ ቀን እግሩን ይሰሩበት እና መልሰዉ ያደርቁታል በመጨረሻ እግሩን እና ሆዱን በዉሃ እያራሱ ካመሳሰሉ በኂላ ለሶስት ቀን እንዲደርቅ ተደርጎ በመጨረሻም ይተኩሱታል።



**ምስል** 8 በቁጭታ እሳት ማንደጃ ሲሰራ

ሀ/ቢያ አባመጋል "ከትላልቅ እቃዎች ማንደጃን መስራት ይቀላል ገብያ ባለዉ ሳዓት ገን ፣እንስራ ከፍያሉ ምጣዶችን እሰራለዉ ። እነሱን ለመስራት ማጎንበስ አለብሽ ይህ ደግሞ ለወገብ ህመም ያጋልጣል ። ማንደጃዉን ስሰራ ግን ሁለትም ለስራ ሶስት ቁጭ ብዬ ስለ ምሰራ ብዙም ኤደክምም" ። እስካሁን ለማሳየት እንደሞከርኩት ባለሙያዎቹ በመደቡበት ምደባ መሰረት ከቁም እቃ የምጣድን አሰራር ከቁጭታ እቃ ደግሞ የእሳት ማንደጃን የአሰራር ሂደትን በምሳሌ ለማስቀመጥ ሞክራለች።

### 4.3.1.4 ማቃጠል/መቶከስ

መቶኮስ ወይም ማቃጠል የሸክላ ስራ የመጨረሻ ህደት ሲሆን የደረቁት ሸክላዎች ጥንካሬ የሚያገኙትና ጥቅም ላይ ለማዋል ዝግጁ የሚሆኑት ከተተኮሱ ወይንም ከተቃጠሉ በኋላ ነዉ፡፡ Cardew(1970:11)እንደጠቆመዉ አፍሪካ ዉስጥ ሸክላዎች ከመተከሳቸዉ ወይንም ከመቃጠላቸዉ በፊት በተለያዩ ደረቅ ሳሮች ወይም ኩበቶች የማጠን(preheating) ስራ ይካሄዳል፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ የደረቁ የሚመስሉት ሸክላዎች የተወሰነ እርጥበት ስለሚኖራቸዉ አርጥበቱ በመጠነኛ ሙቀት ካልተወገደ ከፍተኛ ሙቀት ስያገኛቸዉ ሸክላዎቹ እንዳይሰባበሩ ለመከላከል ነዉ፡፡

በመስክ ቆይታዋ ለመመልከት እንደቻልኩት  የለሊሳ ቡላ የሸክላ በለሙያዎች ሸክላዎቹን ከመተኮሳቸዉ በፊት በተሰባበሩ እንስራዎች ላይ ጭዶ በደንብ በመነስነስ ከማንደዳቸዉ በፊት ለግማሽ ሰአታት ያህል በጪስ በደንብ እንዲታጠኑ ከተደረገ ቡኋላ በስተመጨረሻ በምጣዱ የላይኛዉ ክፍል ላይ የተለያዩ  የእንጨት ስብርባሪዎች ፣ ጭድ እና ገለባ በመጨመር ደርቆ የተዘጋጁትን ሸክላዎች እንዲቃጠሉ / እንደተኮሱ ያደርጓቸዋል፡፡



**ምስል** 9 ምጣድ ሰቃጠል/ሲተኮስ



**ምስል** 10 ምጣድ ከተቃጠሌ በኋላ

ከእሳት ማንደጃ እና ከማጬሻ በስተቀር ሁሉም የሸክላ አይነቶች  ተተኩሶ ከወጡ ቡኋላ የታችኛዉ ክፍላቸዉን እበት ይቀባሉ፡፡ መረጃ አቃባዮቹ እንደ ጠቆሙኝ ከሆነ እበት የሚቀባበት

ዋና ምክንያት ሸክላዎቹ የታችኛዉ ክፍላቸዉ ሲወፍር በቢላዋ (seenxii) ይፈቀፍቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጭረት ያወጣሉ ፤ጭረቱን ያዩ ገበያተኞች ሰባራ ነዉ እያሉ ስለማይገዙን ለመሸፈን ሳይሆን “ይህን ማድረግ ከድሮም ያለ ልምድ ነዉ“ በማለት የገልፃሉ፡፡

ወ/ሮ አልፊያ አ/ድልቢ የሚትባል የሸክላ ባለሙያ የሸክላ ቅጡ እበት የሚቀባበት ምክንያት ስትገልፅ "በቢላዋ(seenxii) ስፈገፈግ የሻከረዉ ቂጡ እንዲለሰልስና እንዲስተካከል ነዉ የምንቀባዉ፡፡ ይህም ከዱሮ ጀምሮ ያለ ልምድ ነዉ፡፡" በማለት ነዉ፡፡ በለላ በኩል ቡሰታኒ መሃመድሳኒ የተባለች ወጣት ባለሙያ የሸክላ ቂጡ እበት የሚቀባዉ በብዛት ስለሚሰሩ ቁርጥማት (Nyaataa) እንዳያማቸዉ መሆኑን ገልፃለች፡፡ "እጃችንና ወገባችን ቁርጥማት(Nyaataa) እንዳያመን ነዉ፡፡" ብላለች፡፡ (08/08/11 ለሊሳቡላ)

ባጠቃላይ እነዚህ የሸክላ ባለሙያዎች የሸክላ ቂጡ እበት የሚቀባዉ ለምንድነዉ? የሚለዉን ጥያቄ አንስታላቸዉ ከዱሮ የቆዬ ልምድ መሆኑን ተናግራዋል፡፡ "ዱሮ እናቶቻችንም እበት ቀብቶ ሲሸጡ ስላየን እኛም እንደዛ እናደርጋለን ፤ለቁርጥማት መድሓኒትነቱም የታወቀ ነዉ ብለዉኛል፡፡

## 4.3.2 የሸክላ ቁሶች ጠቀሜታ

### 4.3.2.1 ማህበራዊ ጠቀሜታ

የሸክላ ባለሙያዎች በተለያየ መጠንና ቅርፅ ቁሶችን ሲሰሩ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ይሰጣሉ፡፡ የቁሶቹን የአሰራር ጥበብና ያዘሉትን ሃሳብ በአግባቡ ለመገንዘብ ደግሞ በየዘውጉ ማደራጀት ተገቢ ነው፡፡ እኔም ከቁሶቹ ባለቤቶች ጋር በመሆን በሚከተለው መንገድ ከፍለናቸዋል፡፡

### 4.3.2.2 ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች

የሸክላ ባለሙያዎች ለተለያዩ አገልግልት የሚውሉ ቁሶችን ይሰራሉ፡፡ ፈሳሽ ነገሮችን ለማዘጋጃትና ለማቅረቢያነት ከሚውሉ ቁሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ እነሱም፡- እንስራ፣ጀበናና ገንቦ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ባለሙያዎቹ እነዚህን ቁሶች በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ያደርሳሉ፡፡

### 4.3.2.3 ምግብ ለማዘጋጃነትና ለማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች

በሸክላ ባለሙያዎች ከሚሰሩ ቁሶች መካከል ለምግብ ማዘጋጃና ማቅረቢያ የሚሆኑ ቁሶች አሉ፡፡ እነሱም፡-ምጣድና ሸክላ ድስት የሚባሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ቁሶቹ የተለያየ መጠንና ቅርፅ ያላቸው በመሆናቸው መጠኑ ብዙ ወይም ትንሽ የሆነ ምግብ ለማዘጋጃና ለማቅረቢያ የሚውሉ ቁሶች ናቸው፡፡

### 4.3.2.4 የሸክላ ቁሶች ባህላዊ አገልግሎት

የሸክላ ቁሶች ለተጠቃሚው ማህበረሰቡ የእለት ከእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የማህበረሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤን፣ ወግ፣ ፍልስፍናን፣ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማሳወቅ በኩል አበርክቶ አላቸው፡፡ በዚህ መነሻ እሳቤ የሸክላ ቁሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ትዕምርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.3.2.5 ሀብታምነትን የሚያመለክቱ የሸክላ ቁሶች

በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ከሚሰጡት አገልግልት አንፃር የተገልጋዮቹን የሀብት መጠን መጠቆም አንዱ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሀብታም በሚባሉ ሰዎች ቤት ከሚገኙ ቁሶች መካከል የሚከተለት ይገኙበታል፡፡ እነሱም፡- ጋንና እንስራ ናቸው፡፡

### 4.3.2.6 ድህነትን የሚያመላክቱ የሸክላ ቁሶች

እነዚህ ቁሶች አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት የሀብት መጠናቸው አነስተኛ በሆኑ የማህበረሰብ ክፍል ቤት ውስጥ ነው፡፡ እነሱም፡- ምጣድና እሳት ማንደጃ ናቸዉ፡፡

### 4.3.2.7 ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ

የሸክላ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል ያቀርባሉ፡፡ ቁሶቹን ለሚያበጇቸው ባለሙያዎች እንድሁም ለተጠቃሚው የማህበረሰብ ክፍል አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ለባለሙያዎቹ የሰሩትን ቁሶች በመሸጥ የራሳቸውንና

ቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመምራት የሚያግዝ ገንዘብ ያገኙበታል፡፡ ለቁሶቹ ተጠቃሚዎች ደግሞ በሚፈልጉት መጠንና ቅርፅ ቁሶቹን በትዕዛዝ አሰርተው መጠቀም መቻላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ የሸክላ ቁሶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስመልከት ወ/ሮ ኣልፊያ አ/ዲልቢ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡ ‹‹እኔ ሁለት ወንድና ሶስት ሴት ልጆቼን የማሳድገው ሸክላ በመሸጥ ነው፡፡ ሽያጩ ርካሽ ቢሆንም ያው እሰራለሁ፡፡ ያው የሸክላ ቁሶቹን በየሳምንቱ ባልሸጥ ልጆቼን ምን አቃምሳቸው ነበር፡፡ እንኳን ሳይሸጥ ተሸጦም ጠብ የሚል ብር አልተገኝም፡፡" (08/08/2011 ለሊሳ ቡላ)

## 4.4 ጾታዊ ተሳትፎ

በአፍሪካ ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ከሸክላ ስራ ጋር ተያያዥ የሆኑ ባርካታ ጥናቶችን ያከሄዱ በርካታ አጥኚዎች እንደ ጠቆሙት የሸክላ ስራ በአብዛኛዉ የሚከወነዉ በሴቶች ነዉ፡፡ ሴቶች ለሸክላ ስራ የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ከማቅረብ ጀምሮ ሸክላዉን ሰርተዉ ገብያ ወስዶ እስከ መሸጥ ባለዉ ሂደት ዉስጥ ከፍተኛዉን ድርሻ ይወስዳሉ ፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ቦታ ላይ በተወሰነ መልኩ ከወንዶች መጠነኛ እገዛ ያገኛሉ፡፡

በለሊሳ ቡላ ቀበሌ ስራዉን የሚከዉኑት ሴቶች ናቸዉ፡፡ ለሸክላ ስራ የሚያገለግለዉን አፈር መቆፈር ፤በተለያዩ መምቻዎች ቀጥቅጠዉ የማድቀቅ ፣ወደ የቤታቸዉ ተሸክሞ ማምጣት፣ ቤት ከደረሰ ባኋላም ጥሬ እቃዉን ለማድቀቅ መፍጨት፣የተፈጨዉን አፈር ከዉሃ ጋር ለማዋሀድ፣ በእገራቸዉ ማቡኳት፣ ለመስራት ማዘጋጀት፣ የተለያዩ ቅርጾችን ማዉጣት፣ ማድረቅ ፣ ማቃጠል ፣ወደገብያ ወስዶ መሸጥ እነኚህ ሁሉ ሂደቶች በሴቶች የሚከወኑ ናቸዉ፡፡

በሸክላ ስራ ዉስጥ የወንዶች ድርሻ ምድነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ ብዙዎቹ ባለሞያዎች በሳቅና በአግርሞት "እነሱ ደግሞ ምን ድርሻ አለቸዉ? ምንም ድርሻ የላቸዉም እንዲሰሩም አንፈቅድም፡፡ ነገር ግን በጣም ከቸገረን እና ጊዜ ካጠረን አልፎ አለፎ እንጨት በማምጣት ፣ ጭድ በመሰብሰብ እና ዉሃን በመቅዳት ካልሆነ ከአፈር ጋራ የተያያዙትን ነገሮች በምንም ሁኔታ እዲነኩ አይፈቀድም፡፡ ወንዶች በእርሻ ስራ እንጂ በእኛ ስራ ምን ያገባቸዋል" ባይ ናቸዉ፡፡ መልሱ ባለመስራታቸዉ ምንም ቅሬታ ሳያሰሙ የወንዶች ስራ አይደለም ነዉ ፡፡

ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገበት ቀበሌ ላይ የሸክላ ስራ የሚከውኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወንበት ምክንያት በተመለከተ ወ/ሮ አሊማ አ/ባ ዱራ እንዲህ ገልፀውታል፡፡ "በባህላችን ወንድ የሴትን ስራ አይሰራም ነውር ነው፡፡ ሸክላ የምናበጀዉ ሴቶች ነን ፡፡ ምክንያቱም ወንዶች ከልጅነቴ አንስቼ እስከ ማዉቀዉ ድረስ በእርሻና በመሳሰሉት ነገሮች በመሳተፍ ያግዙናል እንጂ ሸክላ ሲሰሩ አይቼ አላዉቅም""፡፡ (7/7/2011 ለሊሳ ቡላ)

ጣሀ አ/ጊሳ ፣ማህመድ አ/ጊሳ እና ሱልጣን አባ ተማም የተባሉ የሸክላ ሰራተኛ ወይም ቤተሰቦች ጋር በተካሄደዉ ዉይይት በለሊሳ ቡላ "የሸክላ ስራ ሙሉ በሙሉ የሚከናወነዉ በሴቶች መሆኑን እና ወንድ ቢሰራ በሴቶቹ በኩል የሚናቅ መሆኑን በሌላ መልኩ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች አብዛኛዎቹ በቤት ውስጥ ለምግብ፣መጠጥ ማዘጋጃነትና ማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል ደግሞ ምግብና መጠጥ የማዘጋጀትና ማቅረብ ተግባር በአብዛኛው የሚተገበረው በሴቶች አማካኝነት መሆኑ ሌላኛው ተጠቃሽ ምክንያት እንደሆነ እና እኛ የእርሻ ስራን እናከናዉናለን ነገር ግን አይሞላልንም ፡፡ ከነገሮች ያለመመቻቸት ሁኔታ ነዉ እንጂ ቤተሰቦቻችን ስራዉን ቢያቆሙ ደስ ይለናል በማለት አሳባቸዉን አስፍረዋል ፡፡



**ምስል 11** ጣሀ አ/ጊሳ ቃለመጠይቅ ስደረግለት

ከዚህም በተጨማሪ ቤተሰቦቻችን የሸክላውን አፈር ከመቆፈሩ ተግባር በስተቀር ብዙ ጉልበት የሚጠይቅ ተግባር ባለመሆኑና ፀሃይ ሳይመታቸው ስለሚሰሩ ተመራጭ ያደርጉታል። የሸክላ ስራ ከጭቃ ማድበልበል ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእጅ ቅልጥፍና የሚጠይቅና ጌጣጌጥ የሚደረግበት ስራ በመሆኑ ምርጫችን ነው ይላሉ። በዚህ መነሻ ምክንያት ሴቶች እናታቸው የምትሰራውን ቁስ እየተመለከቱ እንደ እድሜአቸውና ግንዛቤአቸው መጠን ይሰራሉ። ወንዶች ግን የሸክላ ሰራ እንዲለምዱ አይደረጉም ይልቁንም አባቶቻቸው የሚሰሩትን ተግባር እንዱለምዱ ይደረጋል'።

አ/ተማም አ/ቡልጉ የ61 አመት የእድሜ ባለፀጋና ከሸክላ ባለሙያዎች ዉጭ የቀበሌ ሊቀመንበር ሲሆኑ ባህላዊ የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወን ተግባር ነው። የሸክላ ስራ በሴቶች ብቻ የሚሰራው ለምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ የመለሱት መልስ የሚከተለዉን የመስላል።

"Uummata naannoo keessatti dalagaa dhalaa fi dhiiraa jedhamee qoodamni jira. Hojii suphee irratti ga'ee dubartootaa olaanaa sababni ta'eef meeshaaleen ogummaa kanaan hojjetaman hojii mana keessaa wajjin waan wal qabatuufi. Meeshaan suphee yeroo hojjetamu biyyoo gingilchuu, daakuu fi bukeessuu barbaada. Haaluma wal fakkaatuun dubartoonni yeroo biddeena hojjetanu daakuu madhaanii gingilchuu, daakuu fi bukeessuu barbaachisa. Hojiin lamaan kun wal fakkeenya qabu. Daakuu fi bukeessuun akka aadaa uummata naannootti kan hojjetamu gennootaani."

"በማህበረሰቡ ውስጥ የሴትና የወንድ ተግባር የሚል የስራ ክፍፍል አለ ። በሸክላ ስራ ላይ የሴቶች ሚና ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ስለሚያያዙ ነው። የሸክላ ቁስ ሲሰራ አፈር ማንጓለል መፍጨትና ማቡካት የሚባሉ ሂደቶች አሉት። በተመሳሳይ ሴቶች የእንጀራ እህል ለማዘጋጀት እህል ማንጓለል፣መፍጨትና ማቡካት የሚባሉ ሂደቶችን ማለፍ ይጠይቃል። በሁለቱ ተግባራት መካከል ተመሳሳይነት ይታይበታል። መፍጨትና ማቡካት በማህበረሰቡ ባህል ሴቶች የሚተገብሩት ተግባር ስለሆነ ነው"።(7/7/20011 ለሊሳ ቡላ)

እንግዲህ ጠቅለል ባለ መልኩ እስካሁን ከቀረቡት የወንዶች እና የሴቶች መረጃ አቀባይዎች ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለዉ በለሊሳ ቡላ አከባቢ የሸክላ ስራ የሚከወነዉ ሙሉ በሙሉ በሴቶች መሆኑን ነዉ፡፡

በሌላ መልኩ በባለሙያዎቹ የሚሰሩ ቁሶች አብዛኛዎቹ በቤት ውስጥ ለምግብ፣መጠጥ ማዘጋጃነትና ማቅረቢያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል ደግሞ ምግብና መጠጥ የማዘጋጀትና ማቅረብ ተግባር በአብዛኛው የሚተገበረው በሴቶች አማካኝነት መሆኑ ሌለኛው ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሸክላውን አፈር ከመቆፈሩ ተግባር በስተቀር ብዙ ጉልበት የሚጠይቅ ተግባር ባለመሆኑና ፀሃይ ሳይመታቸው ስለሚሰሩ ተመራጭ ያደርጉታል፡፡ የሸክላ ስራ ከጭቃ ማድቦልቦል ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእጅ ፍጥነትን የሚጠይቅና ጌጣጌጥ

የሚደረግበት ስራ በመሆኑ ምርጫችን ነው ይላሉ፡፡ በዚህ መነሻ ምክንያት ሴቶች እናታቸው የምትሰራውን ቁስ እየተመለከቱ እንደ እድሜአቸውና ግንዛቤአቸው መጠን ይሰራሉ፡፡ ወንድች ግን የሸክላ አሰራርን እንዲለምዱ አይደረጉም ይልቁንም አባቶቻቸው የሚሰሩትን ተግባር እንዲለምዱ ይደረጋል፡፡

## 4.5 የሸክላ ሰራተኞቹ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ ያጋጠሚቸዉ ችግሮች

በዚህ ንዑስ ክፍል የሸክላ ሰራተኞቹ/ባለሙያዎቹ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ ያጋጠሚቸዉ ችግሮች ምን ምን እንደ ሆኑ ይዳሰሳሉ፡፡ አጥኚዋ በመስክ ቆይታዋ ከባለሙያዎቹ ጋር ባካሄደችዉ ቃለመጠይቅ እና እሷም በማየት እንዳረጋገጠችዉ ባለሙያዎቹ በግብርና እና በሸክላ ስራ የተሰማሩ ቢሆንም የኑሮአቸዉ ሁኔታ በጣም ዝቅ ያለ ነዉ ፡፡እንዲሁም በአከባቢያቸዉ በግብርና ብቻ የሚተዳደሩ ሰዎች ከሸክላ ሰራተኞች የተሸለ ኑሮ እንደሚኖሩ ለማረጋገጥ ችላለች፡፡

በመሆኑም ባለ ሙያዎቹ በሙያቸዉ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ችግር ከፈጠሩባቸዉ ጉዳዮዎች በመጀመርያ የማህበረሰቡ አሉታዊ አመለካከት፣ለቁሶቹ መስርያ የሚያገለግሉትን የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

ስለ ኢትዮጵያ የሸክላ ስራ ታሪክ በሚያነሳዉ ክፍል ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንረዳዉ ሀገረሰባዊ እጅስራ ባለሙያዎቹ በተለይም የሸክላና የብረታብረት ሰራተኞች የተለየ መንፈሳዊ ሀይል (Special spiritual power) ያላቸዉ ተደርገዉ እደሚቆጠሩ በርካታ ምሁራን መጠቆማቸዉ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ባለ ሙያዎቹ ባለሙያ ባልሆኑ ማህበረሰቦች እደሚፈሩ ፣እንደሚገለሉና የተለያየ አጓጉል ስሞች እደሚሰጣቸዉ ግልጽ ነዉ ፡፡ በአፍሪካ ዉስጥ የእጅ ባለሙያዎች ለማህበረሰቡ የእለት ተእለት ህይወት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ሰርተዉ ቢያቀርቡም ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹና ለሙያዉ ያለዉ አሉታዊ አመለካከት የጠነከረ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በለሊሳ ቡላ አከባቢ ያሉ የሸክላ ባለሙያዎች ከሙያቸዉ ጋራ ተያይዘዉ ሸክላ በማይሰሩ ማህበረሰቦች ዘንድ በጥሩ እይታ የሚታዩ አይደለም ፡፡ ሸክላ የማይሰራዉ ማህበረሰብ ባለሙያዎቹን "አናሳ ፣ ቡዳ" የሚለዉን መጠርያ በመስጠት ከፍተኛ የሆነ ስነ ልቦናዊ ተጽኖ ያሳድርባቸዋል ፡፡ በዚህ የተነሳም ባለሙያዎቹ ሸክላዉን ከማይሰራዉ ማህበረሰብ እራሳቸዉን አግልለዉ የግል ህይወታቸዉን ይመራሉ ፡፡ ጋብቻን የሚፈጽሙትም እደነሱ ሰራተኛ ከሆነዉ ወገን ሲሆን አንድ ሁለት የመቀላቀል ነገር እዳለ በጥናቱ የታየ ነዉ፡፡

## 4.6 የማህበረሰቡ አሉታዊ አመለካከት

በለሊሳ ቡላ አካባቢ ያሉ የሸክላ ባለሙያዎች ከሙያቸዉ ጋራ ተያይዘዉ ሸክላ በማይሰራ ማህበረሰብ ዘንድ በበጎ አመለካከት አይታዩም ሸክላ የማይሰራ ማህበረሰብ" ሰዉ ይበላሉ ቡዳ ናቸዉ" በማለት ስነልቦናዊ ጫና አሳድሮባቸዋል፡፡ በዚም የተነሳ ባለሙያዎቹ እራሳቸዉን ከማይሰራዉ ማህበረሰብ አግልለዉ እንደ ሁኔታዉ ከራሰቸዉ ቡድን ጋር የየግላቸዉን ኑሮ ይኖራሉ ፡፡ በአብዛኛዉ ጋብቻን የሚፈጽሙት እደነሱ ሰራተኛ ከሆነ ወገን እንጂ ሰራተኛ ካልሆኑት ጋር አይደለም ፡፡ ነገር ግን ከሸክላ ባለሙያዎች አልፎ አልፎ የተገኘዉ መረጃ ሰራተኛ ካልሆኑት ጋር በጋብቻ መቀላቀል እንደተጀመረ የተገኘዉ መረጃ ያስረዳል፡፡

ወይዘሮ ፋጡማ አባ ተማም 40 አመትዋ ሲሆን የሶስት ልጆች እናት ነች፡፡ ከሸክላዉ ሰሪ ማህበረሰብ አንዷ ስትሆን የአካባቢዉ ማህበረሰብ በሙያቸዉ ምክንያት የሚሰጣቸዉን አሉባልታ እንዲሁም ጋብቻን በተመለከተ የሚከተለዉን ሀሳብ አቅርባለች፡፡

“Nuti nama. Akkuma argitu isinirraa maaltu adda nu baase? Haa ta’u malee hojii suphee kana waan hojjennuuf qofa uummatni naannoo ilaachaa fi maqaa gaarii nuuf hin qabu. Yeroon baradhu mana barumsaattis ta’e bakka gabaa fi mana wofcootti yeroo hiryoota koo waliin wal arginu nu yeellaasisu. Yoo waa jenneen wanti jarri nuun jedhan “budaa nama nyaatu” jedhanii waan ta”eef nutis kana waan beeknuuf yoo waan fedhe jedhan dhaga’aatuma akka waan hin dhaga”inii bira dabarra. Fuudhaaf heeruma ilaalchisee duraan jarris uummata gurguddaa isaanii wajjin raawwatu. Amma garuu wal makuun jalqabameera. Ijoolleen lama fedhii isaaniitiin wal fuudhanii ijoollee godhatanii jiraataa jiru maal ta’an. Dhuguma utuu nama nyaanna ta’ee maatiin sun maalif hin dhumne? Kanumallee ilaalanii nu hin dhiifne tuffiin isaanii sanuma.”

“ሰዉ ነን። እየዉ ከናንተ በምን ተለየን? ነገር ግን ይህን ሽክላ በመስራታችን ብቻ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ለኛ ጥሩ አመለካከት ና ጥሩ ስም የላቸዉም:: በምማርበት ሳዓት በትምህርት ቤትም ፣ በገብያም ሆነ በወፍጮ ቤት ስንገናኝ ጓደኞቼ ያሽማቅቁናል። የሆነ ነገር ብንናገራቸዉ የሚሰድቡን ‘’ቡዳ፣ ሰዉ በሊታ’’ በማለት ስለሆነ እኛም ይህን ስለምናዉቅ ምንም ቢሉን እየሰማን እንዳልሰማን እናልፋቸዋለን።ጋብቻን አስመልክቶ ከዚህን በፊት እነሱም ከራሳቸዉ ከትላልቁ ማህበረሰብ ጋር ነበር የሚፈጽሙት። አዉን መቀላቀል ጀምረናል። ሁለት ልጆች በግላቸዉ/በፍቃደቸዉ ተገብተዋል እና ምን ተፈጠረ እይዉ ተዋልደዉ እየኖሩ ነዉ። እዉነት ሰዉ የምንበላ ቢሆን እስካሁን ያቤተሰብ ለምን አላለቀም? ይህን እንኳን አይቶ አልተዉንም ንቀታቸዉ ያዉ ነዉ።" (14/7/2011)

ሰፋ ማመሳኒ የ30 አመት ወጣት ሲሆን ከሸክላ ሰሪ ማህበረሰብ አካል ነዉ። የአካባቢዉ ማህበረሰብ ከሙያቸዉ ጋር እንዲሁም ጋብቻን በተመለከተ ምን አይነት አመለካከት አለዉ የሚለዉን ጥያቄ ሳነሳለት የመለሰልኝ መልስ የሚመለከተዉን ይመስላል።

“Nuti ijoollee jaraa waliin wal fuudhuun waan yaadamu natti hin fakkaatu. Jarri akka waan nuti gad aanaa taaneetti nu yaadu. Intala

isaanii nutti kennuu mitii akka waan abaarsa qabnuu mucaa isaanii baadhatanii yoo diqqa itti dhufneyyuu nun dhoksu. Karaa irratti yeroo lama na qunnameera. Akkan of jibbu na godheera. Amma amma wal fuudhuun eegalameera. Fuuldurattis itti fufuu danda'a hin beekamu. Ani gara kootiin ilaalchi isaanii kun keessoo isaaniitii waan bahu waan natti hin fakkaanneef utuu hafeen jedha."

"እኛ የነሱን ልጆች ማግባት የሚታሰብ ነገር አይመስለኝም። እነሱ እኛን የሚያስቡት እናሳ እንደሆን ነዉ። አይደለም ልጃቸዉን ወደኛ ሊጨምሩ እርግማን ያለን ይመስል በአጋጣሚ እጻናት ይዘዉ ከመጣንባቸዉ ይሸፋፍናሉ። በመንገድ ላይ ሁለቴ አገጥሞኛል። እራሴን እንድጠላ አድርጎኛል። አሁን አሁን መጋባት ጀምረዋል። ሊቀጥል ይችላል አይታወቅም። እኔ በበኩሌ ይህ አመለካከታቸዉ መቼም ከዉስጣቸዉ የሚወጣ ስለማይመስለኝ ቢቀር ባይነኝ።" (14/7/2011 ለሊሳ ቡላ)

ከፋጡማ ና ከሰፋ አስተያት የምንረዳዉ ሀሳብ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ያለዉ አሉታዊ አመለከሰከት የከፋ በመሆኑ ከፍተኛ የስነ ልቦና ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑን ነዉ። ስለዚህ እንደ ዋና ምክንያት የሚገልጹት ከሸክላዉ ስራ ጋር በተያያዘ ምክንያት እንደሚዘለፉ እንጂ እነሱ ምንም ችግር የለብንም ባዮች ናቸዉ ።

ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ያለዉ አሉታዊ አመለከሰከት የከፋ በመሆኑ በለሙያዎቹ ተሸማቀዉ እና እራሳቸዉን እስከመጥላት የደረሱበት ዋናዉ ምክንያት እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ቦታ ሁሉ ትችት እንደሚቀርብባቸዉ እና ልጆቻቸዉ ወደ ትምህርት ቤት ለመማር ሄደዉ ከልጆች ቢጣሉ እያለቀሱ የሚመጡት "ፉጋ" አሉን በማለት እደሆነ ነዉ የሚናገሩት ።

ሀ/ሱልጣን አባራያ የ68 አመት አዛዉንት ናቸዉ። ማህበረሰቡ ከሙያቸዉ ጋር እንዲሁም ጋብቻን በተመለከተ ምን አይነት አመለካከት አለዉ ለሚለዉ ጥያቄ እንድህ አጫዉተዉኛል።

"Nutiif uummatni guddaan walittii fageenya guddaa qabna. Jarri nuyiin akka gadi-aanaatti nu ilaalu. Barcuma nuti irra teeny irra hin ta'anu. Nutis arginee kan jaraa irra hin teenyu. Amma amma daawaa masjiidaa himamu dhagahanii jijjiiramaa dhufani malee duraan masjiidattillee nu biraa ka'anii

bakka jijjiirratu. Akkamitti nama akkanaatii wajjin waa.ee gaaa’ilaa yaadda? Maqaan keenya fugaadhaaf gadheedha. Yeroo tokko maal ta’e seetemasjiida ijaaruuf hundi keessanuu humnaan, qarshiidhaan yookin nyaata fidunis ta’ee karaa dandeessanuun hirmaadhaa nuun jedhani. Masjiidni kan hunda keenyaa waan ta’eef nutis itti hirmaanne. Nyaata nuti geessine nyaachuu didani. Hojii masjiida ijaaruutti baayyinaan kan dhihaatan ijoollee keenya turan. Baayyee itti dhaga’ame. Guyyaa itti aanutti ijoolleen keenya baayyee hir’ataa dhufan. Imaamni masjiidaa dhimma kana hubatanii daawaagodhani. Sana booda waliin nyaachuus ta’ee dhuguu akkasumas yeroo gaddaa walitti dhihaachuu egalle. Yeroo ammaa sirriitti nagaa wal gaafanna. Garuu gaa’ila hin geggeessinu.”

“እኛ ና ትልቁ ማህበረሰብ በጣም ትልቅ ርቀት አለን፡፡ እነሱን እኛን እንደ አናሳ ነዉ የሚያዩን፡፡ እኛ የተቀመጥንበት ወንበር ላይ አይቀመጡም፡፡ እኛም ደርሰን የነሱ ላይ አንቀመጥም፡፡ እንዲሁም አሁን አሁን ከየመስጂዶቹ ዳዋ(ሀይማኖታዊ መልዕክት) እየሰሙ እየተለወጡ መጡ እንጂ ከዚህን በፊት በመስጅድ እንኳን ብንገናኝ እኛ መሆናችን ካወቁ ከጎናች ተነስተዉ ቦታ ይቀይራሉ፡፡ እንዴት ከእንደዚህ አይነት ሰዉ ጋር ስለ ጋብቻ ታስብያለሽ? ስማችን ፋጋና መጥፎ ነዉ፡፡ አንዴ ምን ተፈጠረ መሰለሽ መስጅድ ለመስራት ሁላቹም የየድርሻቹን በምትችሉት መንገድ በጉልበትም፣ በገንዘብም ፣ለሰራተኞች ምግብ በማድረስም እንድንሳተፍ ጥሬ አቀረቡ፡፡ እንግዲህ መስጂድ የሁሉም ነዉ እና እኛም ተሳተፍንበት፡፡ ከዛ ምግባችንን አገለሉብን፡፡ በመስጂዱ ስራ በብዛት የተሳተፉት የኛ ልጆች ነበሩ፡፡ እና በጣም ቅር አላቸዉ፡፡ በሁለተኛዉ ቀን ልጆቹ እየቀነሱ መጡ፡፡ ሼኪዉ ጉዳዩ ስለ ገባቸዉ ይህን አስመልክተዉ ዳዋዳዋ(ሀይማኖታዊ መልዕክት) አደረጉ ከዛን ጊዜ በኋላ አብረን መብላትም ሆነ መጠጣት ፣ እንዲሁም በለቅሶ በጣም መቀራረብ ጀምረናል፡፡ አሁን አሁን ጥሩ ሰላምታ እንለዋወጣለን፡፡ ነገርግን አንጋባም፡፡"

አባራያ አባዱራ የ73 ዓመት አዛዉንት ሲሆኑ ከሽክላ ሰሪ ማህበረሰብ ወጭ ናቸዉ፡፡ የአከባቢዉ ማህበረሰብ ለባለ ሙያዎቹ ከስራቸዉ ጋር በተያያዘ ስለሚሰጧቸዉ አሉታዊ ስሞች እንዲሁም ጋብቻን በተመለከተ ምን ይላሉ? ስላቸዉ የሚከተለዉን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

"Gaa'ila ilaalchisee yoomiyyuu akka isaan itti yaadan hin ta"u. wal fuudhan inni jedhamus dhuguma. Garuu maatii harka qalleeyyii irraati. Kanaafuu itti hin fufn yaada jedhun qaba. Ijoollee keenyatti waan himamuu qabu itti himaa guddisuun ga'ee keenya. Jiruu ummataa garagaraa irratti waliin hirmaachuu eegalleerra. Keessattuu masjiidaafi gadda irratti. Haa ta'uu garuu waan keessa keenya jiru haqnee baasuu hin dandeenyu. Yoo ifa hin baanes ilaalchi keenya sanuma. "

"ጋብቻን በተመለከተ መቼም ቢሆን እነሱ እደሚፈልጉት አይሆንም፡፡ አዉን ተጋቡ የሚባሉትም እዉነት ነዉ፡፡  ነገር ግን ከአቅመ ደካማ ቤተሰቦች ነዉ፡፡ እና አይቀጥል ባይ ነኝ፡፡ ለልጆቻችን መንገር ያለብንን እየነገርን ማሳደግ የኛ ድርሻ ነዉ፡፡ በማህበራዊ ኑሮ በተለያዩ ቦታ ላይ አብረን መሳተፍ ጀምረናል፡፡ በመስጂድና በለቅሶ ያም ቢሆን በዉስጣችን ያለዉን ነገር ፍቀን ማዉጣት አንችልም፡፡ በይፋ ባይወጣም አመለካከታችን ያዉ ነዉ፡፡"

እንግዲህ እስካሁን ከቀረቡት የተለያዩ ሴቶች እና ወንዶች መረጃ አቃባዮች ሀሳብ መረዳት የሚቻለዉ ከሸክላ ሰራተኞቹ ዉጭ ያሉ ማህበረሰብ በለሙያዎቹን በሚመለከት ያላቸዉ አሉታዊ አስታየት በጣም ከፍተኛ የሆነ ነዉ፡፡ ይህም ባለሙያዎቹ የገጠሟቸዉን ችግሮች እንደቀልድ መርሳት የማይችሉት ትልቅ ጫና ከመሆኑ የተነሳ በሙያቸዉ አፍረዉ እስከ መማረር ደርሰዋል፡፡

የሙባለሙያዎቹ ከሙያቸው ጋር በተያያዘ ባጋጠማቸው ችግሮች ምክንያት በሙያው ብዙም ትርፋማ አለመሆናቸው ተገልጸዋል ፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ እነዚህ ባለሙያዎች ከገጠማቸው ችግሮች ጋር እየተጣጣሩ  ከሙያው ጋር እስካሁን ቢቆዩም  ወደ ፊት ሙያውን ተረካቢ ናቸዉ  ተብለው ለሚጠበቁት ልጆቻቸው ሙያቸውን እንዳያወርሱ በአነስተኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የሙያው ቀጣይነት አደጋ ላይ መውደቁን አመላካች ነው፡፡

እንደ ብዙዎቹ መረጃ አቀባዮች እምነት ከሆነ በአሁኑ ጊዜ ባለሙያዎቹ ሙያውን በማከናወን ላይ የሚገኙት ጥበቡን ወደውት ሳይሆን ለእለት ጎሮሮ ማሚያቸዉ  ለማግኘት ሲሉ የሚከውኑት መሆኑ ነው፡፡ የሚገርመዉ  ባለሙያዎቹ የተሻለ ገቢ ቢኖራቸው ሙያውን

ለማቋረጥ ፍቃደኛ መሆናቸው ደጋግመው እየገለጹ ይገኛሉ እንጂ የቤተሰቦቻችን ዉርስ ነዉ አንተወዉም የሚሉ የሉም፡፡

ሀ/ወሬ አ/ቡልጉ  የሸክላ ስራ የሚያከናውኑት ጥበቡን ወደውት አለመሆኑን እና የተሻለ ገቢ ቢያገኙ ስራውን ለማቋረጥ እንደ ማያንገራግሩ  የገለጹት በሚከተለው መልኩ ነው፡፡

"Qoonqoodhaaf malee gammachuudhaan miti kanan hojjetaa jiru. Jireenya koo jijjiiruu utuu danda'ee hamma har'aa fooyya'ee ture jiruun koo. Wantin buufadhe yoo jiraate biyyoo baatanii deemuu, dhukkuba dugdaafi human fixuudha. Utuun dhiisee taa'ee guyyaa tokkoof nama na nyaachisu hin argadhu kanaafuu utuun lubbuun jiruu utuun hin nyaatin hin du'u jedheeni malee qotiyyoo lama utuun qabaadhee biyyoo hin qotu? Hamma hamma immoo humni koo hanqataa jira. Waanuman hojjedhu dhabeen tattaafataa jira."

"የእለት ጎሮሮን ለመድፈን ነው እንጂ የምሰራዉ ደስተኛ ሁኜ አይደለም፡፡ ሕይወቴን የሚለዉጥልኝ  ቢሆን እስካሁን ደስተኛ ያደርገኝ ነበር፡፡ ያተረፍኩት ነገር ቢኖር  አፈር በመሸከም እና በማጓጓዝ የወገብ በሽታ  እና አቅም መጨረስን ነዉ፡፡ ትቼ ብቀመጥ ለአንድ ቀን የሚያጎርሰኝ አላገኝም እና በሕይወት እያለዉ ሳልበላ ልሙት ብዬ እንጂ አንድ ሁለት በሬ ቢኖረኝ ለማን ብዬ ነዉ አፈር የምቆፍረዉ? አሁን አሁን እማ አቅምም እያጠረኝ መተዋል፡፡  የምሰራው ጠፍቶኝ እታገላለዉ፡፡"

## 4.7 የጥሬ እቃ አቅርቦት ችግር

Bricks (1967;13) የሸክላ አፈር በማንኛዉም የአለም ክፍል የሚገኝ ቢሆንም ጥራት ያለዉ አፈር ለማግኘት  ባለሙያዎቹ ረዥም መንገድ ይጓዛሉ በማለት ገልጸዋሏ ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ  የለሊሳ ቡላ የሸክላ ስራ ባለሙያዎቹ ለሸክላ ስራ የሚሆኑ ጥራት ያለዉ የዋልካ(ቦረሬ) አፈር እና  ሸክላዉ ቀይ ቀለም እንዲይዝ የሚያደርገዉን ቀይ አፈር ለማግኘት ረጅም መንገድ ይጓዛሉ፡፡ ባለሙያዎቹን የገጠማቸዉ ችግር ጥሬ እቃ ለማምጣት ረጅም መንገድ

መንዝ ብቻም አይደለም። ይህን ረጅም መንገድ ተጉዘዉ ከፈለጉበት ቦታ የፈለጉትን ያህል አፈር ወስዶ ለመመለስ አለመታደላቸዉም ጭምር እንጂ። መሬቱ የባለሀብት እንደ መሆኑ ለባለቦታዉ ግብር መገበር እንዳለባቸዉ እና እየገበሩም እንደልባቸዉ እንዳይጠቀሙ የሚከለከሉበት ሁኔታ አጋጥሟቸዋል። ወ/ሮ ከንዚ ማመሳኒ ፣ ወ/ሮ ሚስኩ አወል እና ወ/ት ቡርቱካን ባደረግነዉ ዉይይት ወቅት "የጥሬ እቃ አቅርቦት ለወደፊት ይገጥመናል ብላችሁ ታስባላችሁ?" ለሚለዉ ጥያቄ የሚከተለዉን ምላሽ ሰተዉኛል ። "የሸክላ አፈሩን ቦታ የምንጠቀመዉ ከመንግስት ሳይሆን ከግለሰብ ነዉ ። ከዚን በፊት እደፈለግን የምንጠቀመዉን ባለንብረቱና የቀበሌዉ ኃላፊዎች ተጣልተዉ በዚህ የተነሳ እኛንም እንዳንጠቀም ከለከለን እና በልመና ነዉ እየተጠቀምን ያለነዉ ። ያዉም ከአንድ ሰዉ በአመት አምሳ ብር እየተቀበለ ነዉ"ብለዋል።

## 4.8 የሙያዉ ቀጣይነት

ባለሙያዎቹ ከሙያቸው ጋር በተያያዘ ባጋጠማቸው ችግሮች ምክንያት በሙያው ብዙም ትርፋማ አለመሆናቸው ተገልጿል ። በመሆኑም ምንም እንኳ እነዚህ ባለሙያዎች ከገጠማቸው ችግሮች ጋር እየተጣጣሩ ከሙያው ጋር እስካሁን ቢቆዩም ወደ ፊት ሙያውን ተረካቢ ናቸዉ ተብለው ለሚጠበቁት ልጆቻቸው ሙያቸውን እንዳይወርሱ በሚመስል ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም የሙያው ቀጣይነት አደጋ ላይ መውደቁን አመላካች ነው።

እንደ ብዙዎቹ መረጃ አቀባዮች እምነት ከሆነ በአሁኑ ጊዜ ባለሙያዎቹ ሙያውን በማከናወን ላይ የሚገኙት ጥበቡን ወደውት ሳይሆን ለእለት ጎሮሮ ማሚያቸዉን ለማግኘት ሲሉ የሚከውኑት መሆኑን ነው። የሚገርመዉ ባለሙያዎቹ የተሸለ ገቢ ቢኖራቸው ሙያውን ለማቋረጥ ፍቃደኛ መሆናቸው ደጋግመው እየገለጹ ይገኛሉ። እንጂ የቤተሰቦቻችን ዉርስ ነዉ አንተወዉም የሚሉ የሉም።

ሀ/ሙዳሬ አ/ቢያ የሸክላ ስራ የሚያከናውኑት ጥበቡን ወደውት አለመሆኑን እና የተሻለ ገቢ ቢያገኙ ስራውን ለማቋረጥ እንደማያንገራግሩ የገለጹት በሚከተለው መልኩ ነው። "የእለት ጎሮሮን ለመድፈን ነው እንጂ የምሰራዉ ደስተኛ ሁኜ አይደለም ሕይወቴን የሚለዉጥልኝ ቢሆን እስካሁን ደስተኛ የደርገኝ ነበር ።ያተረፍኩት ነገር ቢኖር አፈር በመሸከም እና በማንንዝ የወገብ በሽታ እና አቅም መጨረስን ነዉ ፡ትቼ ብቀመጥ ለአንድ ቀን የሚያጎርሰኝ አላገኝም እና በሕይወት እያለዉ ሳልበላ ልሙት ብዬ እንጂ አንድ ሁለት በሬ ቢኖረኝ ለማን ብዬነዉ አፈር የምቆፍረዉ አሁን አሁን እማ አቅምም እያጠረኝ የምሰራው ጠፍቶኝ እታገላለዉ።"

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ

በዚህ ክፍል ውስጥ ጥናቱ የቁሶቹን አሰራርና አገልግሎት፣ የቁሶቹን መነሻ ቅርፅ እንዲሁም ቁሶቹ የማህበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ በምን መልኩ ያሳያሉ? የሚለትን ጉዳዮች ተመልክቶ የተገኘዉ ፍሬ ሃሳቦች የቀረበበት ክፍል ነው። የጥናቱን ግኝትና ጥናቱ በተከናወነበት አካባቢ ላይ ለቀጣዩ ቢሰሩ መልካም ነው ያልኳቸውን ይሁንታዎች ታክሎው ቀርበዋል።

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በለሊሳ ቡላ ቀበሌ ማህበረሰብ ባህላዊ የሸክላ ስራ እና የኑሮ ዘይቤ መተንተን አላማ አድርጎ የተካሄደ ነዉ። ጥናቱ ባተኮረበት ቦታ ላይ በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች አሰራርና አገልግሎት ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ታውቀዋል።

ማህበረሰቡ በመገልገያ ቁሶቹ አማካኝነት ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውን እና ባህላዊ አኗኗራቸውን የሚያሳዩባቸው መሆናቸውን በጥናቱ ታውቀዋል።በለሊሳ ቡላ አከባቢ አዉንም ድረስ የሸክላ ስራ ከጥሬ እቃ አቅርቦት ጀምሮ ሸክላዉን ሰርቶ በማጠናቀቅ ገብያወስዶ እስከ መሸጥ ድረስ ያሉ ሂደቶች  ሙሉ በሙሉ የሚከናወነዉ በሴቶች ነዉ። ወንዶች የእረሻ ስራ ያከናዉናሉ እንጂ በሙያዉ ምንም አይነት እገዛ አያደርጉም ።

የሸክላ ስራ በሴቶች የሚከናወነው አብዛኛዎቹ ቁሶች በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸውና የአሰራር ሂደታቸውም ከቤት ውስጥ ስራ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት መሆኑ ታውቀዋል ።

የጥናቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ በመስክ ቆይታ ቃለ መጠይቅ ፣መልከታና ተተኳሪ ቡድና ዉይይት በመረጃ መሰብሰብያነት  ተገልግላለች ። መረጃዎቹ በተፈጥሮአዊ መችት የተገኙ ሲሆነኑ በቨዲዮ ካሜራ ፣ በቴፕ እና በፎቶ ግራፍ ምስል ተቀርጸዋል ። ባለሙያዎቹ ባህላዊ እዉቀታቸዉን ተጠቅሞ የተለያዩ የሸክላ ዉጤቶችን በመስራት ለገብያ ያቀርባሉ ። በባለሙያዎቹ የሚሰሩ የሸክላ ዉጤቶች ለባለሙያዎቹም ሆነ ለተጠቃሚዉ ማህበረሰብ የእለተ ተእለት ግልጋሎት የሚዉሉ ናቸዉ ።

ባለሙያዎቹ ባህላዊ እዉቀታቸዉን በመጠቀም አሁንም ድረስ ሙያቸዉን እያከናወኑ ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ባለዉ አሉታዊ አመለካከት አንጉል ስሞችን መስጠት ፣ጋብቻና በሌሎች ማህበራዊ ግንኙነቶች የተነሳ ለተለያዩ ስነ ልቦናዊ ችግሮች ተጋልጠዋል ።

በስተመጨረሽም ባለሙያዎቹ ከሙያቸው ጋር በተያያዘ ባጋጠማቸው ችግሮች ምክንያት በሙያው ብዙም ትርፋማ አለመሆናቸው ተገልጿል። በመሆኑም ምንም እንኳ እነዚህ ባለሙያዎች ከገጠማቸው ችግሮች ጋር እየተጣጣሩ ከሙያው ጋር እስካሁን ቢቆዩም ወደ ፊት ሙያውን ተረካቢ ናቸዉ ተብለው ለሚጠበቁት ልጆቻቸው ሙያቸውን እንዳያወርሱ በከፍተኛ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም የሙያው ቀጣይነት አደጋ ላይ መውደቁን አመላካች ነው።

## 5.2 የይሁንታ ሃሳብ

በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ የሚያሳዩ መሆናቸው ታውቀዋል። ባለሙያዎቹ ቁሶቹን ሲሰሩ በአካባቢያቸው የሚመለከቱትን ቅርፅ መነሻ አደርገው ነው። ቁሶቹ ጥቅል የሆነ ለውጥ እንድያመጡ ይህሽጋገር ዘንድ እንዲሁም ባለሙያዎቹ በሙያቸዉ እንዲ ኮሩና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባህላዊ ጥበብ ለቀጣይ ትዉልድ ይሽጋገር ዘንድ አጥኝዋ የሚከተለትን የይሁንታ ሃሳቦች ሰንዝራለች።

- ✓ ባህላዊ የሸክላ ዉጤቶች የሀገር ሽማግሌዎችና የሚመለከታቸው አካላት በውሁደት በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማንነት መግለጫ መሆናቸውን ለማህበረሰቡ ተከታታይ ግንዛቤ ቢፈጥሩ፤
- ✓ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ከሚመለከታቸው አካለት ጋር ጥምረት በመፍጠር ስለ ሸክለ ስራ የሚያበረታቱ ድራማዎችን በቪዴዮ ቀርፀው ማህበረሰቡ በብዛት በሚገኙባቸው ቦታዎች ላይ እንደአመቺነቱ ቢያሳዩ፤
- ✓ የወረዳው ጥቃቅንና ንግድ ኢንደስትሪ ጽ/ቤት ተተኪ ባለሙያዎችን ለማፍራት የገንዘብ አቅርቦት ቢያመቻቹላቸው፤
- ✓ በትምህርት ቤት ውስጥ የባህል ጥናት የሚባል ክበብ ቢቋቋምና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ ቢደረግ ጥሩ ውጤት ይመጣል የሚል ሃሳብ አለኝ

- ✓ ባለሙያዎቹ በሙያቸዉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መንግስት የሸክላ አፈር መቆፈርያ መሬት ቢሰጣቸዉ እና የሸክላ ዉጤቶችን ተፈላጊነት በተለያየ መልኩ ቢያስፋፉ
- ✓ በአካባቢዉ የሸክላ ስራ የሚከወነዉ በሴቶች መሆኑ ተገልጿል በተለያየ መንገድ ወንዶችን የማሳተፍ ስራ ቢሰራ ባይ ነኝ።

# ዋቢዎች

ሀብታሙ እንግዳው፡፡(2001)፡፡ ‹‹በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ሻሞ ጉድጓዲት ገጠር ቀበሌ የሻሞ መድሃኒያለም ሸክላ ስራ ውጤቶች የአሰራር ሂደትና ጠቀሜታ ትንተና"፣ ኤም.ኤ.ዲግሪ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ለማ ንጋቱ፡፡(1999)፡፡ "በየም ብሄረሰብ ጾታ ተኮር ተረቶች የወንድና ‹ምስል›› ትንተና"፤ ኤም.ኤ.ቴሲስ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰለሞን ተሾመ ፡፡(2007)፡፡ <u>የፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ</u>፤ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ አዲስ አበባ፡፡

አስቴር ሙለ ፡፡(2000)፡፡ ‹‹ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሳቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ››፤የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍል ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(1992)፡፡ <u>የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን</u>፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተዲስ አበባ፤ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(2009)፡፡ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር</u>፤ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ Tefera Seyoum Printing Press.

ደምስ መሸሻ ፡፡(2009)፡፡ "ባህላዊ የሸክላና አንጥረኝነት ስራ በክስታኔ ማህበረሰብ" ፤አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

ፍቃደ አዘዘ ፡፡(1991)፡፡ <u>የስነቃል መምሪያ</u>፤አዱስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ዴርጅት፡፡

Beals,L. Ralph and Harry Hoijer,1958. <u>An Introduction to Anthropology</u>. Los Angeles,University of California..

Bricks, Tony, 1967. <u>The Art of the Modern potter</u>.London;Country Life Limited.

Bronner, J. Simon, 1986. “Folk objects.” In folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Elliot Oring (ed.). Logan, Utah; Utah State University press.

Cleary,Mc Ann, 2017. “Material Culture” on line.WWW.http://Mc.Ann Cleary,html.2004.. Saturday,March 11,8:25:14 PM.

Dorson, Richard, 1972. M ed. Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London:The University of Chicago Press.

Fleming,E.McClung, 2017. “Artifact study;A proposed model.’’ Available on line at:URL:http//WWW.jstor.org/view/00840416/pdf.Saturday,March11,7:07:21 PM

Gedef Abawa, 2005. An Ethnoarchaeological Investigation of Pottery Making Among Traditional potters of Gondar. Department of Archaeology, M.A.Thesis, Addis Ababa university.

Glassie, Henry. Folkloristic study of the American Artifact;objects and objectives

Goldstein, Keneth S, 1974. AGuide for Field Workers in Folklore. By Folklore Associates, Inc. Hatboro, Pennsylivania; Republished by Gale Research company, Book Tower, Detroit,

In Hand book of American Folklore, 1983. Richard M.Dorson/ed/. Bloomington; India University press.

Jackson, Bruce. Feildwork,1987. Urbana and Chicago: University of Illinois Press.

Marchese,Ronald T, 1984. “Material culture and Artifact classification.” In American Material culture;The shape of Things Around us. Edith Mayo/ed./.Bowling Green;Bowling Green state university popular press.

Garuma, 2008. Omonada Written statistical Report. A report from Agricultural beareu; Educational Beareu; Culture and Tourism Beareu And Health Beareu

Pankhurst, Richard, 1964. “The old time hand craft of Ethiopia” In Ethiopian observer. Published in Ethiopia and Britain; Vol. 8 No. 3. Pp. 221-242,

Prown,J.David, 2017. “Mind in Matter: An Introduction to Material culture Theory and Method.” online Available at:URL:LttP;//WWW.Jstor.org/about/terms. PP.7-10; Saturday, March 11, 7:23:20 PM

Schelter,Thomas, 2017. “Understanding the nine models of material culture Interpetation.” online Available at:http//WWW.btnep.org. PP.7-8; Saturday, March 11,7:01:43 PM

Silverman, Raymond A. (ed.), 1999. Ethiopia: Traditions of Creativity. East Lasting; Michigan state University Museum

Takele Merid, 2007. "Gendered Culture Pottery as Women’s Activity in Ethiopia:A case Study of Selected Cites in Addis Ababa and its Surroundings." Addis Ababa University;School of Graduate studies,MA. Thesis in Ethiopian Studies.

Tsehai Berhane, 1991. “Gender and Occupational Potters in Wolayta Imposed Femininity and Mysterious survival Ethiopa.” In Gender Issues in Ethiopa. Addis Abeba Univarsity ; Institute of Ethiopa Studies.

Woodward, 2007. Understanding Material Culture. London, sage publications.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

## የአውራ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | እድሜ | መኖሪያ አካባቢ | የስራ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀ/ሱልጣን አባራያ | ሴ | 68 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 2 | ወ/ሮ ካንዚ ማመሳኒ | ሴ | 36 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 3 | ወ/ሮ አሊማ ማሀመድሳኒ | ሴ | 20 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 4 | ወ/ሮ ፋጡማ አባተማም | ሴ | 40 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 5 | ሀ/ ሙሂዲን አ/ጊዲ | ሴ | 40 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 6 | ሀ/ቢያ አባመጋል | ሴ | 60 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 7 | ሀ/ሱልጣን አ/ራያ | ሴ | 45 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 8 | ሀ/ነዚፍ አ/ዱራ | ሴ | 38 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 9 | ሀ/ካሚል አ/ጎጀም | ሴ | 45 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 10 | ሀ/ኒያ አ/ፊጣ | ሴ | 40 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 11 | ወ/ሮ ኡሚ ሱለይማን | ሴ | 38 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 12 | ሀ/ቆሮ አ/ሚልኪ | ሴ | 32 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 13 | ሀ/ራያ ሼ/ከማል | ሴ | 42 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 14 | ሀ/ነዚፍ አ/ዱራ | ሴ | 35 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 15 | ሀ/ወሬ አ/ቡልጉ | ሴ | 37 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 16 | ሀ/ቆሮ አ/ቦር | ሴ | 42 | ለሊሳ ቡላ | ታሪክ አዋቂ |
| 17 | ቡርቱካኒ አ/ጂሃድ | ሴ | 29 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 18 | አሊማ አ/ጀበል | ሴ | 38 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |
| 19 | ሰፋ ማመሳኒ | ወ | 30 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 20 | ወ/ሮ አልፍያ አ/ድልቢ | ሴ | 33 | ለሊሳ ቡላ | የሸክላ ስራ ባለሙያ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 21 | ማህመድ አ/ጊሳ | ወ | 20 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 22 | አ/ራያ አ/ዱራ | ወ | 73 | ለሊሳ ቡላ | ታሪክ አዋቂ |
| 23 | ሱልጣን አ/ ተማም | ወ | 32 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 24 | ማመሳኒ ታጁ | ወ | 18 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 25 | ሀ/ከማል አ/ኦሊ | ሴ | 40 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 26 | ሼ/አወል አ/መጫ | ወ | 42 | ለሊሳ ቡላ | የአይማኖት መሪ እና ታሪክ አዋቂ |
| 27 | አጊሳ አ/መጋል | ወ | 75 | ለሊሳ ቡላ | ታሪክ አዋቂ |
| 28 | አ/ተማም አ/ቡልጉ | ወ | 61 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 29 | አ/ማጫ አ/ገዊሳ | ወ | 75 | ለሊሳ ቡላ | ታሪክ አዋቂ |
| 30 | ጣሀ አ/ጊሳ | ወ | 68 | ለሊሳ ቡላ | ታሪክ አዋቂ |
| 31 | ሀ/ካነዚ ሀጂ | ሴ | 42 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ |
| 32 | አ/አሊ አ/ዱራ | ወ | 39 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 33 | አለዉያ አ/ተማም | ሴ | 20 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 34 | አሊማ ረያ | ሴ | 22 | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 35 | ሐ/መደድ ኣ/ ኦሊ | 55 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ ቤተሰብ |
| 36 | ሃቢባ ዜኑ | 22 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | የሽክላ ስራ ባለሙያ |
| 37 | ናስር ኣ/ኦሊ | 32 | ወ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 38 | ኣ/ቢያ ኣ/ዱራ | 60 | ወ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 39 | ርዳ ኣ/ዱራ | 46 | ወ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 40 | ኣዎል ቃሲም | 35 | ወ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 41 | ኣ/ጎጃም ኣ/ቡልጉ | 57 | ወ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 42 | ሓ/ዲልቢ ኣ/ኦሊ | 70 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 43 | ወ/ሮ ሙዳሬ ቢያ | 42 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 44 | ወ/ሮ ራቢያ ጀማል | 26 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |
| 45 | ሀ/ካንዚ ኣ/ጅሃድ | 67 | ሴ | ለሊሳ ቡላ | ለሎች ማህበረሰቦች |

# አባሪ ሁለት

## የሸክላ ስራ ባለሞያዎች ለማወያየት የቀረቡ ጥቄዎች

1. የተሳታፊዎቹ ሙሉ ስም እድሜ የቤተሰብ ብዛት የትውልድ ቦታ
2. በሸክላ ስራ ሙያ ለምን ያህል ጊዜ ቆይታችኋል?
3. ሙያውን ከማን ለመዳችሁት ?
4. ምን ምን እቃዎችን ትሰራላችሁ ? አሰራራቸውስ እንዴት ነው?
5. የምትሰሯቸው የሸክላ ውጤቶች ዋጋቸው ምን ያህል ነው? በስራው የድካማችሁን ዋጋ እያገኛችሁ ነው?
6. በሸክላ ስራ ሂደት የወንዶች ድርሻ ምንድነው?
7. መንግስት ከስራችሁ ጋር በተያያዘ ምን እገዛ አድርጎላችኋል?
8. መንግስት ወደፊት ከስራችሁ ጋር በተያያዘ ምን እንዲያደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?
9. ወደፊት የአፈር የገሃ ድንጋይ የእንጨት እጥረት ይገጥመናል ብላችሁ ትሰጋላችሁ?
10. ህብረተሰቡ በተለይ በሰራተኛው ውጭ ያለው ለእናንተና ለሙያችሁ ምን አስተያየት አለው ? ምን ምን ይላችኋል፡፡ የእናንተስ ምላሽ ምንድ ነው ?
11. ከሰራተኛ ውጭ ካለው ማህበረሰብ ጋር ትጋባላችሁ? ምን ምን ማህበራዊ ህይወት ላይ አብራቹ ትሳተፋላቹ ?
12. የተሻለ ገቢ ወይም ገንዘብ ብታገኙ ሙያውን ለማቋረጥ ፍቃደኛ ናችሁ?
13. ሙያውን ለልጆቻችሁ ወይም ከእናንተ ውጭ ላለው ማህበረሰብ ለማስተማር ፍቃደኛ ናችሁ?
14. በሸክላ ውጤቶች ላይ የተለያዩ ቅርጾች ጌጦች አሉ፡፡ የእነዚህ ቅርጾችና ጌጦች ጠቀሜታ ወይም መልእክት ምንድነው ?

# አባሪ ሶስት

## ለታሪክ አዋቂ ሽማግሌ እና ለባለሙያ ቤተሰቦች የቀረቡ ጥያቄዎች

1.ሙሉ ስም ፣ዕድሜ ፣የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት ፣መኖርያ አከባቢ

2.ቤተሰብዎ ከሰራተኛ ወገን ናቸው ? ከእርስዎ ቤተሰብ ሸክላ የሚሰራ አለ?

3.በዚህ አካባቢ ሸክላ ስራ መች ተጀመረ ? እነማን ጀመሩ?

4.ቤተሰብዎ ወይም በአጠቃላይ ባለሙያው ሸክላ በመስራቱ ምክንያት በማይሰራዉ ማህበረሰብ ዘንድ እንዴት ይታያል?

5.ከሸክላ ሰሪዎች ጋር ትጋባላችሁ ? ምን ያህል ቀረቤታ አላቹ ?

6.ከሰራተኛ ውጭ ያለው ማህበረሰብ እንዲያ ከብራችሁ ምን መደረግ አለበት ያላሉ?

# አባሪ አራት

## ለወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የቀረቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች

1.ሙሉ ስም ፣ዕድሜ ፣የትምርት ደረጃ ፣ የስራ ድርሻ

2.በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች የማህበረሰቡን አኗኗር በምን መልኩ ያሳያል?

3 .በሽክላ ባለሙያዎች ለሚሰሩ ቁሶች ማህበረሰቡ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል ?

4. በሽክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ሙለ በሙለ ለውጥ እንዳይ ይታይባቸዉ ያከናወናችሁት ተግባር ካለ ብገልጹልኝ ከላልሆነ ለምን?

6. የሸክለ ስራ በሴቶች የሚሰራው ለምንድ ነው?

7 የሸክላ ባለሙያዎች ቁሶችን ሲሰሩ መነሻ የሚያደርጉት ቅርፅ ምንድ ነው?

# አባሪ አምስት

## ለወረደው ጥቃቅንና ንግዴ ኢንደስትሪ ጽ/ቤት የቀረቡ ጥያቄዎች

1፣ ሙሉ ስም ፣እድሜ ፣የትምርት ደረጃ ፣የስራ ድርሻ

1. በሸክላ ባለሙያዎች የተለያዩ ቁሶችን እንዱሰሩ ምን አይነት ድጋፍታደርጋለችሁ?

2. የሸክላ ባለሙያዎች ተተኪን እንዲያፈሩ የተከናወነ ተግባር ካለ ብትገልፁልኝከልሆነ ለምን?

3. በሸክላ ባለሙያዎች የሚሰሩ ቁሶች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎትምንድ ነው?

የሸክሊና አንጥረኛ ባሆሙያዎች ቁሶቹን ሲሰሩ መነሻ የሚያዯርጉት ቅርፅ ምንዴን ነው?

# አባሪ ስድስት

## ከሰራተኛው ወገን ውጭ ለሆኑ የአካባቢው ሽማግሌዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስም እድሜ የጋብቻ ሁኔታ የቤተሰብ ብዛት መኖሪያ አካባቢ
   ለሊሳ ቡላ  ያሉት ሸክላ ሰራተኞች ሸክላ ስራ መቼ እንደ ጀመሩ የሚያውቁት ካለ ቢነግሩኝ?
2. ሸክላ ሰራተኞቹ የዚሁ አካባቢ ነዋሪዎች ናቸው?
3. ከሸክላ ሰራተኞች ጋር ጋብቻ ትፈጽማላችሁ ? ማህበርስ ትጠጣላችሁ?
4. ሸክላ ሰራተኞችቹ ከእነሱ ውጭ ያለው ማህበረሰብ (ቡዳ) እያለ እንደሚሰድባቸው አጫውተውኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው? ለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ እምነቱ አላችሁ?

# አባሪ ሰባት

## ለጥቃትን አነስተኛ ንግድና እንዱስትሪ የስራ ኀላፊ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስም እድሜ የትምህርት ደረጃ የስራ ድርሻ
2. የሽክላ ሰራተኞችን ህይወት ለመለወጥ የተደረገ ሙከራ ካለ ቢነግሩኝ?
3. ባለሞያዎቹ ማህበረሰቡ የሚያደርስባቸውን መገልገል ለማስቀረት የተደረገ ሙከራ አለ?
4. በወረዳው ከሽክላ ስራ ጋር በተያያዘ ከአሁን በፊት የተካሄደ ጥናት አለ?
5. የሽክላ ስራ ሙያ በአከባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚሰጠው
6. ሽክላ ሰራተኞች በሙያቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ገበያ በማፈላለግ በኩል በመስሪያ ቤታችሁ የተደረገ እገዛ ካለ ቢነግሩኝ?
7. የሽክላ ስራ ጥበብ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ሰራተኞቹም በሙያቸው እንዲከበሩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?
8. ከሽክላ ስራ ጋርም ሆነ በአጠቃላይ ከእጅ ስራ ጋር በተያያዘ ሊነግሩኝ የሚችሉት አስተያየት ካለ ቢነግሩኝ?

# አባሪ ስምንት

አንድ መስከኛ የቁሳዊ ባህል ዉጠቶችን መስክ ላይ በመገኘት ለመሰብሰብ ና ለመሰነድ ሲነሳ የመስክ መሰነጃ (field documentation sheet) በማበጀት ቁሶችን ሊሰበስብ ይችላል። ቅፁ ላይ እንደ አስፈላግነቱ የሚጨመሩ ወይም የሚቀነሱ ነጥቦች እንደሚኖሩ ከግምት ዉስጥ በማስገባት የሚከተለዉን ልሆን እንደሚችል Somjee (1993:110-111) አመልክቷል

የመስክ መሰነጃ ቅፅ (field documentation sheet)

የት/ቤቱ/የት/ክፍሉ/የተቋሙ ስም______________ ቀን________________

ሀ. የቅሱ አይነት 1.___________የባለቤት ብሄረሰቡ ስም_________ የሰብሳቢዉ ስም____________

1. __________________ክልል_________________
2. __________________ዞን_______________ ወረዳ______________
3. __________________ቀበሌ______________ ጎጥ______________

ለ. የቁስ አገልግሎት

1. _______________ የተገልጋዩ ስም_____________
2. ________________________ ጾታ__________________________________________
3. _____________ እድሜ___________________
4. _____________ ወጣት___________________

ሽማግሌ___________________

ቅሱ አገልግሎት የሚሰጥበት ግዜ፦ ለበአላት_____________ ለሰርግ_____________

ሐ. ቅሱ የሚሰራባቸዉ ንጥረ ቁሶች ዝርዝር

1. ክብሪት______________ ቅርሳቸዉ ምን ይመስላል?____________
2. ከአፈር______________ መጠናቸዉ ምን ያህላል?_____________
3. ከድነጋይ_____________
4. ከእንጨት____________
5. ከአፅዋት_____________

መ. የባለሙያዉ ማንነት

- ስም______________ ባለሙያዉ ቅሱን የሚሰራብት ምክንያት፡ለራስ ነው____ለገበያ ነዉ____ ለዘመድ ነዉ___
- ፆታ______________ የገቤዉ ሁነታ- ዋጋ________
- እድሜ____________ ለሃገር ዉስጥ ገበያ_________
- የመኖሪያ አከባቢ_____________ ለዉጭ ገበያ_______________

ሠ. የቁስ አሰራር ደረጃዎች

- በመጀመሪያ ደረጃ ምን ይከናወናል?__________________________________
- በመጀመሪያ ደረጃ ምን ይከናወናል?__________________________________
- በመጀመሪያ ደረጃ ምን ይከናወናል?__________________________________
- በመጨረሻ ምን ይሆናል?__________________________________________

Somjee(1993:110-111) ባቀረበዉ ቅፅ መሰረት የተዘጋጀ

# አባሪ ዘጠኝ የፍቶ ንባብ





የሸክላ ሰሪ በተሰቦች ሸክላን ስያስጎበኙ        ቃለመጠይቅ ከአሊማ ጋር





የሸክላ መስሪያ አፈር        ቃለመጠይቅ ከብረቱካን ጋር





ቃለመጠይቅ ከሰፋ ጋር

ምጣድ ከመጠበሱ በፊት





እሳት ማንደጃ

ወጥ መስርያ ሸክላ





እጣን ማጨሻ

የቡና ማፈሻ